## ከመፅሐፉ ከተወሰዱ መነባበል ፡-

አቶ ለማ መገርሳ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት የለቀቁት ወደው ሳይሆን ተገደው ነው። እርሳቸውን ከክልል ፕሬዝዳንትነት ለመግፋት የተሄደበት መንገድ የኦህዴድ/ ኦዲፒን መተዳደሪያ ደምብ የተፃረረ ከመሆኑ በተጨማሪ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትን ስልጣን የገፈፈ ነበር። አንድ የክልል ፕሬዝዳንት ህግና ደምብን በተከተለ መልኩ ከፕሬዝዳንትነት ስልጣኑ መልቀቅ የሚችለው በሁለት መንገዶች ብቻ ነው። አንደኛው በገዛ ፍላጎቱ ስልጣኔን መልቀቅ እፈልጋለሁ በማለት የመልቀቂያ ደብዳቤ ለክልሉ ምክርቤት አስገብተው ተቀባይነትን ካገኘ ሲሆን፤ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ የክልሉ ምክርቤት ግምገማ አካሂደው የክልሉ ፕሬዝዳንት ባሳዩት የስራ አፈፃፀም ድክመት ምክንያት መቀጠል የለባቸውም የሚል ውሳኔን ካስተላለፈ ነው። አቶ ለማ መገርሳ ለኦሮሚያ ክልል ምክርቤት (ጨፌ) ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለመልቀቅ ያስገቡት የመልቀቂያ ደብዳቤ አልነበረም። የኦሮሚያ ክልል ምክርቤትም በእርሳቸው ዙሪያ ተሰብስበው ግምገማ በማካሄድ እርሳቸው ያሳዩት የስራ አፈፃፀም አነስተኛ በመሆኑ በፕሬዝዳንትነት መቀጠል የለባቸውም የሚል ውሳኔ አላስተላለፈም። . . . ከወራት በፊት እርሳቸው ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት አልለቅም በማለታቸው ሲመርዙአቸው ተሞክረው አልተሳካም።

========================

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ አክቲቬስት ጃዋር ሞሐመድን ቢሮዋቸው ድረስ በማስጠራት "ከአሁን በኋላ ወጣቱ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ ከማነሳሳት እንዲትቆጠብ አመከርሃለሁ፣ ከሼክ ሞሐመድ አላሙዲ ገንዘብ እንደተቀበልክ ደርሰንበታል። በህዝቡ ስም ገንዘብ ሰብስበሃል። " ብለውታል። . . .

========================

አቶ አባዱላ ገመዳ በለውጡ ሂደት ውስጥ ቲም ለማን የሚያግዝ መስለው ነበር የቲሙን አባላቶች የተቀላቀሉት። ሽፈት ሲገለጥ ተልዕኮአቸው ቲም ለማ ውስጥ ገብተው በማደከም አፍርሰዋቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ለመሆን ነበር። ይህንን አስቀድሞ ከህወሃት ጋር በመወያየት ተልኮውን ካሳኩት ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ እንደሚሾሙ ከህወሃት ቃል ተገብቶላቸዋል። እድላቸውን ለማስፈፀት ሲሉም ከህወሃት ጋር የተጣሉ አስመስለው ነበር የኦሮሞን ህዝብ ለመቅረብ የሞከሩት። በመጨረሻ ግን ከህወሃት የተቀበሉትን ተልዕኮና ጠቅላይ ሚኒስቴር የመሆን ህልማቸው በቲም ለማ ጥንካሬ ተጨናግፎባቸዋል። በ፱ኛው የኦዲፒ ጉባኤ ላይ በጡረታ ምክንያት በክብር የተሸኙት እኚ እኚህ ሰው አሁን በዶ/ር አብይ አህመድ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ልዩ አማካሪ በመሆን ተሹመው ኦሮሚያ ክልልን በእጅአዙር እያስተዳደሩ ይገኛሉ።

Dinsho Printing press

Price 150 Birr / 10 USD

# የተጠለፈ ትግል



# The Hijacked Revolution

ሙድህን ሲራጅ

ሐምሌ 2011 ዓ.ም

# የተጠለፈ ትግል

The Hijacked Revolution

በመድህን ሲራጅ

ሐምሌ 2011 ዓ.ም

© መድህን ሲራጅ ሐምሌ 2011 ዓ.ም

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው ።

1ኛ ዕትም

አስተያየትዎን mudhin_dinsho2012@gmail.com ላይ ይላኩልን



# ማውጫ

መታሰቢያ .............................................. . ..............................3
መግቢያ ..............................................................................6
የቤተ መንግስቱ ዘዋሪዎች ......................................................9
የአቶ አባዱላ ገመዳ ገባ ወጣ ፖለቲካ...........................................29
የፀጥታ መዋቅሩ አደረጃጀት ..................................................35
የዶ/ር አብይ አህመድና አቶ ለማ መገርሳ ጉዳይ ...........................45
አቶ ለማ መገርሳ ወደ ፌደራል የሄዱት ወደው ወይስ ተገደው?......63
አዲሱ የሙስና መረብ.............................................................68
በደህንነት ካሜራው አየታደኑ የሚገኙ ......................................78
የፌስቡክ ሰራዊቶች.............................................................82
የውጪ ምንዛሪው ነገር .........................................................85
የዜጎች መፈናቀል ቀውስ........................................................87
በአፋን ኦሮሞ የመገልገል ጥያቄ? ...........................................90
ሰውዬውና የሰውዬው መፅሐፍቶች ...........................................95
የመጪው ምርጫ ዕጣ ፋንታ......................................................98
ኦሮሞን የመከፋፈል ሴራ ..................................................... 102
ኦነግን የማኮላሸት ሴራ ........................................................111
የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች መተባበር አለባቸው ...........................12
የፊንፊኔ ውጋት...................................................................130
የፊንፊኔ ጉዳይ ከምን ደረሰ?....................................................134
ቀጣዩ የኦሮሞ ህዝብ ትግል ምን መሆን አለበት.............................138
የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከየት ተነስቶ ወዴት እየሄደ ነው?...................143
የኦሮሞ የነፃነት ትግል የትላንትናዎቹ ፈተናዎች................................145
የኦሮሞ የነፃነት ትግል ጠላቶች እነማን ናቸው...................................148
የኦሮሞ የነፃነት ትግል የዛሬዎቹ ፈተናዎች........... . ..................... 149

# መታሰቢያ

መታሳቢያነቱ ከሁለት ሶስት አመታት በፊት በነበረው ህዝባዊ ትግል ላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ብለው ለተሰው አገር ወዳድ ዜጎቻችን በሙሉ ይሁንልኝ ።





## መግቢያ

ባለፉት ሁለት ምዕተ-ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያየ መልኩ በመደራጀት በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በነበሩት መንግስታት ላይ ጥያቄ ሲያነሱ ቆይቷል፡፡ በ1960 ዎቹ ሲነሱ የነበሩት የዜጎች ጥያቄ የመሬት ባለቤትነትና ሰርቶ የመጠቀም አጀንዳ ያነገበ ሲሆን በጥያቄዎቹ ውስጥ የማንነት ጉዳይና የዴሞክራሲ ጥያቄም ብቅ ብቅ መለት ጀመሩ፡፡ ንጉሱም ጥያቄውን በብስለት ከማስተናገድ ይልቅ የተወሰኑትን ቡድኖች ለይተው ለመያዝ በመሞከርና የመላውን ህዝብ ድምጽ በመናቅ ለጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ባለመስጠታቸዉ በሃይል ተወግደው ሀገሪቷ በወታደራዊ አመራር ሥር እንዲትወድቅ ሆነ፡፡ የመሬት የባለቤትነት ጥያቄም በከፊሉ የተመለሰ ቢሆንም የማንነትና የዜጎች በመሬታቸው ላይ ተጠቃሚ አለመሆን በመንግሥት ላይ ከጥያቄም አልፎ ወደ ተቃውም በመሸጋገር በብሔርና በፖለቲካ አይዲኦሎጅ በተደራጁ ሃይሎች በ1983 ዓ.ም ወታደራዊው መንግሥት ሲወድቅና የሽግግር መንግስት ሲቋቋም የብዙ ዜጎች ጥያቄ እንደሚመለስ ተስፋ አድርገዉ ነበር፡፡ በሽግግር ወቅት በጥልቀትና በስፋት ሳይመከርበትና ከስምምነት ሳይደረስ አንዳንዱን የፓላቲካ ፓርቲ ገፍተው በማስወጣት ሀገርቷን የመምራት እጣ ፋንታ በኢህአዴግ(ህወሃት፤ ደኢህዴን፤ ብአዴንና ኦህዴድ ስብስብ) የበላይነት መሆኑ ተረጋገጠ፡፡ በኢህአዴግ ውስጥ የተሰበሰቡት የእህት ድርጅቶች ፓርቲ አመራር ከአመጣጣቸው ከምርኮ ምርኮ በቅብብሎሽ ለህወሃት ያደሩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ወክለናል ያሉትን ብሔር /ብሔረሰብ እንኳን ለይተው ካለማወቅ የተነሳ ህወሃት የሚያራምደውን ስተራቴጅካዊ የፓላቲካ

ጨወታ ሳይቋቋሙ ቀርተው ሀገርቷን ለከፍተኛ ኪሣራ ዳርጓታል። በዚህ አጋጣሚ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ህወሃት በኢህአዴግ ውስጥ ለፈጸመው ስውር ተንኮል የስርዓቱ አስፈጻሚዎች በስተቀር የትግራይን ህዝብ የማይወክልና የክልሉ ህዝብ እንደማንኛውም የሀገሪቱ ህዝቦች ተጎጂ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ኢህአዴግ የሀገርቷ ዜጎች አንግበው የተነሱትን የፍትሃዊ ተጠቃሚነትና የማንነት ጥያቄ የመለሱ በማስመሰል ህዝቦችን በመከፋፈል የአፈናና የዝርፊያ መዋቅር ዘርግተው መንግሥት የመሰረቱ ጥቅት ግለሰቦች ወደ ቡድን አድገው ህዝቡን ስያመርሩ ቆይተዋል። ይህንን የተገናዘበው መላውየኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ በለፉት 28 ዓመታት በልዩ ሁኔታ በተለየ ሰትራቴጂ ኦሮሚያ ላይ በማተኮር ሲደረጉ የነበሩ የፓለቲካና የኢኮኖሚ ብዝበዛ የተገነዘበው የኦሮሞና ኦሮሚያ ህዝብ ከዳር እስከ ዳር በመንቀሳቀስ ኢህአዴግ ላይ ጥያቄ መንሳት ጀመረ። በኃላም በተመሳሰይ ሁኔታ ተጎጂ የነበሩ የአማራ ክልል ዜጎችም ትግሉን ተቀላቅሏል። በደቡብ ክልልም የሲዳማ፤ የወላይታ፤ የሌሎችም የክልል ጥያቄና የአስተዳደር ወሰን ጉዳይ ውስጥ ለውስጥ ሲብላላና ወደ ተቃውሞ በመሸጋገር ላይ ነበር። እንዲሁም አዳጊ ተብለው ገሸሽ የተደረጉት የቤኒሻንጉል፤ የጋምቤላ፤ ሱማሌና አፋር ክልሎች በህወሃት የዘረፋ መዋቅር ለኮንትሮባንድ(አፋርና ሱማሌ) እንዲሁም በኢንቨስትመንት ስም ለመሬት ወረራ(ቤኒሻንጉልና ጋምቤላ) በመጠቀም በሚደረጉት የኢኮኖሚ አሻጥር የክልሉን ነዋሪ ቅሬታ አስገብተዋል። በአጠቃላይ ከላይ በተነሱት ምክንያቶች ዜጎች በመንግሥት ላይ ቅሬታ ስለአደረባቸው ባለፉት ሃያ አመታት በላይ በኦሮሚያ ሳይቋረጥ ሲካሄድ የነበረውን የለውጥ ፍላጎት ትግል እንዲቀላቀሉና ሀገር የሚመራው





የፖላቲካ ፓርቲ ራሱን እንዲፈትሽና የአመራር ለውጥ እንዲያደርግ አስገድዶታል።ለውጡ ከመጣ ወዲህ ምን ምን ተከናወኑ እውን ለውጡ የህዝቡን ጥያቄ ይዞ እየሄደ ነው ወይ? ፌድራሊዝሙስ እጣ ፈንታው ምን ልሆን ይችላል? ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እየፈጸሙ የሚገኙት ደባ ተገደው ነው ወይስ አስበውበት ነወ? የጸጥታ መዋቅሩ የኢኮኖሚና የፓላቲካ አሻጥር ከየት ወዴት? የመሳሰሉ ጥያቄዎች ከዚህ መጽሃፍ ያገኙታል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ይህን መጽሃፍ አግኝተዉ እንደሚያነቡና ራሳቸውን እንደሚፈትሹበት ተስፋ እናደርጋለን።

*መልካም የንባብ ጊዜ*

## የቤተመንግስቱ ዘዋሪዎች

በኢትዮጵያመሪዎች ታሪክ ንጉሰ ነገሥቱን፤ ፕሬዝዳንቱንም ሆነጠቅላይ ሚኒስቴሮቹን ለማመካር በሚል ሰበብ በየበተ-መንግሥቱ የሚሰገሰጉ ግለሰቦች በሀገራችን ለተደረጉት መልካም ሆነ መጥፎ ታርከ አሻራቸዉ የጎላ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነዉ:: ለምሳሌ በአጼ-ምኒሊክ ዘመን የቤተ-ክርስቲያን መሪዎችና የሸዋ ባለአባቶች ለንጉሱ የፓላቲካ ስኬት ትልቅ መጠቀሚያ ሆነው ይገኛሉ:: በአጼ ሃይለስላሴ ዘመንም በተመሳሰይ ሁኔታ የቀጠለ ቢሆንም የምዕራቡን አለም በማካተት በልዩ መስፈርት የተመረጡ ምሁራንን በመጠቀም ሀገርቷን ለመስተዳደር ተችለዋል::በኮሎኔል መንግሥቱ ዘመን በተለየ ሁኔታ በፖለቲካ አይዶሎጂ መሰረት ባደረገ መልኩ የጦር መሃንዲሶችና አብዮታዊ አስታሳሰብ ያላቸዉ ምሁራን ቤተ-መንግሥቱን ሲያማክሩ ነበር:: በኢህዴግ ዘመን በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሃያ አመታት የቤተ-መንግሥቱም ሆነ የጸጥታ መዋቅሩ ዘርና የፓላቲካ ታማኝነትን መስፈርት በሚያደርግ እንዲመራ ተደረገ:: ከጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በኃላ ቤተ-መንግሥቱም ሆነ የጸጥታ መዋቅሩ አመራር መላ `ያጣ ወጥነት የሌለው ከመሆኑም ባለይ ስውር ኮንትሮባንዲስቶች የፓላቲካውንና ኢኮኖሚውን መዋቅር ወደፈለጉበት አቅጣጫ የማዘር አቅም አጎልብቶ ነበር:: ዛሬስ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቤተ-መንግሥትና መንበረ-ሥልጣን በማን እጅ ነው?





### 1. አቶ አለማየሁ ከተማ

አቶ አለማየሁ ከተማ በማንነታቸው የሚኮሩ አገር ወዳድ ባለሀብቶችን ለህወሃት አሳልፈው በመስጠት ደባው ነበር በአጭር ጊዜ ውስጥ አንቱ ከተባሉ ተቋራጮች ውስጥ አንዱ ለመሆን የበቃው። የአገርን ሀብት በመዘበር ቱጃርና ተፅዕኖ ፈጣሪ ለመሆን የበቃት ይህ ወላዋይ የባለስልጣናት ጥገኛ ያለጨረታ አሸንፈው ያሰራው የጂማ ጋምቤላ የአስፋልት መንገድ ለአንድ አመት እንኳን አገልግሎት ሳይሰጥ ነበር ለብልሽት የተዳረገው።

ከትውልድ ቦታቸው ከኢሉባቦር በመነሳት ቤደሌ ደባና ቴክኒክና ሙያ የተማሩና በጋምቤላ ክልል የኮንስትራክሽን ሥራዎችን በቀዳሚነት ሲወስዱ ከነበረ በኃላ ከህወሃት ጋር በመስማማት በአፋርና በትግራይ ክልሎች ትልልቅ የቤትና የመንገድ ግንባተዎችን በመውሰድ ከፍተኛ ሥራ የሰሩ ተቋራጭ ናቸው:: ለኦሮሞ ህዝብ ብለው ከህወሃት ጋር ያልተስማሙ በማስመሰል ቼክ በማጭበርበራቸው በህግ ሊጠየቁ ሲሉ ሀገር ጥለው ስለ ሸሹ ድርጅታቸው ለከፍተኛ ኪሣራ ተዳርጓዋል:: በለውጡ ማግሥት ቆዳቸውን ቀይሮ ታጋይ በመምሰል በሥውር የቤተ-መንግሥቱ ጉዳይ አስፈጻሚ በመሆን ሰዎችን ሲያስሾሙና ሲያሽሩ ይታያሉ:: ከዋና አቃቢ ህጉ ከአቶ ብርሃኑ ጸጋዬና ከአገር ውስጥ ፀጥታ ኃላፊው አቶ ዳመላሽ ገ/ሚካኤል ጋር በመተባበር ባለሀብቶችን በማስፈራራት ከፍተኛ ገንዘብ የማሰባሰብ ሥራ እየተወጡ ይገኛሉ:: በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ የሚያዙትን ከፍተኛ መጠን ያላቸውን የውጪ ምንዛሬዎች በማፈን ለውጪ ሀገር ባንክ ያቃብላሉ:: በአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል አነፍናፊነት የሚያዘው

የውጭ ምንዛሬ ገንዘብ በአቶ ብርሃኑ ጸጋዬ የህግ ከለላነት በፈጣኑ አቶ አለማየሁ ከተማ አቀባይነት በውጪ ሀገር ባንኮች ይከማቻል ወይም በአሜሪካ ቤቶችን ይገዛል፡፡ ዝርዝሩ በዚህ መጽሃፍ ውስጥ ወደፊት የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

## 2. አቶ ብርሃኑ ጸጋዬ

በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ተወልደው ያደጉና የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ማግኘት ባለመቻላቸው በሰርተፍኬት ሥራ ጀምረው አህዴድ ውስጥ በመግባት ብዙ የኦሮሞ ወጣቶችን ለህወሃት አሳልፈው በመስጠት ለስቃይ የዳረጉበት ካሣ ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ሁኔታዎች ሲመቻችላቸው የመግቢያ ውጤት ማምጣት ከቅድመ አያታቸው መንዳር በሩቁ ተንጣሎ የሚታየውን የዳሸን ተራራን የመውጣት ያህል ከበዳቸው፡፡ አብሮ አደጋቸው የሆነውአቶ ደጄኔ (የኦሮሚያ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበረና በኃላ በእሳቸው ሚስጥር ያወጣብኛል በሚል ሰበብ ሆን ተብሎ በመኪና አደጋ ህይወቱ እንዲያልፍ የተደረገ) ማትሪክ ተፈትኖላቸው ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ገብተው ህግ እንዲማሩ ዕድል ተመቻችቶላቸው ከጨረሱ በኃላም በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል ተመድበው ስራ ጀመሩ፡፡ በምሥራቅ ተመድበው ሲሰሩ በነበሩበት ጊዜ ከባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር የገንዘብ ዝውውርና ህገ-ወጥ ንግድ ላይ ተሰማርተው ብዙ ገንዘብ ያከባቱና በአዲስ አበባ ከተማውስጥ የቪላዎች (በተለምደው ሳር ቤት ተብለው በሚጠራው አከባቢ ለኢምባሲ የተከራየ) እና የሪል ስቴት(ሲአምሲና አለም ገና) ህንጻዎች ባለቤት የሆኑ ቱጃር ለመሆን የቻሉ ዛሬ የህግና ፍትህ ተቋሙን በበላይነት እየመሩ የቤተ-መንግሥቱ ዘዋሪ ለመሆን በቅተዋል፡፡በእሳቸው





አመለካከት ገንዘብ የሁሉ የበላይ ነው ብለው የሚያሚኑና ምንም ስለ ተወከሉበት የኦሮሞም ሆነ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፋንታ ከቁብ የማይቆጥሩ የተሰጣቸውን የዋና አቃቤ ህግ ሥልጣን ተገን በማድረግ የትግራይና የኦሮሞ ባለሀብቶች ላይ አትኩረው በመስራት እያስፈራሩ በጣም ከፍተኛ ገንዘብ በመሰብሰብ በዋሽንግተን ዲሲ የብዙ ቤቶች በለቤት ናቸዉ፡፡

በጂማ የአህዴድ ጉባኤ ላይም ከወ/ሮ አዳነች አቤቤ ጋር ከፍተኛ የማጭበርበር ስተራቴጂ ነድፈው ከፌደራል እስከ ኦሮሚያ ክልል ተቋማት የፈለጉትን ሰው የማስመረጥና የማስቀረት ሲፈልጉ ሰዎችን አደራጅተውበት ስም እያስጠሩ በማሸማቀቅ ጉባዔ ጥለው እንዲሄዱ የማድረግ ተልዕኮ ወስደው የተሳካ ሥራ አከናውነዋል፡፡ በሴራቸውም ወ/ሮ ጣይባ ሁሴንና አቶ ኡመር ሁሴን ከሥራ አስፈጻሚነት እንዲወጡ፣ አቶ ሞቱማ መቃሳ፣ ወ/ሮ ደሚቱና አቶ ከፍያለዉ ከአህዴድ /ኦዲፒ/ ማዕከላዊ ኮሚቴነት እንዲወጡ አቶ አበበ ደግሞ ከኦዲት ኮሚቴ እንዲወጡ ተዳርጓል፡፡

ከፍተኛ ባለሀብቶችም እንዲመቱ ተልዕኮ ተሰጧቸው በእሳቸዉ በትረ ስልጣን ዱላ የተቃጣባቸውና እጅ መንሻ ሰጥተው የተረፉት የሰደሬ ሪዞሪትና ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ባላቤት አቶ ድንቁ ደያሳ የኢሊሊ ሆቴል ባለቤት አቶ ገምሹ በየነና አቶ አለም ተፈራ ከባለሀብቶች ውሸጥ የሚጠቀሱ፣ እንዲሁም ደግሞ ላለመመለስ የተመቱ የሊድ ስታር ኮሌጅ በላቤት ዶ/ር ገመቺስ ደስታ (LTVና Moa ቲቪ ባላቤት) በቀጣይ ትኩረት ውስጥ የገቡላቸዉ የካንትሪ ክላብ ባላቤት ዶ/ር መሰለ ኃይሌ እና ሌሉችም የቡና ላኪ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ (የኦሮሚያ ገቢዎች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር) እና ዶ/ር ሚሊኬሳ ሚደክሳ (የኦሮሚያ

መሬት ማናጅመንት ቢሮ ሃላፊ) በክልል ደረጃ የጉዳይ አስፈጻሚነት ሚና ተሰጥተዋቸዋል፡፡ አቶ ብርሃኑ አህዴድ ውስጥ ያሉ ነባር ሴት ታጋዩችንም ያማገጡ ሲሆን፣ አዲስ ገቢዎችንም ሞክረው ተሳክቶላቸዋል ሳይሳካላቸው የቀሩትንም ከሥልጣን አስነስተው አስባርሯል፡፡ ይህንንም ባገኙት አጋጣሚ እንደጀብዱ እያወሩ ሌሎችን ለማንበርካክ ተጠቅመውበታል፡፡

አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ከእርሳቸው ጋር ከጥቅም ጋር የተገናኘ ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን አቶ አዲሱ ቀበኔሳን ለእጩነት አቅርበው የስደተኞች ጉዳይ ፅህፈት ቤት ኮሚሽነር ሆኖ እንዲሾሙ አስደርጓል። የእነኚ ተሿሚና ተሿሚግንኙነት የሚጀምረው በፍትህ ዘርፍ ውስጥ ነው። የአገራችንን ፍትህ ጉዳዮች ሲያዛቡና ዜጎችን በፍትህ እጦት ሲያማርሩ የኖሩት እኚ የህግ ባለሙያዎች በረዥም ጊዜ ቁርኝታቸው ደሃ ዜጎችን በድለው ጥሪት ሊያፈሩ ችለዋል። ለሹመት የበቁት የስደተኞች ጉዳይ ጽህፈት ቤት ቀደም ብለው በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ስር ሲተዳደር የቆየ ከፍተኛ በጀት ያለውና ለስደተኞች ሲባል ከፍተኛ የውጪ እርዳታ የሚደረግለት መስሪያቤት ነው። ከደቡብ ሱዳን ተሰደው በኢትዮጵያ ጋምቤላ ክልል በሚገኙት አንድ ሚሊዮን አካባቢ ስደተኞች ስም የስደተኞች ጉዳይ ፅህፈት ቤት ከፍተኛ የሆነ እርዳታ እየተደረገለት ይገኛል። አቶ አዲሱ ቀበኔሳ ከሶስት ዓመት በፊት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ፕሬዝዳንት እያሉ ከወይዘሮ አስቴር ማሞ ጋር በመሆን የቄሮ ትግል ላይ የተሳተፉ የአካባቢው ወጣቶች ላይ ከ18-20 አመት የእስራት ፍርድ እንዲፈረድባቸው ያስደረጉ የአካባቢው ተወላጅ ናቸው። ለዚም ስራቸው በወይዘሮ አስቴር ማሞ ተጠቁሞ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዝዳንት ሆነው ለመሾም በቅተው ነበር። በተጨማሪም አቶ አዲሱ





ቀበኔሳ ከቀድሞ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተርና ከአሁኑ ታዳኝ አቶ ጌታቸው አሰፋ ጋር በመነጋገር ዶክተር አብይ አህመድ፣ አቶ ለማ መገርሳና ሌሎች 300 የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት እንዲታሰሩ የእስር ማዘዣ ትዕዛዝ ቆርጠባቸው ነበር። ከዚያ በኋላ አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ በተመረጡ ጊዜ አቶ አዲሱ ቀበኔሳን ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዝዳንትነት ባነሷቸው ጊዜ፣ መነሳት የለባቸውም ብሎ ሲከራከሩላቸው የነበሩት አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ናቸው። እኚ አዲሱ የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነር በጀኔቭ የሚካሄደውን የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ለመካፈል በአቶ በርሃኑ ፀጋዬ ትዕዛዝ ወደዛው አምርቷል። ቀደም ባለጊዜ ከሰብዓዊ መብት ረጋጮች ጋር በመመሳጠር ዜጎቻችን እንዲረገጡ፣ አካላቸው እንድጎድል፣ እንዲገደሉና ንብረታቸውን እንዲቀሙ ሲያደርጉና ሲያስደርጉ የነበሩት የጥቂት ግለሰቦችስብስብ ነው ዛሬም በለውጡ ማግስት የአገሪቷን የፍትህ ተቋማት በበላይነት እየመራና እያደራጀ የሚገኘው።

አዲሱ የፍትህ ተቋማት እየተመራ የሚገኘው ቀድሞ ባለጊዜ ከህወሃት ጋር ተባብረው ፍትህን ሲያዛቡ በነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን የአገርንና ህዝቡን ሀብትም በመዘበሩ በኩልም የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ናቸው። የዛሬው የፍትህ ተቋማት የበላይ ዘዋሪአቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ዛሬም እንደቀደመው ጊዜ የተሻለ የመንግስት ሀላፊነቶች ተሰጥቶአቸው ፍትህን በገንዘብ እየለወጡ የቅንጦት መኖሪያ ቤቶችን ከባህርማዶ እያስገዙ ይገኛሉ። እኚ ባለብዙ ስልጣን ባለጊዜ ሹመኛ፣ በካደናዳ አሜሪካ አንድ ሀብታም የተባለ የምዕራቡ አለም ሰው ሊኖርበት የሚችለውን አይነት መኖሪያ ቤቶቹ በአቶ ድንቁ ደያሳና አቶ ሳሙኤል ታፈሰ አማካኝነት እያስገዙ ይገኛሉ። በሳንሻይን

ሪልስቴት ፣ማርዮት አፓርትመንትስ ባለቤት በአቶ ሳሙኤል ታፈሰ አማካኝነት የሚከናወኑትን የመኖሪያ ቤቶች ግዢ አቶ ድንቁ ደያሳ አያውቅም። በከፍተኛ የገቢግብር ማጭበርበር ሊከሰስ የነበረው አቶ ሳሙኤል ታፈሰ እንደውለታና ግዳጅ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ለአቶ ብርሃኑ ፀጋዬና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ ኢንጂኔር ታከለ ኡማ ከአሜሪካና ካናዳ መኖሪያቤቶችን ገዝቶላቸዋል።

ዛሬ ዛሬ ዜጎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በሚያስብል ሁኔታ ከቄያቸው ሲፈናቀሉ ሲሰደዱ የታችኛው አመራር በዚህ እኩይ ተግባር በግልጽ እየተሳተፈ እሳቸው ፍትህን በማዛባት ለግላዊ ጥቅማቸው እያዋሉ ይገኛሉ። እኚ የፍትህ ተቋማት የበላይ ጠባቂ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የህግ መዕቀፍ አውጥተው ማገዝ ሲገባቸዉ ከዱባይ እስከ ዋሽንግተን ዲሲ ቅንጡ ሴቶችን ይዘው የሚመላለሱበት ምክንያት ትልቅ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ታዲያ ህዝቡ ሲጠብቅ የነበረውፍትህ እውነት እየመጣ ነውን? ቀጣይ ምርጫስ ምን ሊሆን ይችላል?ጊዜ ይመልሰው ...





### 3. አቶ ዳመላሽ ገ/ሚካኤል

አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት የአገር ውስጥ ፀጥታ ጉዳዮች ዋና ሀላፊ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እኚ የፀጥታው ዘርፍ ዘዋሪ ተወልደው ያደጉት በምዕራብ ሸዋ ዞን በኤጀሬ (አዲስ አለም) ከተማ ሲሆን ወላጅ አባታቸውና እናታቸው የተዋወቁት በራንበራስ  በቀለ ኮልቦ ቤት ነው። ወላጅ አባታቸው የበራንበራስ በቀለ ኮልቦ ገባር የነበሩ ሲሆን ወላጅ እናታቸው ደግሞ በዚው በበራንበራስ በቀለ በቤት ውስጥ ሰራተኝነት ተቀጥረው ይሰሩ በነበሩበት ወቅት አቶ ደመላሽና  ለአቶሁለት ሴት ልጆችን ወልደዋል። የዛሬው የአገራችን የፀጥታ ጉዳዮች ሀላፊ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ገ/ሚካኤል ምንም የቀዳማዊ አፄ ሀይለስላሴ ወታደር ሆነው በንጉሱ የፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ያገለገሉ ቢሆኑም ልጆቻቸውን ግን በአካባቢው ማንነት አንፀውለማሳደግ አልታደሉም። ከደርግ መንግስት ውድቀት ማግስት የህወሃት የአገሪቷን ስልጣን መቆናጠጥን ተከትለው ወደህወሃት የተጠጉት እኚ የቀድሞና የአሁኑ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ባልደረባአባታቸው በብሔርትግሬ እንደሆኑ በማመላከትነበር ሀያ ሰባት አመት በሙሉ ሲሰሩ የቆዩት። ምንም ወላጅ አባታቸው በብሔር ባይሆኑም ከህወሃት የተሻለ ስልጣንና ታማኝነትን ለመጎናፀፍ ተፀቅሞበታል።  ይህንን ተከትለው ከህወሃት የተሰጣቸው የመጀመሪያው ተልዕኮ ወደምዕራብ ኦሮሚያ አካባቢ ሄደው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሰልሉ ነበር።  አቶ ደመላሽ ወደ ምስራቅ ወለጋና ምዕራብ ወለጋ በመሄድ በዚያ ይኖሩ የነበሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ ባለሀብቶችና ምሁራንን በማሳሰርና በማስጨፍጨፍ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በማሳካታቸው ከህወሃት አመኔታን ለማትረፍ

ችለዋል። በምዕራቡ የአገራችን ክፍል ቆይታቸው በአካባቢው ነዋሪዎችላይ የፈፀሟቸው በደሎች ለቀጣዩ ጫፍ የወጣ ድፍረትና ጭካኔ መነሻ ሆኖዋቸዋል።

የኦሮሞ ወጣቶች ትግል ውስጥ ስማቸው የሚነሳ ኢንጂኔር ተስፋሁን ጨመዳ፣ አቶ ከፍያለው እና ሌሎች ብዙ የኦሮሞ ወጣቶችን ከአቶ ተስፋዬ ኡርጌ የጋር በመመሳጠር ለእስራትና ስቃይ ዳርገዋል። የዛኔ አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽነር የነበሩ ሲሆን አቶ ተስፋዬ ኡርጌ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል የደህንነት ቢሮ ኃላፊ ነበሩ። በእስር ቤት ቆይታቸው ኢንጂኔር ተስፋሁን ጨመዳ ለመናገር የሚከብድ ሰቅጣጭ የማሰቃየት ወንጀል ተፈፅሞበት በእስር እያለ ህይወቱ አልፏል። አቶ ከፍያለሁ ደግሞ ሁለት እግሮቹ በአሰቃቂ መንገድ ተቆርጦ ከእስር ከተፈታ በኋላ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ ቀርበው የደረሱበትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችንና ወንጀሎችን ሲዘረዝር ስሜታችንን መቆጣጠር የቻልነው በእምባ እየታጠብንና ሰው መሆናችንን እየጠላን ተከታትለነዋል ።

እኚ የኦሮሚያ ክልልን የፀጥታ ዘርፍ ሲመሩ የነበሩ ሁለቱ ግለሰቦች በሰላም ማስከበርና ፀጥታን ማስፈን ሽፋን መልሰው አሳድገው ያስተማራቸው ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነን ሰቅጣጭ በደል ሲፈፅሙ ይኖረዋል ። የአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤልና አቶ ተስፋዬ ኡርጌን ከስራ ያለፈ ወዳጅነት፣ የጥቅም ትስስርና "የፀጥታ ዘርፉ አደረጃጀት" በሚለው ርዕስ ስር ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ። የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ለተፈጸሙ ግድያዎች፣ አፈናዎችና ሰቆቃዎች ዋነኛ ፈጻሚ የነበረ መሆኑን የሚያምኑት ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድ በቀድሞ የፅህፈት ቤቱ ሀላፊ አቶ ጌታቸው አሰፋ ፋንታ ጀኔራል አደም





መሐመድን ዋና ዳይረክተር አድርጎ በሾሙበት ጊዜ ለፓርላማ ባደረጉት ንግግር የአገራችን መከላከያና ደህንነት ከገዥው ፓርቲ ፖለቲካ ያልተላቀቁና ወገንተኛ ሆነው ሲሰሩ እንደነበር ገልፀው ይህም አሰራር እንደሚለወጥ ቃል ገብተው ነበር። ሆኖም ግን ዶክተር አብይ አህመድ ወደጠቅላይ ሚኒስትርነት ከመጡ በኋላ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፅህፈትቤት የአገር ውስጥ ፀጥታ ጉዳዮች ሀላፊ ሆነው በእርሳቸው የተሾሙት አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ዛሬም እንደቀድሞአቸው ወጣቱን፣ ምሁሩን፣ ባለሀብቱን ከማሳደድ አልተቆጠቡም።


የመከላከያና ፌደራል ፖሊስ አባላትን መልምለውከዚያም የአነግጦር እንደሆኑ አስመስለው በምዕራብ ኦሮሚያናጉጂ አካባቢዎች በማስፈር ንፁሃንን እያስገደሉ የሰብዓዊ መብት ረገጣን እየፈፀሙ የሚገኙት እኚህ የዛሬ የአገር ውስጥ ፀጥታ ኃላፊአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ናቸው ።ይልቁኑ የጀኔራል አደም መሐመድን ስልጣን ጠቅልለው የያዙት እንዲሁም ለጄነራሉ ምንም አይነት ታዛዥነትና ከበረታን ያላሳዩ እኚ የአገርፀጥታ ጉዳዮች ፈርጥእራሳቸውን ብቸኛው የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ሹመኛ በማድረግ ስልጣናቸውን ያለአግባብ እየተጠቀሙ ያነጣጠሩባቸውን ግለሰቦች በማጥቃትና ረዣዥምና ትላልቅ የሙስና መረቦችን በመዘርጋት ላይ ተጠምደው ይገኛሉ።

ምንም ዛሬ ዛሬ በአገራችን በተለይም በመዲናችን ባልተለመደ መልኩ የተንሰራፋውን የወንጀል ድርጊት መከላከልና ማስቆም የእርሳቸው ዋነኛ የሀላፊነት ድርሻ ቢሆንም፣ የአገር ውስጥ ፀጥታ ጉዳዮች ሀላፊው አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ግን የተመደቡበትን የስራ ሀላፊነት ወደጎን በማለት ዋና ስራቸውን የቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ዝናሽ ታያቸውና አቶ አለማየሁ

ከተማን ትዕዛዞች በመፈፀምላይ አድርጓል። አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ከጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ ያገኙት ተአማኒነት፣ ለቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ዝናሽ ታያቸውያሳዩት ታዛዥነትና ከአቶ ብርሃኑ ፀጋዬና አቶ አለማየሁ ከተማ ጋር የፈጠሩት የጥቅም ትስስር ከቤተመንግሥቱ ዘዋሪዎች አንዱ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

## 4. ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የሚታወቀው በበርካታ መፅሐፍቶቹ ላይ በሚያንፀባርቃቸው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ይዘት ባላቸው ወጎቹ ነው። በመፅሐፍቶቹ ውስጥ የዘውዳዊ ዘመን አስተዳደርን በማጉላት የፌደራሊዝም ስርዓቱን አስተዳደር ደግሞ በማንኳሰስ በሰፊው ለመዳሰስ ሞክሯል። በዚም አሃዳዊ ስርዓትን ለመመለስ ከሚዳከሩ አካላት አድናቆትን ብቻ ሳይሆን ክብርና እውቅናን ለማግኘት ችለዋል።



ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ልክ ዶ/ር አብይ አህመድ ወደጠቅላይ ሚኒስቴርነት እንደመጣ30 ሚሊዮን ብር ከማህበረ ቅዱሳን ሰብስበው





በመስጠቱ ምን ያክል አቅም እንዳለውና ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኑን ለጠቅላይ ሚንስቴሩ አስመስክረዋል ። በዚም የጠቅላይ ሚኒስተሩን ትኩረት መሳብ በመቻሉ አማካሪው ሆኖ ለመመረጥ ችለዋል ። ከዶ/ር አብይ አህመድ ጋር የመጀመሪያ የውጪ ጉዞውን ወደ ሰሜን አሜሪካ ያደረገው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በዋሽንግተን ዲሲ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ከከተማዋና አካባቢዋ ነዋሪ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ያደረጉትን መድረክ ሲመራ አንገት የሚያስደፋ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። ሆኖም የዛኔ የተቃወሙት አሁን ላይ ተቀብለውታል።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ለጉብኝት ወደፈረንሳይ አገር ባመሩበት ጊዜ አንድ የግብረሰዶማዊያን ማህበር አባላቶቹ ኢትዮጵያን መጎብኘት እንደሚፈልጉ ገልፆውላቸው እርሳቸውም ፈቅደላቸዉ ነበር። ይህንን ሚስጥር የሚያውቀው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ የቅርብ ወዳጅና አማካሪ የሆነው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ብቻ ነበር፡፡ እርሱም ይህንን ሚስጥር አሳልፎ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማህበራት በመስጠቱ ማህበራቱ የግብረሰዶማዊያንን ጉዞ በመቃወም ሊያስቀሯቸው ችለዋል፡፡ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የኢትዮጵያ ታሪክን አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስተሩን እያማከሩ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ያክልም ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ አዲሱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ የኢትዮጵያ ታሪክን አስመልክቶ ጥልቅ እውቀት እንዳላቸው ሹክ ብለዋቸው ነበር፡፡

## 5. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ


ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከአዲስ አበባ ጥቂት ኪሎሜትር ርቃ በምትገኘው ቢሾፍቱ ከተማ በ1950ዓ.ም ነበር የተወለዱት። እድሜያቸውም 17 ዓመት እንደሞላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ትምህርት መከታተል ጀመሩ። በመጀመሪያ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው በወቅቱ ከነበሩ ተማሪዎች ጋር በመሆን ዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት ይከበር ሲሉ ይታገሉ ከነበሩ ወጣት የአብዮቱ የበኩር ልጆች ጋር ትግላቸውን ጀመሩ። የኢህአፓ ታጋይ ሆነው እያሉ ፓርቲውን በግልፅ ነቅፈዋል በሚል ክስ ለወራት ከታሠሩ በኋላ ወደሱዳን አመሩ፤ እዚያም ለሁለት ዓመት ያክል ቆይተው የጥገኝነት ጥያቄያቸውን ወደተቀበለችው አሜሪካ አመሩ። በ1983 ዓ.ም ኢህዴግ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ከኢህዴግ ጋር ለመስራት ተስማምተው ወደ አገር የገቡ ሰው ነበሩ። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከዩኒቨርሲቲ መምህርነታቸው በተጨማሪ በንግዱ ዘርፍ ላይ በመሰማራት የማዳበሪያ ፋብሪካ፣ ሆቴሎችና ሌሎች የንግድ ተቋማት ነበሯቸው።

በምርጫ 97 ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸው ዶ/ር ብርሃኑ ፓርቲያቸው ቅንጅት ለአንድነት እና ዲሞክራሲ ጋር ከ138 የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት መቀመጫዎች 137 ለማግኘት ችለዋል። ከዚው ምርጫ ውጤት ማግስት ዶ/ር ብርሃኑም አዲስ አበባን በከንቲባነት እንዲያስተዳድሩ በፓርቲያቸው ተሹመው ነበር። ነገር ግን የምርጫውን ውጤት አንቀበልም ማለታቸውን ተከትሎ የተነሳው ግርግር ዶ/ር ብርሃኑ ለእሥር እንዲዳረጉ ምክንያት ሆነ። ዶ/ር ብርሃኑ' የነፃነት ጎህ ሲቀድ' የተሰኘውን መፅሐፋቸውን የፃፉት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሳሉነበር፡፡ መፅሐፉ በኡጋንዳ ከተማ ካምፓላ በ1998 ዓ.ም ሊታተምችለዋል። ለ21 ወራት ያክል እሥር





ላይ ከቆዩ በኋላ በ1999 ዓ.ም ወደአሜሪካ ተመልሰዋል። አሜሪካ ሳሉም ግንቦት 7 የተሰኘ የፖለቲካ ፓርቲ አቋቁመዋል። ሚያዝያ 16/2001 ዓ.ም.፤ ኢህዴግ ግንቦት 7 መፈንቅለ መንግስተ ሊያካሂድ ቢሞክርም አክሽፌዋለሁ ሲል አስታወቀ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም 35 ሰዎች ለእስር ተዳረጉ። በዚያው ዓመት የሃገሪቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እርሳቸው በሌሉበት የሞት ብይን ወሰነባቸው፡፡ ከእርሳቸው ጋር ሌሎች 4 ግለሰቦች በሌሉበት የሞት ፍርድ የተበየነባቸው ሲሆን 33 ግለሰቦች ደግሞ የዕድሜ ልክ እሥራት ሰለባ ሆኑ።



እኚህ የአሃዳዊ ስርዓት አቀንቃኝ ሐምሌ 2007 ዓ.ም ወደ ኤርትራ በማቅናት መሬት ላይ ያሉ የፓርቲው 'የነፃነት ታጋዮችን' በይፋ ተቀላቅለዋል። ግዜው ደርሶም እኚህ ብልጣብልጥ ፖለቲከኛንጨምሮ ሌሎች የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ከዓመታት የውጭ ሃገራት ቆይታ በኋላ ጳጉሜ 4/2010 ዓ.ም ወደ ሃገር ቤት ተመልሰዋል።ዶ/ርብርሃኑነጋ ዝናን አጥብቀው ይፈልጋሉ፡፡ ዝናን ለመጎናፀፍ ደግሞ ስልጣንንመያዝ ብቸኛ መንገድ አድርገው መርጠዋል፡፡ ስልጣን አጥብቀው ፈላጊው

የኢኮኖሚክስ ምሁሩ በኢህዴግ መንግስት ሶስት በተለያዩ ጊዜ በአቋራጭ የስልጣን መያዝ ሴራን አዘጋጅተው ከሽፎባቸዋል። እነዚም የሚከተሉት ናቸው:-

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በ1993 ዓ.ም የህወሀትን መከፋፈል በሰሙ ጊዜ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር በማሰብ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (አአዩ) የተማሪዎችን ቅናቄ ከተማሪው የተነሳ በማስመሰል ከኋላ ሆኖ መርቶታል። በዚህም የአራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎ፣ ስድስት ኪሎና ኤፍቢ ካምፓስ ተማሪዎች ከተመራቂዎች ውጪ ለአንድ አንድ አመት ከትምህርት ገበታቸው ተቀጥተዋል። በአዲስ አበባም ብዙ የዝርፊያ ወንጀሎች ተፈፅመዋል። ተማሪዎቹ ግን በዶ/ር ብርሃኑ ሴራ ተነሳስተው እንደፈጸሙት ጊዜው ካለፈ በኋላ ነበር የገባቸው።

በ1997 ዓ.ምለ1997ቱ ምርጫ ቅንጅት የተባለውን ፓርቲ አቋቁመው፣ አቶ ልደቱ አያሌው እና ሌሎች አቶ በድሩ ሁሴንን የመሳሰሉ ሰዎች የአዲስ አበባን ህዝብ አሳምነው አብዛኛው ወጣት አምነዋቸው መረጧቸው። አዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ብቻ መመረጣቸው ያላረካቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ፓርላማ አንገባም በማለት ወጣቱን የልብ ልብ እንዲሰማው በማድረግ አመፅ አስነሱ። አቶ ልደቱ አያለው ለምን ወጣቱን እናስጨርሳለን ብለው ፓርላማ በመግባታቸው "ከህደቱ" ተብለው እንዲጠሉ ተዘመተባቸው። ብዙ የአዲስ አበባ ወጣትም ተገደለ ታሰረ። ህወሃትም እነ ዶ/ር ብርሃኑን አሰረ፤ ሴራውም ከሸፈ። በኃላም መንግሥትን ይቅርታ ጠይቀው ከእስር ቤት ከወጡ በኃላ የትጥቅ ትግል እንደአማራጭ በመውሰድ መታገል ጀመሩ::





ሶስተኛው በ2010/11 ዓ.ም የተፈጸመ ነዉ:: ዶ/ር አብይ አህመድ ያቀረበልንን ጥሪ ተቀብለን እንደአርበኞች ግንቦት 7 ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ መጥተናል በማለት አዲስ አባበ ገቡ። አዲስ አባበ ገብተው ሳምንት ሳይቀዩ ከኢህአፓ የቀሰሙትን የከተማ ትግል ስልት ለማፋፋም ወጣቶችን በማነሳሳት ግርግር አስነስተው የዶ/ር አብይን አቅም አዳክመው የሽግግር መንግስት በሚለው ሽፋን ስልጣንን ለመያዝ አሴሩ። ዶ/ር ብርሃኑ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ የመፈንቅለ መንግስቱ ሴራ ውስጥም በዶ/ር አብይ አህመድ ያኮረፉ የህወሃት ጀነራሎችና በአቶ ለማ መገርሳ ያኮረፉ የቀድሞ ኦህደድ አመራር አባላት እንዲሳተፉ አደረጉ። ሲጀምሩም የሸገር ወጣቶችን በገንዘብ ገዝተው የግጭቱን መነሻ የኦነግ ደጋፊዎችን ለመተናኮል አደረጉ። ቀጥለውም በቄሮና በሸገር ወጣት መካከል የተፈጠረውን ግጭት እንደከፍተት ተጠቅመው፣ የሸገር ወጣቶችን በገንዘብ ገዝተውና የጦር መሳሪያ አስታጥቀው በቡራዩ የሚኖሩ የጋሞ ህዝብ እንዲፈናቀሉ አስደረጉ። ያዘጋጁት አክቲቭስቶች በታማኝ በየነ (በገንዘብ አሰባሳቢነቱ የተመረጠ) ፊት አውራሪነትና በቴዲ አፍሮ (በጉራጌነቱ የተመረጠ) አጫፋሪነት እንዲሁም በኢሳት ሚዲያም (በጸረ-ፌድራልዝምነቱ ተመረጠ) እንድያራግብላቸው አስደረጉ። በአዲስ አበባ ጎዳናዎችም የዶ/ር አብይን መንግስት የሚቃወም ትልቅ ሰልፍ ተካሄደ።

በባሌም በቦሌም ስልጣን ለማኝ ባዩ ዶ/ር ብርሃኑ ባልታወቀና ለጊዜው ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ተከርብተው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ደጋፊ በመሆን እንደውሃ ቀጂ ቤተ መንግስት መመላለስ ጀመሩ:: ሳይቆዩም ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሚያቀነቅኑትን የዜግነት ፓለቲካ ለማራመድ ይረዳ በሚመስል


መልኩ ኢዜማ (ኢትዮጵያዊ ዜግነት ለማህበር ፍትህ ) የሚል ካርድ ይዘው ብቅ አሉ:: በዚህ ካርድ ስድስት የሚሆኑ ጸረ ብሔር ፌዴራልዝም ፓሪቲዎችን አሰባሰቡ:: አቶ ልደቱ አያሌውን በካልቾ ብለው ከፓርቲያቸው ትግል ሜዳ አሳልፈው ከአጥር ውጪ አሽቀንጥው ጣሉዋቸው:: ዛሬ ዛሬ በስውር የጠቅላይ ሚኒስቴሩ አማካሪና የቤተ-መንግሥቱ ዘዋሪዎች ተርታ ውስጥ ለመግባት አንድ እግር አስገብተዋል:: ኢዜማ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሚመኙትን ሀገራዊ ፓርቲ ይተካ ይሁን? ምኞት ሆኖ ሊቀር ይችል ይሆን? ዶ/ር ብርሃኑም ሽር ጉዱን ቀጥለዋል:: ሌላው መታወቅ ያለበት ሀቅ በቅርቡ በተቃዋሚነታቸው የሚታወቁትን የኢሳት ጋዜጠኞች ከጠቅላይ ሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ወስደው ያስባረሯቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መሆናቸው ነው። በመንግስት ገንዘብ አፓርታማ ተከራይቶላቸው በየቲቪው እየዞሩ ጠቅላይ ሚኒስቴሩን እያሞካሹ የሚውሉት እነ ጋዜጠኛ ሲሳይ አገና ለምን ከኢሳት እንዳልተባረሩ ማስረዳት አያስፈልገውም።

## 6. አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ

ጎንደር ተወልደው አዲስ አበባ ያደጉት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ረዥም እድሜያቸውን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በመሳተፍ አሳልፈዋል። በዜግነት እንግሊዛዊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ አንድ ጊዜ የገዢው መንግስት ባለስልጣን በመሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ የመንግስት ተቃዋሚ ፓርቲን በመምራት ከአገራችን ኢትዮጵያ ጠለቅ ያለ ልምድን ሊቀስሙ ችለዋል።







አቶ አንዳርጋቸው ረዘም ላለ ጊዜ የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ውስጥ አንዱ በመሆን በተለያዩ የአመራር ቦታዎች ላይ ተመድበው አገልግሏል። ከዚያም ከኢህአዴግ ጋር ባለመስማማታቸው ወደእንግሊዝ አገር በመሄድ የፖለቲካ ጥገኝነትን ጠይቀው ከዚያም የአገሩ ዜግነት ተሰጥቶአቸው እዚያው መኖር ጀመሩ። ከዚያም አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የአርበኞች ግንባር የተባለን ታጣቂ ቡድን ተቀላቅለዋል።

አቶ አንዳርጋቸው እንግሊዝ አገር ሆኖ ግንባሩን እየመሩ ባሉበት ግዜ በኤርትራ የሚገኙትን የአርበኞች ግምቦት 7ን አባላት ለማነጋገር ወደዛው እያመሩ እያሉ በየመን አገር መንግስት በሰነዓ አየር ማረፊያ ተይዘው ለኢትዮጵያ መንግስት ተላልፈው የተሰጡት። በየመን መንግስት አማካኝነት ተላልፈው ለኢትዮጵያ መንግስት ከተሰጡ በኃላ በአገር ክህደት ወንጀል

ክስ ተመስርቶባቸውና የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ለጥዊት አመታት የእስራት ጊዜን ያሳለፉት። በእስር ላይ እያሉም በኢህአደግ ውስጥ የፖለቲካ ሽግሽግ መከናወኑንና ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ወደጠቅላይ ሚኒስተርነት ስልጣን መምጣታቸውን ተከትለው በነፃ ሊለቀቁ ተችለዋል። ከእስር ከተፈቱም በኃላ አራት ኪሎ ቤተመንግስት መመላለስ ያዘወተሩት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ የቀድሞ ፓርቲያቸው በመከሰሙና የዜግነት ጉዳያቸው ምርጫን ከመወዳደር ስለሚያግዳቸው ቀጥተኛ የመንግስት ተቃማዊ ወይም ደጋፊ ፖለቲከኛ ከመሆን እራሳቸውን አገለሉ። ነገር ግን የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ የፖለቲካ አማካሪ ለመሆን የበቁት አቶ አንዳርጋቸው ካሳለፏቸው የፖለቲካ ህይወት ጊዜያቸው በተለየ መልኩ አሁን ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸውን በማጎልበት የቤተመንግሥቱ ዘዋሪ ለመሆን ችለዋል። በአሁኑ ጊዜ ህገመንግሥቱ ተቀይረውና የብሔር ፌደራሊዝሙ ፈርሶ አሃዳዊ ስርዓት በሚመሰረትበት ዙሪያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድን እያማከሩና ጫና እያሳደረባቸው ከሚገኙ የቤተመንግሥቱ ዘዋሪዎች ውስጥ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቅርብ ወዳጅ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ይገኛሉ።

አርቲስት ደበበ ሰይፉና ዶክተር ዳኛቸው አሰፋም ቤተመንግሥት ከሚመላለሱት ውስጥ በመሆናቸው መጪው ምርጫ ከተከናወነ ለኢህአዴግ የምርጫ ቅስቀሳ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በኢትዮጵያ ታሪክ ዙሪያ ጥልቅ ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የአገራችን ታሪኮችን አስመልከተው ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድን እያማከሯቸው ይገኛሉ ።





ከላይ ስማቸው የተጠቀሰና ሌሎች የአራት ኪሎው ቤተመንግሥት (እነሱ የሚኒሊክ ቤተመንግሥት ይላሉ) ዘዋሪዎች አንድ የሚስማሙበት ፍላጎት አላቸው። እሱም አሁን ያለውን የፌደራሊዝም ስርዓት ወደ መልካምድርን ያገናዘበ የአስተዳደሮች ከለላና ፕሬዝዳንሻል ስርዓት መቀየር ነው። የሙስና መረባቸዉን ከመዘርጋት በተጨማሪይህንን ይፈፅም ዘንድም ቀን ለሊት ሳይሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እየጎተጎቱ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ቀድሞውኑ ይህ ፍላጎታቸው ስለሆነ ጉትጎታ ላንል እንችላለን። ይልቁንስ እንዴት ህገመንግስቱ ተቀይሮ እነሱ የሚፈልጉት አገር እውን የማትሆንበት ላይ በጋራ እየመከሩ ይገኛሉ።

## የአቶ አባዱላ ገመዳ ገባ ወጣ ፖለቲካ

ባሌ አካባቢ ተወልደው ያደጉት አቶ አባዱላ ገመዳ ገና በወጣትነት እድሜያቸው የደርግ የጦር ሠራዊትን የተቀላቀሉ ይሆን እንጂ ወደመጨረሻ በህወሃትና የደርግ ጦር መካከል ሲደረግ የነበረ ውጊያ ላይ ሊማረኩ ችለዋል። በመቀጠልም አብዛኛው የአገራችን ህዝቦች ተደራጅተው የፖለቲካ ፓርቲና ድርጅት በማቋቋም አምባገነኑን የደርግ መንግስት ከላያቸው ላይ አሽቀንጥረው ለመጣል ሲዋጉት በነበረበት ዘመን፣ ምርኮኛ ሆነው በሰሜናዊ የአገራችን ክፍል ትግራይ ከህወሃት ጋር የተዋወቁት እኚ የቀድሞ የደርግ ሰራዊት የኦሮሞን ህዝብ መልሰው እንዲወጉ ሲባል ከሌሎች ምርኮኞች ጋር ኦህድድን እንዲመሰርቱ ተደርገዋል።

አቶ አባዱላ ገመዳ በሀረርጌ በደኖ በሚባል ስፍራ የኦነግ ጦር የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ የዘር ጭፍጨፋ ወንጀል አካሂደዋል በማለት ዶክመንተሪ ፊልም ያዘጋጀ ሴረኛ የህወሃት ምልምል ነው። የኦነግ ጦር የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ የዘር ጭፍጨፋ እንዳካሄደ ተደርጎ በአቶ አባዱላ የስክሪፕት ፀሃፊነትና ዳይሬክተርነት የተሰራው ዶክመንተሪ ፊልም አላማው ሁለት ነበር፦ አንደኛው በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከኦህደድ ይልቅ የህዝብ ተወዳጅነት የነበረውን ኦነግን ለመወንጀልና ስሙን ጥላሸት ለመቀባት ታስቦ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በዚህ በተቀነባበረ ቁርሾ ምክያት የኦሮሞና አማራ ህዝቦች ተባብረው በአንድነት በመታገል ለህወሃት ስልጣን አደጋ እንዳይሆኑ በማሰብ ነው።

አቶ አባዱላ በዚህ ዶኩመንተሪ ፊልም ተጠቅሞ የኦህደድ ካድሬዎችን ሲያሰለጥንበት ነበር ፣ የመንግስት ሠራተኞችም በግድ ዶኩመንተሪውን





ገዝቶት እንዲያዩ ተደርገዋል። አቶ አባዱላ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ዶኩመንተሪ ፊልም ኦነግ በአርባጉጉ አማራን ጨርሰዋል ብሎ አቀናብረዋል። በተጨማሪም ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች የኦሮሞ ህዝብ ላይ እንዲቀናጁ ለማነሳሳትና ለማስቻል አስቦ ነበር።

የአገር መከላከያ ውስጥ እያለ ለህወሃት ጥቅም ሲል ለፈፀማቸው እነዚህና በርካታ የተንኮል ድርጊቶቹና ባሳየው ታማኝነቱ ተራ የደርግ ወታደር የነበረ ምርኮኛ በጥቂት ግዜ ውስጥ የሜጀር ጀነራልነት ማዕረግን ለመጎናፀፍ ችለዋል።

አቶ አባዱላ ገመዳ ከአገር መከላከያ ሰራዊት አመራርነቱ የኦህደድ ሊቀመንበርና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሆኖ በሰራበት አመታት ሙሉበሙሉ በእናትም በአባትም ኦሮሞ የሆኑትን ካድሬዎች በኦነግ አሳበው እንዲባረሩ አድርጓል። በምትካቸውም ከዚህ በተቃራኒ የኦሮሞ ህዝብ ፍላጎት ደንታ የማይሰጣቸውንና በደም ኦሮሞ ያልሆኑ ነገር ግን አፋን ኦሮሞን በሚችሉ ግለሰቦች ተክቶአቸዋል። በአቶ አባዱላ የኦህደድ ሊቀመንበርነትና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት ዘመን የኦህደድ ካድሬ ሆኖ ለማገልገልም ሆነ ለመሾም በደም ሙሉበሙሉ ኦሮሞ አለመሆንና ብሔርተኛ (nationalist) አለመሆን ዋነኛው መስፈርቶች ነበሩ። በነዚህ መስፈርቶቹ የዛኔ የመለመላቸው ወጣቶችም አሁን ተመሳሳይ ሁኔታ በመፈጠሩ የኦህደድ/ ኦዲፒን ስራአስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ እያጥለቀለቁ ይገኛሉ። ዛሬም እንደትላንቱ የአቶ አባዱላ የኦህደድ ሊቀመንበርነት ዘመን በዶ/ር አብይ አህመድ ዘመንም በደም በሁለቱም በእናታቸውና በአባታቸው በኩል ኦሮሞ የሆኑና ብሔርተኛ ናቸው ተብለው

የታመነባቸው የአህደድ/ ኦዲፒ ከፍተኛ አመራር ከሀላፊነት ቦታቸው እየተገፈተሩ ይገኛሉ።

አቶ አባዱላ ገመዳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሆነው የኦሮሞን ህዝብ ለመምራት በመጣበት ጊዜ፣ 'ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ለመታረቅና ሊክሰው ነው የመጣሁት' በማለትበጥርሱ እየሳቀ የኦሮሞን ፖለቲካ የሚያሻግር መስሎ የኦሮሞን ማንነት የማዳከም ስራ ሰርቷል። ይህ የህወሃት ስራአስፈፃሚ የነበረ አስመሳይ ህወሃቶችና አህደዶች ዘንድ የሚታወቀው "ለኦሮሞ ህዝብ ልማት እንጂ ማንነት አያስፈልገውም" በሚለው መሪውና አቋሙ ነው ። በልማት ስምም እስካሁን የህዝብና መንግስትን ሀብት እየመዘበረ የሚገኝ አንድ ትልቅ የሙስና መረብ ለመዘርጋት ችለዋል።

ከአንድ አመት በፊት ቲም ለማ የህወሃትን አምባገነናዊ ስርዓት ለመገርሰስ ወደስራ በገባበት ጊዜ አቶ አባዱላ ገመዳ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አፈጉባዔ ነበር። ከዚያም ባልተጠበቀ መልኩ የነበረበትን የሀላፊነት ቦታ ለቀው ወደኦሮሚያ ክልል ለመሄድ ሲባል የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገብተው ነበረ። ቀጥለውም ወደኦሮሚያ ክልል መሄዱን ለምን እንደፈለገ ተጠይቀው፣ "ህዝቤ ተፈናቅሎ እያለ ፌደራል ላይ ምን እሰራለሁ፣ በዚህ ፈታኝ ወቅት ወደክልል ሄጄ ህዝቤን ማገልገል ስለሚፈልግ ነው" በማለት ሚዛን የማያነሳ ምላሽ እንደሰጠ ሁላችንም የምናስታውሰው ጉዳይ ነው። የመጀመርያው አላማ የነበረው ህወሃትን አኩርፎ የመጣ በማስመሰል ኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ነው።

አቶ አባዱላ ገመዳ በለውጡ ሂደት ውስጥ ቲም ለማን የሚያግዝ መስለው ነበር የቲሙን አባላቶች የተቀላቀለው። ሆኖም ግን ሽፋኑ ሲገለጥ ተልዕኮው ሌላ ነበር። የአቶ አባዱላ ዋነኛ አላማየነበረው ቲም ለማ ውስጥ ገብተው





በማዳከም አፍርሰዋቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆን ነው። ይህንን አስቀድሞ ከህወሃት ጋር የተወያየው አቶ አባዱላ ገመዳ፣ ተልኮውን ካሳካው ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ እንደሚሾም ከህወሃት ቃል ተገብቶለት ነበር። እድሉን ለማስፋት ሲልም ከህወሃት ጋር የተጣላ አስመስለው ነበር የኦሮሞን ህዝብ ለመቅረብ የሞከረው። በመጨረሻ ግን የህወሃት የተቀበለውን ተልዕኮና ጠቅላይ ሚኒስቴር የመሆን ህልሙ በቲም ለማ ጥንካሬ ተጨናግፎበታል።

አቶ አባዱላገመዳ ለኦሮሞ ህዝብ ትግልና ፖለቲካ ትልቅ ጥላቻና ንቀት እንዳለው ብዙ ግዜ አሳይቶናል። በቅርቡ ከአንድ ወር በፊት በጅማና አዳማ ከተማ ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ዞኖችና የከተማ አስተዳደሮች ለተወጣጡ የአህደድ/ ኦዲፒ ካድሬዎች ከአቶ ሌንጮ ለታና አቶ ሌንጮ ባቲ ጋር በመሆን ስልጠና ሲሰጡ በነበረበት ጊዜ ካድሬዎቹ ከአህደድ ይልቅ ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ማንነት ጉዳይ ዙሪያ ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክተዋል የሚል ሀሳብ አስነስተው፣ በዚህ የተበሳጨው አቶ አባዱላ ገመዳ ሁለቱን ሌንጮዎች ከጎኑ አስቀምጠው "እኛ እንደኦነግ በኤርትራ ስንዱ ሞቃዲሾ ውስጥ አልተመሰረትንም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ የኦሮሞን ህዝብ የማንነት ትግል ታሪክ ማጠልሸት ነው።

አቶ አባዱላ ባለፉት 27 አመታት የደረሱትን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣና የግድያ ወንጀሎች የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዘናዊ የሚያውቀውንያክል ያውቃል። የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴርመለስ ዘናዊ ከሁሉም ከአህደድ አመራሮች አስበልጠው የሚያምነው አቶ አባዱላን ብቻ ነበር። የአቶ ደራራ ከፈኒና የእውቁ የኦሮሞ ታጋይና አርቲስት ኤቢሳ አዱኛ ግድያንኦፐሬሽን የመራው አቶ አባዱላ ገመዳ ነው። የቀድሞ የአህደድ

ታጋዮችን እነ አቶ ሀሰን አሊና ወይዘሮ አልማዝ መኮን ያስባረራቸው እራሱ አቶ አባዱላ ገመዳ ነው። አነግን የማፅዳት ዘመቻ በሚል ሽፋን በወለጋ ሀረርጌ አምቦ ጅማና በሌሎች የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች በርካታ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑትን ግለሰቦች ከነጋዴው ከምሁሩ ከአርሶአደሩ አስገድለዋል። በአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በአመራርነት በሰራበት ጊዜም በኦነግና ትምክህት ስም ኦሮሞና አማራ የሆኑ የሠራዊቱ አባላት ላይ በደል ፈፅመዋል። እንግዲህ አቶ አባዱላ ለዚ ሁሉ ወንጀሎቹ እንደነ አቶ በረከት ስምኦን ተጠያቂ ሆኖ ዘብጥያ መውረድ ሲገባው በፍቼ ከተማ የተገነባው የጀግናው ጀኔራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሀውልት ምርቃት ላይ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ጀግና ተብሎ ተወድሰዋል። የኦሮሚያ ልማት ማህበርን በቦርድ ሰብሳቢነት እየመራ የሚገኘው እኚ ፀረኦሮሞ ትግል የሆኑት ዛሬም የህዝብ ገንዘብን በልማት ስም መዘበሩን ቀጥሎበታል።

ህዝቦቻችን የወያኔን ዘረፋና አፋኝ ስርዓት ለአንዴና መጨረሻ ጊዜ ከላዩ ላይ አሽቀንጥረው ለመጣል ሲሉ በአንድነት መንፈስ ተነስተው እልህ አስጨራሽ ትግል ሲያደርጉ በነበሩበት ጊዜ፣ ይህ ሴረኛ ፖለቲከኛ ህወሃትን የሚፈይድና የህዝቡን ትግል ወደኃላ የሚመልስ አንድ ዘዴ ዘይደው ነበር። እሱም በትግሉ ውስጥ የኦረሞ ወጣቶችን ትግል በባህር ማዶ ሆነው የሚመሩት አክቲቬስቶች ያሉበት ድረስ ሄደው ማግኘትና በገንዘብ ሀይል ማስማማት ነው። በእቅዱም መሰረት ከሶስት አመታት በፊት ጃዋር ሞሐመድ የቄሮን ትግል በዋናነት ሲያስተባብርና ሲመራ በነበረበት ጊዜ ሚኒሶታ ድረስ ሄደው ካነጋገረውና የውሽቱን እናበረታታለን እያለ መረጃ ከወወሰደበት በኃላ የህዝቡን ትግል ለማጨናገፍ ሲል ወደአገር ተመልሶ





ከእሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች ሲያሳስርና ሲያስገድል ነበር። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ጀዋር ሞሐመድን በወጥመዱ ውስጥ ማስገባት የጀመረው እድሜ ጠገቡ የኦሮሞ ህዝብ ጨፍጫፊ ፖለቲከኛ፣ ከወራት በፊት ዳግምወጣቱን ተፅዕኖ ፈጣሪ ለማንበርከክ ሲል፣ ሆንግኮንግ ድረስ ተከትለውት በመሄድ ባዘጋጀለት የጋብቻትስስርና ዝምድናጉዳይ ዙሪያ ሊያግባባው ሞክረዋል። ሰውዬው የኦሮሞን ህዝብ ትግልና ማንነት ወደኋላ ለመመለስ ሲባል የማይፈነቅለው ድንጋይ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም ።

በሪፎርሙ ማግስት አቶ አባዱላ ገመዳና ልዩ ወዳጃቸው ወይዘሮ አስቴር ማሞ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ አማካኝነት ወደኦህደድ/ ኦዴፓ አመራርነት ቦታዎች እንደተመለሱ ሁሉ የኦሮሞ ወጣት የአዲስ አበባ ማስቴር ፕላንን ከጫፍ ጫፍ በአንድነት ተነስተው ሲቃወሙ በነበሩበት ጊዜ ለፖሊስና መከላያ ሰራዊት ትዕዛዝ ሰጥተው ያስጨፈጨፏቸው የቀድሞ የኦህደድ ፅህፈት ቤት ሃላፊ አቶ በከር ሻሌና አንጃዎቹ ሹመቶች እየተዘጋጁላቸው ይገኛል።

አቶ አባዱላገመዳ ዛሬ ላይ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ አማካኝነት የኦሮሚያ ክልል ም/ፕሬዝዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ልዩ አማካሪ ሆኖ ተመድበዋል። ሹም ሽሩ እየተካሄደ ያለው በሱ ፍላጎትና ትዕዛዝ መሰረት ነው። በዚም ሹም ሽር የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት እያለ በዘረጋው የቀድሞ የካድሬዎች የሙስና መረብ ላይ መልሰው ነብስ እየዘራበት ይገኛል። አቶ አባዱላ ገመዳ ግምቦት 8 2010 ዓ.ም በጅማ ከተማ በተካሄደው ፱ኛው የኦዴፓ ጉባዔ ላይ ከሌሎች የትግል አጋሮቹ ጋር በክብር ከተሸኘ በኃላ ተመልሰው መጥተው ዳግም ኦሮሚያን በእጃዙር እያስተዳደረ ይገኛል።

## የፀጥታ መዋቅሩ አደረጃጀት

የአገሮች ፀጥታና ሰላምን የማስከበር ጥንካሬ የሚለካው እውቀትና ክህሎትን መሰረት ባደረገ የፀጥታው ዘርፍ አደረጃጀት ጥንካሬዎቻቸው ነው። የመንግስት ፀጥታ ዘርፍ የሚደራጅበት ራሱን የቻለ ሳይንስ አለው። የአንድ አገር የፀጥታው ዘርፍ አደረጃጀት ለሉዓላዊነቷና ደህንነቷ ብሎም ለእድገቷ ጉልህ ሚናን ይጫወታል። የሳለምና ፀጥታ (peace and security) ዘርፍ ተመራማሪዎች የአገሮች የሰላምና ፀጥታ መዋቅሮች ከፖለቲካ ጥገኝነትና ከጥቅም ትስስር በፀዳ መልኩ ገለልተኛ ሆኖ መደራጀት እንዳለበት ይመከራሉ። አክሎም ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ከጥቅም ትስስር ያልፀዳ የፀጥታ ዘርፍ አደረጃጀት የፖለቲከኞችና ወንጀለኞች መጠቀሚያ በመሆን አገርን አደጋ ላይ ሊጥል እንደምችል በመግለፅ ሌሎች ተጨማሪ ተያያዥ ጉዳዮቹንም ያብራራሉ። የፀጥታው ዘርፍ ሲባል በተለያየ ደረጃ ያሉትን የመከላከያ፣ ፖሊስ፣ የመረጃና ደህንነት ተቋማትንና ሌሎች ተመሳሳይ ተልዕኮ ያላቸውንም ተቋማት ያካትታል። በኛም አገር የኢፌድሪ መከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልሎች የፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የክልሎች የፀጥታ ዘርፍ ቢሮዎች፣ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ተቋማት በፀጥታ ዘርፉ ስር ይጠቃለላሉ።

ከአንድ አመት በፊት እንደዛሬው ህወሃት ተገፍታ ሳትሸሸግ በፊት የነበረውን የመንግስት የፀጥታ አወቃቀርና መረብ ሁላችንም የምናውቀው ገሃድ ነው።





የዛኔው የነበረው የፀጥታ አደራጃጀትና መዋቅር ለኢህአዴግ ፖለቲካና ለኢህአዴግ ባለስልጣናት የጥቅም ማሚያ በሚመች መልኩ ከመሰራቱም በላይ የፖለቲካና የጥቅም ወገንተኝነቱ የህወሃትንና የህወሃት ባለስልጣናትን ፍላጎት የሚያስቀድም ነበር። ከጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በፊት የነበረው የፀጥታ ዘርፍ በህወሃት የበላይነት ከመምራቱ በተጨማሪ እያንዳንዱ የፀጥታ ዘርፉ እንቅስቃሴ የህወሃት የፖለቲካና ጥቅም ፍላጎት በሚያስከብር መልኩ እየሰራ ለመሆኑ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። ይህ ከአንድ አመት በፊት የነበረው የፀጥታ ዘርፍ የስንቱን የአገር ተስፋ ወጣት ህይወት እንደቀጠፈ፣ የስንቱን ዜጎች እድሜና አካል እንዳጎደለ፣ ስንቱን ምስኪን እናቶችና አባቶችን እንዳስለቀሰና የስንቱን ለፍተው አዳሪ ንብረት እንደቀማ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ምስክር ነው። የእስር ቤቱ ወይም ተገራፊዎች ቋንቋ አፋን ኦሮሞ የነበረው በህወሃት ፀጥታ ዘርፍ አመራር ጊዜ ነው። የሰላምና ፀጥታ ዘርፉ ንፁሃን ዜጎች ላይ በደል ሲፈፅም የነበረው መከላከያ ሰራዊቱን፣ አቃቤ ህጉን፣ ፍርድ ቤቶቹን፣ የፌደራል ፖሊሱን፣ የክልል ፖሊሶችንና የመረጃና ደህንነት ፅህፈቱን ጨምሮ በቅንጅት ነው። እነዚ የሰላምና ፀጥታ አካላት ስራቸውን ሲያከናውኑ የነበሩት በቅንጅት ነው። እራሳቸው የሰላምና ፀጥታ አስከባሪ ሆኖ እያሉ ንፁሃን ዜጎች ላይ ወንጀል ሲፈፅሙ የነበሩትም በጥምረት ነው። ሲገድሉ፣ ሲገርፉ፣ ሲደፍሩ፣ ሲዘርፉና ሲፈርዱ የነበሩት በቅንጅት ነው። በቂሊንጦ፣ በቃሊት፣ በማዕከላዊ በዝዋይና በድብቅ እስርቤቶች የመቶ ሺዎችን አካልና ነብስ በጭካኔና በአረመኔያዊ መልኩ ሲያስጨንቁ የነበሩት እነዚው የመንግስት የፀጥታ አካላት ናቸው። በተከበረ የህይማኖት ቦታ ዘልቀው ገብተው መስጊድ ውስጥ በምዕመናኑ ላይ ቦምብ ሲያፈነዱ

የነበሩት እነዚው የፀጥታ አካላት ነበሩ።የተከበሩ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት አባቶችን አፍኖ በየእስርቤቱ ሲያማቅቁ የነበሩት እራሳቸው ናቸው። የዋቄፋናና ፕሮቴስታንት ሀይማኖት መሪዎችና አባላትን እነግ ናችሁ እያሉ ሰላም ነስቷቸው ሲያስጨንቋቸው የነበሩት እነዚው ከተለያዩ የፀጥታ ዘርፉ አካላት የተወጣጡ ነብሰ በላዎች ነበሩ። ስንቱ ጭራቅነታቸው ተዘርዝረው ይቻላል።

እዚህ ጋር መታወቅ ያለበት ምንም እነዚህን በጭካኔ የተሞላ አረመኔያዊ ድርጊቶችን በበላይነት ሲመራ የነበረው ህወሃት ቢሆንም ጀሌዎቹ ፈፃሚዎች ግን ከኦህደድ፣ ብአዴን፣ ደህዴንና ከሌሎች የተለያየ የማህበረሰቡ ክፍል የተወጣጡ ነገር ግን እርስበርሳቸው በጥቅም የተሳሰሩ ግለሰቦች ነበሩ። ህወሃት ኦሮሞን በኦሮሞ፣ አማራን በአማራ፣ ሶማሌን በሶማሌ ሲያስገድል ነውየኖረው። ለምሳሌ ተወዳጁን የአምቦ ፈርጥ የድምጻዊት አበበች ደራራን አባት አቶ ደራራ ከፈኒንና ተወዳጁ ድምፃዊ ኤቢሣ አዱኛ እንዲገደሉ ውሳኔ ያስተላለፈባቸው አቶ አባዱላ ገመዳ ነበር። የሰብአዊ መብት ተሟጋች የነበረው የአሁኑ የሶማሌ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ሙስጠፋ ወንድሙ የተገደለበትና እህቶቹ የተደፈሩት በቀድሞ የሶማሌ ክልል ፕረዝዳንት በአቶ መሐመድ ኡመር (አብዲ ኢሌ)ነበር።

አሁንስ?ዋናው ትኩረቴ አሁን ያለው የመንግስት የፀጥታ ሀይል አደረጃጀት፣ መዋቅርና መረብ ምን ይመስላል የሚለውን መግለፅ ነው። ከአንድ አመት በፊት ኦህደድና ብአደን Team Lemmaና ኦሮማራ በሚለው ጥምረት የፖለቲካ ጨዋታ ፍልስፍና ህወሃትን ገፍተው ዶ/ርአብይ አህመድን





ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ካበቁ በኋላ የቀድሞው ተወግደው አዲስ የፀጥታ ሀይል እንደተደራጀ ህዝቡ ይረዳል። ስህተቱ እዚጋ ጋር ነው።

በቀድመው ከላይ የጠቀስኳቸውንና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ወንጀሎች ሲፈፅሙ የነበሩ የፀጥታ ሀይል አባላት አልተወገዱም። ስለዚህ የዶ/ር አብይ አህመድ መንገስት የፀጥታው ዘርፍ አዲስ ነው ማለት ፈፅሞ አይቻልም። አንዳንዶቹ ብቻ ሲታሰሩ ታዝበናል።

ጥያቄው ጥቂቶቹ ብቻ ለምንና እንዴት ተለይተው ታሰሩ ነው? በፊትም ከታሰሩት የፀጥታው ዘርፍ አባላት ጋር ሲያቦኩ የነበሩትስ እንዴት ተሾሙ? መልሱ ቀላል ነው። አሁን በዋናነት በዶ/ር አብይ አህመድ የተሾሙ አካላት ቀድሞ ህወሃት እንደተዳከመችና እንደማትመለስ አውቆ ሌሎቹን በማጋለጥ ከሰውዬው ጎን የተሰለፉ ናቸው። እነ አቶ ተሰፋዬ ኡርጌን (ለጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ድጋፍ ለመስጠት በመስቀል አደባባይ በተጠራው ሰልፍ ላይ የሰኔ 16ቱን የቦምብ ፍንዳታ በዋናነት ያቀነባረና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጽሕፈት ቤት የፀረሽብር ዳይሬክቶሪት የነበረው) እና አቶ ያሬድዘሪሁን (የፌደራል ፖሊስ ኮሚሺን ኮሚሺነርና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጽሕፈት ቤት ምክትል ዳይረክተር የነበረው)ን ቀድሞ ያጋለጡ እራሳቸው አብሮአቸው ሲገድሉ ሲያስሩ የነበሩ የእነሱ የስራ ባልደረቦችና የቅርብ ወዳጆቻቸው ጭምር የነበሩት ናቸው።

አሁን በዋናነት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤትን የሚመሩት ሰው አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ይባላሉ። ጀነራል አደም መሀመድ ለስም ነው የተቀመጡት። አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ምክትል ዳይሬክተርና የአገር ውስጥ የደህንነት ጉዳዮች ሀላፊ ናቸው።

አቶ ደመላሽ እራሳቸውን ለሹመት ያበቁት የባንዳነት ቤት ጎደኞቻቸውን አሳልፎ በመስጠት ነው። አቶ ደመላሽ፣ አቶ ተስፋዬ ኡርጌና አቶ ያሬድ ዘሪሁን ከጓደኝነት አልፎ በጥቅም የተሳሰሩ ወዳጆች ነበሩ። እርስበርስ ምስጥርቻቸውን ይተዋወቃሉ ። አንዱ ስልጠኑን ተጠቅሞ የዘረፈውን ሀብት ዬት እንዳስቀመጠ ሌላው ያውቃል። በጋራም ዘርፈው ሲከፋፈሉ ኖኖረዋል።

አቶ ተስፋዬ ኡርጌና አቶ ያሬድ ዘሪሁን ሲያገቡ ለሁለታቸውም አንደኛ ሚዜ ሆኖ የዳራቸው የአሁኑ የአገሪቷ የፀጥታው ዘርፍ ፈርጥ አቶ ደመላሽ ገ/ሚካአል ነበር። አሁን ላይ ግን እነሱ ታሳሪ ሆኖ እሱ ደግሞ በአሳሪነቱ ቀጥሏል።

ይህ የአሁኑ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ከህወሃቱ ዘመን ተቋም ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማሳያ ነው። ከኋላ የነበሩ አሳሪዎች ወደፊት መጡ እንጂ አንድም አዲስ ሰው በተቋሙ የለም። አሁን ወደፊት የመጡት የቀድሞና የአሁኑ ገራፊዎች የፖለቲካ ታማኝነትና አገልጋይነትን ያስጠብቁልኛል ተብለው በጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብይ አህመድ ስለታመነባቸው ብቻ ነው። የአሁኑ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ከቀድሞው በህወሃት ከሚመራው ተቋም ጋር በሁሉም ነገር ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ የኡሁኑን በበላይነት የሚያዘው አህደድ መሆኑ ነው። አህደድ ለማለትም አያስደፍርም፤ በጠቅላይ ሚኒስተሩ የሚመራ ማለት ትክክለኛ ገለፃ ይሆናል።

አጠቃላይ ጠቅላይ ሚኒሰቴር ዶ/ር አብይ አህመድ የፀጥታው ዘርፍን አደረጃጀት በብቸኝነት መርተዋል። የአሁን የፀጥታው ዘርፍ አደረጃጀት ከህወሃት አደረጃጀት ለየት የሚያደርገው ነገር አንዱ የአሁኑ እንደህወሃት





ዘመን በፓርቲ ሳይሆን እንደዘውዳዊው ዘመን በአንድ ግለሰብ ማለትም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ሀይል ብቻ መደራጀቱ ነው። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይህንን የፀጥታ ዘርፍ እራሳቸው እንደግለሰብ በራሳቸው ፍላጎት ሲያደራጁ ሊያራምዱ የሚፈልጉትውን ስውር የፖለቲካ ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው። ይህ ስውር የፖለቲካ ፍላጎታቸውም የሚመነጨው ከሚያምኑበትና ከሚያራምዱት የዳግማዊ አፄ ሚኒልክ የፖለቲካ አካሄድ ነው።

ከአንድ አመት ወዲህ በፀጥታ ዘርፉ አካባቢ የተመደቡ ባለጊዜዎች የተሾሙት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ተካሂደው በብቃታቸው መሰረት ሳይሆን ከአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ጋር ባላቸው የጥቅም ትስስር ተመርጠው ነው። ለምሳሌም የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር፣ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር እና የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ኃላፊ በነዚህ የህላፊነት ቦታዎች ላይ የተሾሙት በብቃታቸው ከሌሎቹ ባልደረቦቻቸው ሊቀው ሳይሆን ለአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ባሳዩት የተላላኪነት ልምዳቸው በመመረጣአው ምክንያት ነው።

የፀጥታ ዘርፉ አደረጃጀት ደካማ መሆኑ ገና የታየው ሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ድጋፍ ለማድረግ ሰልፉ የወጡ ንፁሃን ላይ በቀላሉ ቦምብ የተወረወረ ቀን ነው። ፀጥታን ማስከበር ቀዳሚ ስራው መሆኑን የተገነዘበ መንግስት እንኳን ሊደግፈው ሰልፍ የወጣን ህዝብ ቀርተው ሊቃወመው የወጣን ህዝብ ራሱ ከአደጋ የመጠበቁን ኃላፊነት ይወስዳል።

የአገርን ደህንነት የሚያስጠብቅ የፀጥታ አካል ቢኖር ኖሮ በግማሽ ቀን የአገሪቷ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሆኑት የአማራ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት ዶ/ር አምባቸው መኮንን፣ የአማራ ክልል የፖለቲካ አደረጃጀት ኃላፊ አቶ እዘዝ ዋሴ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አጠቃላይ የኤታማዦር ሹም ጀኔራል ሰዓረ መኮንን እና ሜጀር ጀኔራል ገዛኢ አበራ ግንባር ግንባራቸውን ተብለው ባልተገደሉ ነበር። ጎሮቤታችን ባለችው መንግስት የሌላት ሶማሊያ ውስጥ እራሱ በዚህ ደረጃና በዝህ መልኩ ባለስልጣናት ሲገደሉ አይታይም ። የአንድ አገር የመከላከያ ሠራዊቱ አዛዥ ማለት አገሪቷ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ውስጥ ቢትገባ እራሱ ከውድመት ያድናታል ተብሎ ተስፋ የሚጣልበት የበላይ አካል ነው። እዩ እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ያደራጁት የፀጥታ አካላት እንኳን አገርና ዜጎቿን ከአደጋና ጠላት ሊጠብቅ ቀርቶ የአገሪቷ ዋነኛ ስልጣን የተቆጣጠሩ ባለስልጣናትንም ከግድያ ሊያስተርፍ አልቻለም። ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች በስጋትና ፍርሃት የተሞላ ኑሮን መኖር ከጀመሩ አመታት ተቆጥሯል።

ኢትዮጵያውያን በገዛ አገራቸው ከሚኖሩበት ቀዬአቸው መቼ እንደሚፈናቀሉ፣ በምን ጊዜ ሁኔታና በማን ሊገደሉ እንደምችሉ አርግጠኞች አይደሉም። መንግስት ከአደጋ ሊጠብቃቸው እንዳልቻለም በተደጋጋሚ አረጋግጦላቸዋል። በየቀኑ ባላሰቡት ቦታና ጊዜ የሚዘረፉ፣ የሚደፈሩና የሚገደሉ የአገራችን ዜጎች መንግስት ከዘራፊዎች ደፋሪዎችና ነብሰ-ገዳዮች ሊያስጥላቸው አቅም እንደሌለው ከተገነዘቡ ቆዩ።







ከዚ የነ ዶ/ር አምባቸው መኮንንና ጀኔራል ሰዓረ መኮንንንሜጀር ጀኔራል ገኣዚ አበራ እናሌሎች ግድያ ተከትለው ደግሞ ምን ያክል ህዝቡ በስጋት እንደሚሞላና ሙሉበሙሉ ከመንግስት አመኔታን እንደሚያጣ መተንበይ ቀላል ነው። ዛሬ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ፀጥታቸውን የሚያስከብርላቸው አካል ባለመኖሩ መንግስት አለ ብሎ ለመቀበል ተቸግረዋል።

አምስት የሚሆኑ ከፍተኛ የአገሪቷ ባለስልጣናት በግማሽ ቀን በተተኮሰባቸው የጥይት እሩምታ ሲገደሉ የአገር ውስጥ ፀጥታ አስከባሪው ዬት ነበር? በባህዳር የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ላይ የተፈፀመው የግድያ ወንጀል የተፈፀመው ቀን 10 ሰዓት አካባቢ ሲሆን ጀኔራል ሰዓረ መኮንንና ጓኞቻቸው የተገደሉት ደግሞ ምሽት 3 ሰዓት አካባቢ ነው። ጀኔራል ሰዓረና ጓደኞቻቸው በአዲስ አበባ የተገደሉት ዶ/ር አምባቸውና ባልደረቦቻቸው ከተገደሉ ከአምስት ሰዓታት ቆይታ በኋላ ነው ። ለግል ጥቅም ሲል የባለሀብቶችንና የአንዳንድ ባለስልጣናትን ስልክ ጠልፈው በመሰለል ላይ የተጠመደው የመረጃና ደህንነት ፅህፈትቤቱ የተጠርጣሪዎችን ስልክ ጠልፈው እንኳን የነ ጀኔራል ሰዓረን ግድያ

መቆጣጠር አልቻለም። እነዚ የአገርን ክብር የሚያሳንሱና የአገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ከባድ ወንጀሎች ሲፈፀሙ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ሹመኞች በማርዮት አፓርትመንት እና Hyatt Regency Hotel እየተዝናኑ ነበር። ወንጀል ተበራክተው ዜጎች ወጥተው መግባትን በፈሩበት፣ የውጪ አገር ድፕሎማቶች ላይ ተደጋጋሚ ወንጀሎች እየተፈፀሙ ባለበት፣ የህዝቦች ግጭትና መፈናቀል የአገሪቷ መለያ በሆነበት ጊዜ ላይ ለመዝናናት የሚሆን ጊዜ ከዬት ተገኝተው ይሆን?

ዶ/ር አብይ አህመድ ኢትዮጵያውያንን ከገቡበት ስጋት አላቀው አገራችንን ወደፊት መምራት ከፈለጉ፣ አጠቃላይ የፀጥታ መዋቅሩን እንደገና በአዲስ መልክ ከጥቅም ትስስር ነፃ በሆኑ አካላትመልሰው ማደራጀት ምርጫ የሌለው ዋነኛና ጊዜ የማይሰጠው ተግባራቸው መሆን ይገባል።

ዶ/ር አብይ አህመድ ልክ ወደ ጠቅላይ ሚኒስተርነት የመጡ ጊዜ ከጎናቸው ቆመው ሲደግፉትና ሲያግዙት የነበሩ አካላት በርካቶች ነበሩ ። የዶ/ር አብይ አህመድን ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ መመረጥን ተከትለው በእርሳቸው ተስፋ ያደረገ ተማሪው፣ መምህሩ፣ ፖሊሱ፣ ሊስትሮው፣ ቀን ሰራተኛው፣ ሾፌሩ፣ አዛውንቱ፣ ነጋዴው፣ ሀይማኖተኛውና ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል አገሪቷ ወደተሻለ ምዕራፍ ትሸጋገራለች ብሎ በማሰብ በተለያየ መንገድ ደስታቸውን ገልፀው ነበር። ከህወሃት አገዛዝ ጋር በመፋለም ዶ/ር አብይ አህመድ ወደአገር መሪነት እንዲመጡ ጉልህ አስተዋፅኦ ያደረጉ አመራርም ነበሩ። አሁን ግን በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ዙሪያ ሲደግፏቸው የነበሩ ዜጎችም ሆኑ ሲያግዟቸው የነበሩ የፓርቲ ባለውለታዎቻቸው የሉም። ለምን ካላችሁ:- ህዝቡ ከእርሳቸው አመኔታን በማጣቱና አጋሮቻቸው ደግሞ ተገፍተው እርሳቸው እንዲርቁ በመደረጋቸው ምክንያት ነው። አሁን





በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ዙሪያ ሆኖ የአሃዳዊ ስርዓትን እንዲመሰርቱ እያስጨነቋቸው የሚገኙትና የዘረፋ ድርጊቶቻቸውን እያጧጧፉ የሚገኙት እነ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ አቶ አለማየሁ ከተማ፣ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ፣ አቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል፣ ዶ/ር ወንድወሰንና ጥቂት አቅም የሌላቸው የኢህአዴግ ሰዎች ብቻ ናቸው ። ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያለህዝቡ ድጋፍና ሌሎች አመራሮች እገዛ ለየብቻ አገር ማስተዳደርን እንደማይቻል አውቀ ከነዚ የቤተመንግሥቱ ዘዋሪዎች ተፅዕኖ እራሳቸውን አላቀው ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ ጊዜው አልረፈደባቸውም። እምቢ አሻፈረኝ ብሎ በዚህው መንገዳቸው ከቀጠሉ ግን ለራሳቸውም፣ ለድርጅታቸውም ሆነ ለኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ጥቁር ታሪክ ውስጥ ስማቸውን አኑረው እንደሚያልፉ ለማወቅ ጠንቋይ መሆን አይጠበቅም።

## የዶ/ር አብይ አህመድና አቶ ለማ መገርሳ ጉዳይ

ብዙዎች ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወደ ኦሮሚያ ክልል መንግስትና ወደያኔው ኦህደድ ጠርተዋቸው፣ ከኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ያስዋወቋቸውና የኦህደድ ሊቀመንበርነት ስልጣናቸውን የለቀቁላቸው እንዲሁም በጫንቃቸው ተሸከሞአቸው ለጠቅላይ ሚኒስቴርነት ያበቁአቸው ባለውለታቸውአቶ ለማ መገርሳን እንደከዱ አልተገለጠላቸውም።



ዶ/ር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከመሆናቸው በፊት በተለያዩ መድረኮች ላይ ከኦሮሞ ህዝብ ከተወጣጡ ወጣቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣





በተለያየ ዳረጃ የሚገኙ አመራር፣ አርቲስቶች፣ ዲያስፖራዎች፣ የተቃዋሚ ጎራ ፖለቲከኞች፣ አክቲቬስቶችና ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር የኦሮሞ ህዝብን የወደፊት እጣፋንታ አስመልክተው መወያየታቸው ይታወሳል።

በነዚም መድረኮች ላይ በኦሮሞ ህዝብ ትግል ውስጥ ሲጠየቁ የነበሩትን ጥያቄዎችና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ እመልሳለሁ በማለት በነበሩት የትግል ጊዜያቶች ውስጥ ትልቅ መስዋዕትነት ለከፈለው የኦሮሞ ህዝብ በተደጋጋሚ ቃል ገብተው ነበር። በዚም የተደሰተው ምስኪኑ ህዝብ ስላመናቸውና አመኔታውን ስለጣለባቸው በሀሴት ተሞልቶ በየሄዱበት ሁሉ ያጨበጭብላቸው ጀመር፣ አቀፉቸው፣ ሳማቸው። ከዚያም ያግዛቸው ጀመር። ካባቸውንም አውልቀው የደረቡላቸውነበሩ።

ዶ/ር አብይ አህመድ ልክ የጠቅላዩ ሚኒስቴርነትን ስልጣንን እንደተቆናጠጡ ለጥቂት ግዜ “ለኢትዮጵያ የተላከ መስህ”ናቸው ካሉአቸው በኋላ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ እንዲመለስ የማይፈልጉ አካላት ከሊቅ እስከ ደቂቅ ይዘምቱባቸው ጀመር። ዶ/ር አብይ “ዘረኛ ነው’” “የአነግ ተላላኪ ነው”፣ “አገሪቷን ሊያፈርስ ነው” ወዘተ ማለት ጀመሩ። “ዶ/ር አብይ ክዶናል” አሉ። እነዚ በመንግሰት መዋቅር ውስጥም ሆነ በውጪ ያሉ አካላት በአንድነት በእጃቸው የሚገኘውን መገናኛ ብዙኃንና ሁሉንም መንገድ ተጠቅመው ዶ/ር አብይ አህመድ ላይ ዘመቱ። በዚህን ጊዜ ምንም የሚዲያ የበላይነት ባይኖራቸውም ግን መላው የኦሮሞ ታጋዮች በሙሉ በአንድነት ቆሞ እነዚህን ጠላቶች በቻሉት ሁሉ መከቱላቸው። ጠቅላዩም በዚህ ጫና ውስጥ ከቲም ለማ ጋር በመሆን የተከመሩ በርካታ የፖለቲካ

ችግሮችን ለመፍታት ቻሉ። ምንም የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄዎችና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች አንዳቸውም ምላሽ ባያገኙ እንኳ።

በነገራችን ላይ ወደመጀመሪያ አካባቢ ለውጥ ሲባል ህዝቡ ዘንድ ብልጭ የሚለው ቲም ለማ የሚለው ቃል ነው። ቲም ለማ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የሚታወቀው እንደማንኛም ስም አይደለም። ቲም ለማ/ Team Lemma የህወሃትን አምባገነናዊ ስርዓት በመገርሰስ የነፃነት ወጋገን ተስፋው ጨልሞበት ለነበረው ተጨቋኙ ኢትዮጵያ ህዝብ ያበራ የትግሉና ለውጡ ተምሳሌት ነው። ቲም ለማ የተመሰረተው የቀድሞዎቹ የኦህደድ አመራርየአዲስ አበባ ማስተር ፕላንን ለምን ተቃወማችሁ በማለት ከወያኔ ጋር በማበርህዝባችንን ከጨፈጨፉና ካስጨፈጨፉበት ማግስት፣ እነዚ ሁለቱ ቡልጉዎች/ ጭራቆች ከስልጣናቸው በመነሳታቸው የኦዲፒ ሊቀመንበር ሆነው በኦህደድ ምክርቤት ከዚያም የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሆነው በጨፌ - የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምክርቤት በተመረጡት በለውጡ መሃንዲስ አቶ ለማ መገርሳ ነው። ቲም ለማ የህወሃትን የበላይነት አምባገነናዊነትና ኢኮኖማያዊ ተጠቃሚነት ለአንደና ለመጨረሻ ጊዜ ለመገርሰስ አቶ ለማ መገርሳ የዘየዱት የኢህአደግ አመራር ቡድን ነው። የቡድኑን ተጫዋች አባላት የመለመሉት የጨዋታውን አሰላለፍና ደምብ የፈለሰፉት የቡድኑ መስራችና መሪ አቶ ለማ መገርሳ ነበሩ።

ቲም ለማ ህወሃትን የመገርሰስ ግብን አልመው በዋናነት ከብአዴን/ አዴፓ እነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፣ አቶ ደመቀ መኮንን፣ አቶ ተስፋዬ፣ ከኦህዴድ አቶ ለማ መገርሳ፣ ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ዶ/ር አብይ አህመድ፣ ወ/ሮ አዳነች አቤቤን በውስጡ አካተው ወደጨዋታው ገባ። የቲም ለማ የጨዋታ





ፍልስፍናም ኦሮማራ ተባለ። ህወሃትን ለመግፋት የግድ የኦሮሞና አማራ ህዝብ ጥምረት ከአስፈላጊም በላይ ግዴታ ነበር። የኦሮሞና አማራን ህዝብ እያጋጩ የራስ ስልጣንን ማራዘም የህወሃት መሪ ስለነበር ሁለቱ ህዝቦች እንዳይስማሙና አንድ እንዳይሆኑ ቁጥር ስፍር የሌለው የተንኮል እውቀትና ገንዘብ ፈሶበት 27 አመታት በሙሉ ከሚታሰበው በላይ ተሰርቶበታል። ይህንን በመረዳት ቀድሞ ኦሮማራን የጨዋታው ፍልስፍና ያደረጉት አቶ ለማ መገርሳ ጥምረቱን ህዝባዊ ለማድረግ ሲባል ጣና የኛ ነው በሚል መሪ ቃል ከኦሮሚያ ክልል በመቶዎች የሚቆጠሩ ልዑካኖችን በመያዝ ወደ ባህርዳር አመሩ። በእምቦጭ መጤ አረም ከተወረረው የጣና ሀይቅም የቻሉትን ያክል ነቀሉ። ቀጥለውም ከአማራ ክልል ከተወጣጡ የማህበረሰቡ ልዑካን ቡድኖች ጋር በሙሉአለም አዳራሽ መከሩ። ብዙ ተጫወቱ፣ በነ አሊ ቢራ ዘፈንም ጨፈሩ። አቶ ለማ መገርሳም ወደዚህ መድረክ ወጥተው ይህንን ብሎ ነበር፦

«ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ ዛሬ ባየነው ትዕይንት ትርጉሙ ገብቶኛል፡፡ኢትዮጵያዊነት ልዩ ነው፡፡ አትዮጵያዊነት ሱስ ነው፡፡ከደም አልፎ ልቡ ውስጥ እንዳለ ዛሬ አይተነዋል፡ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የትም ይሁን የት ፣ምን ያህል የኢትዮጵያዊነት ርሀብ እንዳለበት በመላው ዓለም የሚገኙ ሁሉ መምጣታችንን ሲሰሙ ምን ያህል በውስጣቸው እንዳደረ አይተናል፡፡ ችግሮቻችንን በጋራ እየፈታን ለእድገታችን የምንሰራበት ጊዜም ነው፡፡

ለዚች ሀገር ህይወቱን አሳልፎ የሰጠው ይህ ህዝብ ለሀገሩ፣ ለአንድነቱ ነው፡፡ ትናንት በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ደሙን የገበረው ለኢትዮጵያ ነው፡፡ ለሀገራችን አሁንም መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ወደ ኋላ እያየን

ወደፊት ልንጓዝ አንችልም፡፡ ያለፈውን እንርሳው፡፡ ለሀገራችን አንድነት በጋራ እንቁም። ዛሬ አማራ ክልል የተገኘነው እንደምስታፈልጉን፣ እንደምናስፈልጋችሁ ስለምናምን ነው፡፡ ለኢትዮጵያችን ሁሉም ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ያስፈልጓታል፡፡ ፍቅር ያሸንፋል፡፡ ብሄሮች በጋራ ሊቆሙላት ይገባል፡፡ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ላይ ነው ያለነው፡፡ በጎረቤቶቻችን ላይ ያለውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ለምናደርጋቸው ነገሮች ሀላፊነት ሊሰማን ይገባል፡፡ የሀገሪቱ ተረካቢ ለሆነው ወጣት ስራ ልንፈጥርለት ይገባል፡፡ ትውልዱን ለመቅረጽ ደግሞ ቅድሚያ የሚወስደው ቤተሰብ ነው፡፡ በመቀጠልም ማህበረሰብ፤ ስለሆነም ለስነ-ምግባር ጉዳይ ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል፡፡ አባቶች፣ አባ ገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ስነ-ምግባርን በተመለከተ ትኩረት ልትሰጡት ይገባል፡፡"

በአዳራሹ የተገኘው ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በንግግራቸወሸ ተደምመው በህወሃት ሴራ እያዘነ አቶ ለማ መገርሳ አገሪቷ ካለችበት ቀውስ እንደሚያወጧት ተስፋውን ጣለባቸው።

በዚ ጣና ዳር በሚትገኘው በባህርዳር ከተማ ህወሃት ላይ ባስቆጠረው ጎልም፣ አገሪቷን ከገባችበት ቀውስ ያወጣት ዘንድ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ቲም ለማ ላይ አመኔታና አደራ ተጣለ። ኦህደድና ብአዴንም ለቀጣዩ ጨዋታቸው እጅለእጅ ተያይዘው ቃል በመገባባት ዝግጅቱን ቋጩ።

ከጣናን ኬኛ መልስም ብዙ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስራዎች ተሰሩ። ኦህደድና ብአዴን በመልዕክቱ ተመሳሳይነት ይዘት ያለው መግለጫ ማውጣትን ተያያዙት። ህወሃትም ከወስጥና ከውጪ ተቃውሞ በረታባት። የወስጡ የህወሃት ተጋጣሚዎች ኦህደድና ብአዴን ሲሆኑ የውጪ





ተፋላሚዎቿ ደግሞ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ስም የተቀጣጠለውን በኦሮሞ ወጣቶች ትግል ተከተው ወደአደባባይ ተቃውሞ የገቡ ህዝቦች በሙሉ እና ምዕራባዊያን ናቸው።

ህዝቡ ከየአካባቢው የመግንስት አስተዳደርን አፈረሰ። ታላቋ አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት ህወሃትን ተስፋ የሚያስቆርጥ አቋም መያዝ ጀመሩ። የምዕራባዊያን መገናኛ ብዙኃንም ለኦሮሞ ህዝብ ትግልና አጠቃላይ ለአገሪቷ አሳሳቢ ሁኔታ ሽፋን መስጠት ጀመሩ። 2.6 ሚሊዮን ኦሮሞዎችን ከሶማሌ ክልል ማፈናቀሉ፣ የአስቸኮይ ጊዜ አዋጁን ማሳወጅ፣ ያገኘችውን ሁሉ ማሰር መግደል እና ሌሎች ሴራዎቿ ተደምረው ምንም ሊፈይዷት አልቻሉም። በአውሮፓ ህብረት ግፊት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ በርካታ የፖለቲካ እስረኞችን ፈቱ። ብዙም ሳይቆይ አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለመልቀቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የመልቀቂያ ደብዳቤ አስገቡ። ደብዳቤውም ተቀባይነት አገኘ። የኢህኣደግ አባል ድርጅቶችም ያለውን ሁኔታ አስመልክተው በሊቀመንበሮቻቸው አማካኝነት በኢቴቪ ስቱዲዮ ተገኜተው መግለጫ ሰጡ። ከዚም መግለጫዎች ውስጥ አቶ ለማ መገርሳ የኦህደድ ሊቀመንበር ሆኖ በታህሳስ 25 , 2010 ዓ.ም "ወደዚህ ግምገማ ስንገባ ለውድድር አልነበረም። አንዱ ሻምፒዮና ለማድረግ.... አንዱ ሻምፒዮን ሆኜ ወጣሁ ቢልም የሚሸለመው ሜዳሊያ አይኖርም። ብዙ ችግር ውስጥ ወድቀናል። ሀገሪቷ ቀውስ ውስጥ ነው ያለችው። ለጨዋታ ብለን የገባን ግምገማ አልነበረም። ወደዚህ ግምገማ ስንገባ የግለሰብ ክብር፣ ስልጣን... የማንም ስልጣን ገደል ይግባ! ከሀገር በላይ አይደለም።

ከማናችንም ስልጣናችን፣ ከብራችን፣ ከሀገር በታች ነው።" ያሉበትንግግራቸው በሁሉም ኢትዮጵያውያን ልብ ዘንድ ሰርፃ ገባች።

**የኢህአደግ ሊቀመንበርነት ምርጫ**

መስከረም 25፣ 2011 ዓ.ም በሃዋሳ ሲካሄድ በቆየው የኢህአዴግ 11ኛው ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ የአቶ ሀይለማርያም ደሳለኝን የመልቀቂያ ጥያቄ ተመስርተውየተካሄደው የኢህአደግ ሊቀመንበርነትና ም/ሊቀመንበርነት ምርጫ የተካሄደውነበር። በዚህም 177 የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ድምጽ የሰጡ ሲሆን ዶ/ር አብይአህመድ 176 ድምጽ በማግኘት ሊቀመንበር በመሆን ተመርጠዋል። አቶ ደመቀ መኮንን ደግሞ 149 ድምጽ በማግኘት ምክትል ሊቀ መንበር ሆነው ተመርጠዋል።አቶ ለማ መገርሳ የኦህደድ/ ኦዲፒሊቀመንበርነትስልጣናቸውን አሳልፈው በመስጠትና ከኢህአዴግ እህት ድርጅቶችጋር በመነጋገር ዶ/ር አብይ አህመድ ሊቀመንበር ሆነው እንዲመረጡ ለማስቻል የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ በተጨማሪ ዋጋ ከፍለዋል።

**የለጋ ጣፎ ለጋ ዳዲ ህገወጥ መሬት ወረራን አስመልክተው**

የለጋ ጣፎ የህግወጥ ቤቶችን ግንባታን አስመልክተው የተለያዩ ሀሳቦች በየሚዲያው ቀርበው ሲያጨቃጭና ሲንሸራሸሩ መቆየታቸውን ለማየት ችለን ነበር። በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት የሚስተዋለውን የህገወጥ ቤቶች ግንባታንና የመሬት ወረራን አስመልክተው እንደ አጀንዳ በመያዝ የተወያየበት የኦህደድ/ ኦዲፒ ስራአስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ ነበር። ወይይቱም የተጠናቀቀው በነዚህ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ከተሞች በተለይም በዋና ዋና ከተሞች እንዲሁም በፊንፊኔ ዙሪያልዩ ዞን ያሉት ህገወጥ ቤቶች በጥቂት ወራት ውስጥ መፍረስ





እንዳለባቸው ውሳኔ በማስተላለፍ ነበር። ውሳኔውም ተገባራዊ ይሆን ዘንድ ሁሉም የከተሞቹ ከንቲባዎች ህገወጥ ቤቶችን ማፍረስ እንዲጀምሩ ትዕዛዝ ተሰጣቸው። ቀድሞ ወደስራ የገቡት የለገጣፎ ለገ ዳዲ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ ሀቢባ ቀድመው ወደተባለው ስራ በመግባታቸውበለጋ ጣፎ ከተማ የሚገኙ ህገወጥ ቤቶች መፍረስ ጀመሩ ። በዚ መሀል ከዬት መጣ የተባለ ወሬ 'በለገ ጣፎ ዘርን መሰረት ያደረገ ማፈናቀል እየተፈፀመ ነው' በማለት የግል መገናኛ ብዙሃንን በማጥለቅለቁጉዳዩ በጣም ተራገበ። ጉዳዩ ወደ መንግስታዊ የሆኑት መገናኛ ብዙኀንም ማምራቱ አልቀረም ነበር። ጉዳዩን ለማጣራት ሲሉ የተወሰኑት ሚዲያዎች የኦሮሚያ ክልል የመሬት አስተዳደር ሀላፊ ዶ/ር ሚልኬሳ ሚደጋን አነጋገሩ። እርሳቸውም ህገወጥ ግንባታ ላይ እርምጃ መውሰድ የመንግስት አቋም በመሆኑ ዘመቻው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናገሩ።ምንም ዶ/ር ሚልኬሳ ሚደግሳ ሁኔታዎችን እያዩ የሚገለባበጡ ጀማሪ ካድሬ ቢሆኑም። ጓደኛቸው አቶ ታዬ ደንደአ ግን ከዚህ በተቃራኒ ያመኑበትን ከመናገርና ከማድረግ ወደኃላ የማይሉ ለህዝቡ ብሎ መስዋትነትን የከፈሉ ወጣት አመራር ናቸው።


የለጋ ጣፎ ለጋ ዳዲ ከንቲባም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ምላሽ ለመገናኛ ብዙኀን ሰጥተዋል። የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ የህገወጥ ቤቶች ላይ እርምጃ መውሰድ በቅርቡ እንጀምራለን ብለው ነበር። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኢንጂኔር ታከለ ኡማ ስለጉዳዩ ተጠይቀው ለጋ ጣፎና አዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ከንቲባዎች የሚተዳደሩ ናቸውና እኔን የሚመለከተኝ ስለአዲስ አበባ ብቻ ነው በማለት ምላሻቸውን ለተወሰኑ ሚዲያዎች ሰጥተዋል።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ሲጠበቅ የነበረው የያኔው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ለማ መገርሳ ከሳምንት በኋላ 'ህገወጥ ሳይሆን የፈረሰ ቤት ካለ እናጣራለን'በማለት የሌሎቹን ምላሽ አጠናክረዋል። የህገወጥ ቤቶቹን የማፍረስ ዘመቻ 'ዘርን መሰረት ያደረገ ማፈናቀል' በማለት ጉዳዩን ወደመገናኛ ብዙኃን ወስደው ሲያራግቡ የነበሩ አካላት በለገ ጣፎ ህገወጥ ቤቶቻቸው የፈረሰባቸውን ግለሰቦች በማደራጀት ወደጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት በማምራት ከተወሰነ ደጅ ማጥናት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስተሩን ለማናገር ችለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከተወሰኑ ቀናት በኋላ በለገ ጣፎ ህገወጥ ቤቶች ላይ ስለተከፈተው ዘመቻ ተጠይቀው "እኔ ስለጉዳዩ የማውቀው ነገር የለም።" በማለት በመርገዝ የተለወሰ ምላሽ ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በሊቀመንበርነት የሚመሩት ፓርቲ በጉዳዩ ላይ ተወያይተው አቋም በመያዝ ወደተግባር የገባውን የህገወጥ ቤቶች ግንባታና መሬት ወረራጉዳይን አላውቅም በማለት ሸመጠጡ። ጉዳዩን አላውቅም ያሉበት ምክንያት ውሎ ሳያድር ወዲያውኑ ታወቀ። ዶ/ር አብይ አህመድ ይህንን ያሉበት ምክንያት አቶ ለማ መገርሳን ከአማራ ህዝብና ሌሎች ኦሮሞ ካልሆኑ ህዝቦች ጋር ለማጋጨት እንደሆነ ውሎ ሳያድር ተደረሰበት። ይህንን የሚያደርጉት ከዶ/ር አብይ አህመድ በላይ አቶ ለማ መገርሳ ከአማራና ሌሎች ህዝቦች ተቀባይነትና ተወዳጅነትንለመጎናፀፍ ስለቻሉ ነው ።







በመቀጠልም ከሶማሌ ክልል የተፈናቀሉትን ኦሮሞ ተፈናቃዮች በከተማ የማስፈርና የከተማ ፖለቲካን አስመልክተው፣ አቶ ለማ መገርሳ የተናገሩበት ቪዲዮ ከመጣ ሳይባል ሚዲያዎች ተቀባበሉት፤ በማህበራዊ ትስስር ድረገፆች ላይም ተሰራጨ። ይህ አቶ ለማ መገርሳ በከተማን ፖለቲካ አስፈላጊነት አስፈላጊነት ዙሪያ ትንተና የሰጡበት ቪዲዮይገኝ የነበረው በጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ብቻ ነበር። በመሐል አገር ከተማ አካባቢዎች በተለይም በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚኖሩ ህዝቦች አቶ ለማ መገርሳን እንዲጠሉዋቸውና የተከፈተባቸውን ዘመቻ ለማጠናከር ሲባል፤ይህ ቪዲዮ በቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ትዕዛዝ በአቶ ሽመልስ አብዲሳ በኩል ይፋ ባልሆነ መልኩ ተደብቀው እንዲወጣ ተደረገ። ነገር ግን እንዳሰቡት አቶ ለማ መገርሳን ከላይ ከተጠቀሱ የማህበረሰቡ ክፍሎች ጋር በማጋጨት ተቀባይነታቸውንና ተወዳጅነታቸውን ለመነቀስ አልተቻላቸውም።


**የኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለባለዕጣዎች ወይም ዕድለኞች መተላለፍን አስመልክተው**

የተለያዩ የፕሮግራሞችንና ለፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የዜጎችን መኖሪያ ቤት ችግር መፍታት የመንግስት ዋነኛ ተግባር መሆኑ ይታወቃል። መንግስት በዚህ መሰረት የአዲስ አበባ ኗሪዎችን የመኖሪያ ችግር ለመፍታት ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት በእቅዱ ላይ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥናትን ማካተት ነበረበት። በየፕሮግራሞቹና ለፕሮጀክቶቹ ላይ ሳይካተት ቀርተውበመሐል ችግሮቹ ተስተውለው ከሆነ ደግሞ የፕሮጀክቶቹን ትግበራ አቁሞ እንደገና ማጤን ነበረበት። አለፍ ካለ ደግሞ ፕሮጀክቶቹን መቀየር ይቻል ነበር። ምንም የኗሪዎች የመኖሪያ ቤት ችግር በሎተሪ የማይቀረፍ ቢሆንም የአዲስ አበባ ኗሪዎች በተቀመጠው አቅጣጫ ገንዘባቸውን ቆጥበው የቤት ባለቤት መሆን መብታቸው ነው። የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አርሶአደሮችን አፈናቅላችሁ ቤት ስጡን አላሉም። በሌላ በኩል ደግሞ ፕሮጀክቱ ለአስከፊ ቀውስ ይዳርገናል ብለው መቃወምም የአርሶአደሮቹና ወገኖቻቸው መብት ነው። በአጠቃላይ በመንግስት ስህተት ባለዕድለኞቹና ተፈናቃዮቹ ያልተገባ ቁርሾ ውስጥ መግባት የለባቸውም። የዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት ግን ይህንን ህዝቡን የማባላቱን ፖለቲካዊ ሴራ የሚፈልገው ይመስላል። የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትን ሳያማክሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ኡማን ብቻ ቢሮአቸው ድረስ ጠርተው በኮዬ ፈጬ ተገንብተው ያለቁትን የጋራ መኖሪያ ቶሎዕጣ አውጥተው ለዕድለኞቹ እንዲያከፋፍል ያዘዙአቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ነበሩ። ኢንጂነር ታከለ ኡማምንም ውሳኔው





ባያሳምናቸውም የጠቅላዩን ትዕዛዝ ተቀብለው እርሳቸው እንዳሉት ቤቶቹን አከፋፈሉ።



ከቀናት በኋላ የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ላይ ዕጣ መውጣቱን ተከትለውበተለያዩ በርካታ የኦሮሚያ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፎች ተደረጉ። የኮዬ ፈጬ መኖሪያ ቤቶች የሚገኙበት ቦታ ተገኝተው ተቃውሞአቸውን ያሰሙ ወጣቶችም ነበሩ። ተቃውሞው በቤቶቹ ለምን ዕጣ ወጣ ሳይሆን የኦሮሚያ ክልልና ፊንፊኔ ከተማ ድንበር ጉዳይ እልባት ሳያገኝና ከቦታው ተገፍተው ለተባረሩ አርሶአደሮች በቂ ካሳ ሳይሰጥ ለምን ዕጣ ይወጣል ነው ። በተጨማሪም የኮዬ ፈጬ መንደር መተዳደር ያለበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሳይሆን በኦሮሚያ ክልል መንግስት ነው የሚል ነው።

ይህንን የህዝቡን ተቃውሞ ተከትሎ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የክልሉን መንግስት ሳያማክሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶቹን ለዕድለኞች ማደል ትክክል

አይደለም በማለት የክልሉን አቋም በመገናኛ ብዙኋን በኩልአስተላለፉ። ይህንን የክልሉን መግለጫተከትለው ኦሮሞ ያልሆኑት የፊንፊኔ ከተማ ነዋሪዎች ትኩረታቸውን ወደ አቶ ለማ መገርሳ ላይ በማድረግ ይቃወሙት ጀመር። የለገ ጣፎንቤቶችን ማፍረስ ዘመቻ እኛ ነን ያስቆምነው እያሉ ስፎክሩ የነበሩት የግምቦት 7/ ኢዜማ አመራርም ጉዳዩን አራገቡ። አቶ ለማም እንዲወገዙ ዘመቻውን አጠናከሩ። የኦህደድ/ ኦዲፒ ሊቀመንበር ሆነው እያሉ የክልሉን ፕሬዝዳንት ሳያማክሩ የኮንዶሚኒየም ቤቶቹእንዲያከፋፈሉ በድብቅ ለአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባ ኢንጂኔር ታከለ ኡማ ትዕዛዝ የሰጡት ዶ/ር አብይ አህመድ ከጅምሩአቶ ለማ መገርሳን ለማሳጣትና ከህዝቡ ለማጋጨት በማሰብ ነበር። በዚህ ሴራ አቶ ለማ መገርሳን በሁለት በኩል ከኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎችና ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችግር በተመሳሳይ ጊዜ ለማጋጨትበማለም ነው።

"አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሞ ህዝብ እንዲወድህ ጋርዶሃል። ለማ እያለ አንተን ሊወዱ አይችሉም፤ ህዝቡ በለማ ውስጥ ነው እያየህ ያለው። ስለዚህ ለማን በተቻለው ሁሉ ማስወገድ አለብህ።" ብለው ባለቤታቸው ዶ/ር አብይ አህመድን የመከሩት ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው እኚህተወዳጅ መሪን ለማጥፋት ያላሰሩትና ያላዘመቱባቸው ባለስልጣን የለም።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኦሮሚያ ክልል ልዩ ዞን ከተገነባው የኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ግማሽ ያህሉ ያለዕጣ ከአካባቢው ለተፈናቀሉ አርሶአደሮች እንደተሰጠ መገለፁን ሰምታችሁ ይሆናል። ይህ የኦሮሞ ወጣት እንዳያምፅ ተብሎ የተቀነባበረ የውሸት ዜና ነበር። ያለዕጣ የተከፋፈሉት የጋራ መኖሪያ ቤቶቹ የተሰጡት ለአካባቢው አርሶደሮች





ሳይሆን በአቶ ሽመልስ አብዲሳና ከንቲባ ታከለ ኡማ ለተቀጠሩ ብሎገሮችና የማህበራዊ ሚዲያ አክቲቬስቶች ነው። አቶ ሽመልስ አብዲሳና ኢንጂኔር ታከለ ኡማ ምንም በአህደድ/ ኦዲፒ ውስጥ ሁለት ቡድኖችን በመፍጠርጊንጪና አምቦ ተባብለው ቢነታረኩም ተስማምተው የኮዬ ፈጬን ቤቶች ለወዳጆቻቸውና ቅጥረኞቻቸው አከፋፍለዋል።

**የኦሮሞ ብሔርተኝነት አቋማቸው**

ዶ/ር አብይ አህመድ የፌደራሊዝም ስርዓቱን አይፈልጉትም። ይህንን ደግሞ ከሚያደርጉት ነገረ ስራቸው ለመረዳት ይቻላል። እየደገፉ ያሉት የዜግነት ፖለቲካ አንዱ ማሳያ ነው። የዜግነት ፖለቲካ የሚለውን እራሱ ለአገራችን ያስተዋወቁት እራሳቸው ዶ/ር አብይ አህመድ ናቸው። የዜግነት ፖለቲካን እንዲያራምዱ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ያደራጁትና ከሌሎች ጋር በመዋሃድ ኢዜማ ብለው አዲስ ፓርቲ እንዲመሰርቱ ያስቻሉት ዶ/ር አብይ አህመድ እራሳቸው ናቸው። በተጨማሪም በዙሪያቸው የሰበሰቧቸው ሰዎች እነማናቸው ካልን እርሳቸው የሚፈልጉትን የፖለቲካ መንገድ ወይም አሃዳዊ ስርዓት ከሚያራምዱ ግለሰቦች መሆናቸውን ለመረዳት አያቅትም ። ዶ/ር አብይ አህመድ ወደመሪነት ለመምጣት ሲባል ብሔርተኛ መስለውየኦሮሞ ህዝብና ፌደራሊዝሙን የሚደግፉ ሌለች ህዝቦችን ቀረቡ እንጂ ቀድሞውኑ አቋማቸው የተቃራኒ ነው። የፌደራል ስርዓቱን ባይቃወሙ ኖሮ የሲዳማን ህዝብ ህገመንግሥታዊ ጥያቄ በአደባባይ አያንቋሽሹም ነበር። ብሔርተኛ የሆኑ የኦዲፒ አመራሮች ከያዝኩት ከአሃዳዊ ምስረታ ያስቀሩኛል ብለው ያሰቡት ዶ/ርአብይ አህመድ ለይተውእንዲጠቁ እያደረጉ ነው። ይህንን ደግሞ የጀመሩት የቀድሞ ባለውለታቸው ላይ በመዝመት ነው። አቶ ለማ መገርሳ አንተ በያዝከው

መንገድ ከህዝቡ ጋር እንጋጫለን ይላሉ። ስለዚህ አቶ ለማን ዞር አድርጎ የኦሮሞን ህዝብ በመከፋፈል ለመግጠም ወስነዋል። ኦሮሞ የሆኑትን ከቤተመንግስት፣ ብሔርተኛ የሆኑትን ከኦሮሚያ ክልል አመራርነት እያስመቱ ነው። ዶ/ር አብይ ብሔርተኛ በመሆኑ ኦነግን ለማጥፋት እየሰሩ በጎን ደግሞ ኢ-ዜማን ለይተው እየደገፉ ይገኛል።አቶ ለማ መገርሳ ግን በተቃራኒው በፌደራሊዝሙ እንደማይደራደሩ ገልፀው ነበር ።

ዶ/ር አብይ በኦሮሞ ብሔርተኝነት ያፍራሉ። የእናታቸውን ማንነትና አመለካከት ስለወረሱ ይሆናል።ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም የሚቆረቆር ብሔርተኛ አይደሉም። ይህንን አቋማቸውን በሚደግፍ መልኩም የኦሮሞ አርቲስቶችን በተሰበሰበበት ግዜ << የኦሮሞ ብሔርተኝነት ኦሮሞን ጎዳ እንጂ አልጠቀመም።>> ብለዋል። ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ያበቃቸውን የኦሮሞ ብሔርተኝነትንና ፌደራሊዝሙን እርግፍ አድርጎ በመተው አሃዳዊ ስርዓትን ልጭኑብን ቆርጦ ተነስቷል ።


**የቀዳማዊት እመቤቷ መርዛማ እጆች**

አቶ ለማ መገርሳን ለማጥፋት የተከፈተውን ዘመቻ በበላይነት የሚመሩት የዶ/ር አብይ አህመድ ባለቤት ወይዘሮ ዝናሽ ታያቸውናቸው። አቶ ለማን ለማጥፋት ከዘየዱት ውስጥ የመጀመሪያው በኦህደድ/ ኦዲፒ ውስጥ የሚገኙ የስራአስፈፃሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እንዲዘምቱበት ማስቻልድ ነው። ይህም በአቶ በርሃኑ ፀጋዬ መሪነት እየተፀመ ይገኛል። ሁለተኛው ከአቶ ለማ መገርሳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የኦሮሚያ ክልል አመራሮችን ከሀላፊነታቸው ማስነሳት ነው። ወይዘሮ ዝናሽ ይህንን ይፈፅሙ ዘንድ ትዕዛዝ የሰጡዋቸው ለአቶ ደመላሽ ገ/ሚካኤል ሲሆን እርሳቸው ደግሞ ትዕዛዙን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ ወደ አቶ አዲሱ አረጋ





አስተላልፏል። አቶ አዲሱም ይህንን ትዕዛዝ እየፈፀሙ ይገኛሉ። የኦዲፒ ፅህፈት ቤት ሃላፊ ሆነው ከጥቂት ወራት በፊት የተሾሙት አቶ አዲሱ መደበኛ ስራቸው ሹም ሽር ጉዳይ ላይ ብቻ ሆነዋል። አቶ ለማ መገርሳ የሾሙአቸውን አንስተው ብሔርተኛ ባልሆኑትና በደም ግማሽ ኦሮሞ በሆኑት የድርጅቱ አባላትየመተካት ስራ እየተሰራ ይገኛል። ወለጋ ሀራርጌ አርሲ ወይም ብሔርተኛ መሆን ያስወግዛል። አሁን ከሳምንት በፊት አቶ አዲሱ አረጋ ካድሬዎችን ሰብስበው እያወያዩአቸው ባሉበት መድረክ ላይ አቶ ለማ መገርሳ ኦነግ ናቸው ብለዋል። አክለውም የኦነግ እድሜ እንድረዝም ያደረገው አቶ ለማ ተብዬው ነው ብለዋል። የአቶ ለማን መገርሳን ስም የጠራ አመራር በሙሉ እየተባረረ ይገኛል።



የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ቤተሰብንና የቀዳማዊት እመቤት ወይዘሮ ዝናሽ ታያቸውን ግንኙነት አስመልክተው ያለው ሀቅ ወይዘሮ ዝናሽ

ታያቸው ለዶ/ር አብይ አህመድ ቤተሰቦች ክብር የሌላቸው መሆኑንና የቀዳማዊ እመቤቷ ቤተሰቦች ደግሞ ለዶ/ር አብይ አህመድ ጋር ምንም ቤተሰባዊ ግንኙነት እንደሌላቸውነው።

የሀይማኖት ሰዎችን ተጠቅሞም አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት እንደማይሆናቸው ጫና ለማድረግ ተሞክሯል። በተከፈተባቸው ዘመቻ አቶ ለማ መገርሳን ሊመርዙአቸው ታስቦም ቀደም ተብሎ እርሳቸው በውጭ አገር ህክምና ላይ እንደሚገኙና የጤናቸው ሁኔታ መልካም እንዳልሆነ የሚገልፁ መልዕክቶች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንዲሰራጩ ተደርጓል።



አሁን ላይ አቶ ለማ መገርሳ ከዬትኛውም የመንግስት የመገናኛ ብዙኀን ጋር እንዳይገናኙ ለየመገናኛ ብዙኀኑ ሀላፊዎች በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በኩል ትዕዛዝ ተሰጥቶአቸዋል። ይህም አቶ ለማ መገርሳ በሚዲያ





በኩል እየተኬደበት ያለውን የተጨማለቀ የፖለቲካ መንገድ ለህዝቡ ያጋልጣሉ ተብለው ስለተሰጋ ነው።

## አቶ ለማ መገርሳ ወደፌደራል የሄዱት ወደው ወይስ ተገደው?

አቶ ለማ መገርሳ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት ስልጣናቸው የለቀቁት ወደው ሳይሆን ተገደው ነው። ከአቶ ለማ መገርሳ በፊት ያለፍላጎታቸው ከነበሩበት የህላፊነት ቦታ የተገፉት ቲም ለማ ከመመስረቱ ቀደም ብለው ለአቶ ለማ መገርሳ የኦህደድ ምክትል ሊቀመንበርነት ስልጣናቸውን የለቀቁት ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ናቸው። ከዚያም ልክ ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ ለአቶ ለማ መገርሳ የስልጣን ቦታቸውን ለቀው በቲም ለማና በነበረው የህዝብ ትግል ውስጥ የራሳቸውን አሻራ እንዳስቀመጡ ሁሉ፣ አቶ ለማ መገርሳ የኦህደድ ሊቀመንበርነት ስልጣናቸውን ለዶ/ር አብይ አህመድ ለቀው ወደፊት እንዲመጡ በማድረጋቸው የሚያሳስባቸው የነበረው የህዝቡ ፍላጎት እንጂ የስልጣን ጉዳይ እንዳልሆነ አስመስክረዋል።

በቲም ለማ ውስጥ ህወሃትን በመግፋቱ ረገድ ጉልህ ሚና የተጫወቱት ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁን ከኦህደድ ሀላፊነትና አባልነት ማስወገዱ ተገቢ አልነበረም። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምክርቤት አባል ያልሆኑትን ኢንጂነር ታከለ ኡማን ህግና ደምብን ባልተከተለ አካሄድ የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አድርገው ከመሾም ይልቅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምክርቤት አባል የሆኑትንና የዳበረ የአመራር ልምድ ያላቸውን ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁን የአዲስ አበባ ከንቲባ አድርጎ መሾም አይቻለም ነበርን? ሰዎቹ ህገመንግሥቱ ይከበር የሚሉት እውነታቸውን ነው።የህዝቡን ፍላጎት የሚያስቀድሙትንና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባለውለታ የሆኑትን አቶ ለማ መገርሳን ከክልል ፕሬዝዳንትነት ስልጣናቸው ለመግፋት የተሄደበት





መንገድ የኦህደድ/ ኦዲፒን መተዳደሪያ ደምብ የተፃረረ ከመሆኑ በተጨማሪ የኢፌድሪንና የኦሮሚያ ክልል ህገመንግስቶችን የጣሰ ነበር።



አንድ የክልል ፕሬዝዳንት ከስልጣኑ መነሳት የሚችለው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው መንገድ የክልሉ ፕሬዝዳንት በገዛ ፍላጎቴ ስልጣኔን መልቀቅ እፈልጋለሁ የሚል የመልቀቂያ ደብዳቤ ለክልሉ ምክርቤት በማስገባት ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ነው። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ የክልሉ ምክርቤት ግምገማ አካሂደው ፕሬዝዳንቱ ባሳዩት የስራ ድክመት ምክንያት መቀጠል የለባቸውም የሚል አቋም ከደረሰና ከወሰነ ነው። የመጀመሪያውን መንገድ አስመልክተው አቶ ለማ መገርሳ ለኦሮሚያ ክልል ምክርቤት (ጨፌ) ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለመልቀቅ ሲሉ ያስገቡት የመልቀቂያ ደብዳቤ አልነበረም። ለምሳሌ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከአማራ ክልል ፕሬዝዳንትነታቸው የለቀቁት ህግንና ደምብን ባልጣሰ አካሄድ በገዛ ፈቃዳቸው ስልጣናቸውን ለመልቀቅ ባስገቡት የመልቀቂያ ደብዳቤ መሰረት ነው። ምንም ጠቅላዩ ሚኒስትሩ በእርሳቸው ቦታ የቅርብ ወዳጃቸው

የሆነውን ዶክተር አምባቸው መኮንንን ለመሾም ሲሉ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የአማራ ክልል በፕሬዝዳንትነት ስልጣናቸውን እንዲለቁ ጫና ሲያደርጉባቸው የነበሩ ቢሆንም። አቶ ገዱ አንዳርጋቸውን ጨምሮ ሌሎች ህወሃትን በመገፍተር በቲም ለማ/ TeamLemma ውስጥ ጉልህ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሰዎች ህዝቡ ዘንድ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን ተቀባይነት ያደበዝዛሉ ተብሎ ስለተሰጋ ቀስበቀስ ተመቷል። እየተመቱም ይገኛሉ ።

ወደሁለተኛው ህግና ደምብን የተከተለ ከክልል ፕሬዝዳንትነት የመነሳት መንገድ ስንመጣ ጨፌው ግምገማ አካሂዶና ባሳዩት የስራ ድክመት ምክንያት አቶ ለማ መገርሳ ከክልል ፕሬዝዳንትነት ስልጣናቸው መልቀቅ አለባቸው የሚል ውሳኔን አላስተላለፈም። ጭራሹኑ ጨፌው በዚ ጉዳይ ላይ አልተሰበሰበም። አቶ ለማ መገርሳን ህግና ደምብን በጣሰ አካሄድ ከክልል ፕሬዝዳንነታቸው ለመግፋት የተደረገው ሸፍጥ እንደሚከተለው ነው።


አቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የኢፌድሪ መከላከያ ሚኒስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሆኖ ከመሾማቸው አንድ ሳምንት አስቀድሞ በአዳማ የተካሄደውን የኦዲፒ አመራር ስብሰባ የመሩት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ከዚያ ቀደም ባለ ቀን ከቤተመንግስት አስተዳዳሪነት ሀላፊነታቸው ያባረሯቸውን ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩን ፊትለፊት አትኩረው እያዩ ይህንን ብሎ ነበር፦ "በቅርቡ ከቤተመንግስት ያባረርናቸው አሉ። ወደፊትም ተመሳሳይ ነገር ይቀጥላል። በሳምንት በኃላ የሚኖሩንን አዳዲስ ሾመቶችን አስመልከተው ተቃውሞ ከገጠመን መተራረድ ይመጣል።"

አቶ ለማ መገርሳን ህግና ደምብን በጣሰ አካሄድ ከነበሩበት የክልል ፕሬዝዳንትነት ስልጣን ለመግፋት ሲባል ታቅዶበት በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት





የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት በአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ ክልል ምክርቤት (ጨፌ) ደግሞ በበአዳማ በአስቸኳይ እንዲሰበሰቡ ተደረገ።



አቶ ለማ መገርሳ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባል አለመሆናቸውና በአዳማ የተጠራውን የክልሉን ምክርቤት ስብሰባ መምራት እንዳለባቸው እየታወቀ በአዲስ አበባ የሚካሄደው የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አስቸኳይ ስብሰባ ላይ መገኘት እንዳለባቸው በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ በኩል ጥሪ ቀረበላቸው። አቶ ለማም ከአዳማው ጨፌ ስብሰባ ቀርተው በህዝብ ተወካዮች ስብሰባ ላይ በተገኙ ግዜ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አማካኝነት የመከላከያ ሚኒስቴር ሆኖ ተሾሙ። የክልል ፕሬዝዳንትነት ስልጣናቸውን ህግና ደምብን በተከተለ መልኩ ሳይለቁ ሌላ ሹመት ተሰጣቸው። በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት በአዳማ ሲካሄድ የነበረው

ጨፌ ለማስመሰል አቶ ሽመልስ አብዲሳን የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት አድርጎ ሾማቸው። የአቶ ሽመልስ አብዲሳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት ሹመትም ቢሆን ህግና ደምብን ያልተከተለ ነበር። በመጀመሪያ አቶ ሽመልስ አብዲሳ የነበሩበት የፅቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ሀላፊነት እንድለቁ ለምን ተፈለገ? ቀጥለውስ አቶ ሽመልስ አብዲሳ የኦሮሚያ ክልል ምክርቤት አባል ሆነው እያሉ ለምን ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው እንዲሾሙ ተፈለገ? ከአቶ ሽመልስ የተሻለ ልምድ ያላቸው እነ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ፣ አቶ ኡመር ሁሴንና በርካታ የጨፌው አባላት እያሉ፣ እርሳቸው በምን መስፈርት እንዲሾሙ ተደረገ ?

አገሪቷ መንታ መንገድ ላይ ቆማ እየተተራመሰች በሚትገኝበት በዚህ በፈተና ሰዓት አገሪቷን ከመፍረስ ለማዳን አትኩረው መስራት ሲገባቸው፣ ጠላት ከሩቅ አይመጣም እንደሚባለው ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአራት ኪሎ ቤተመንግሥት ያበቋቸውን ባለውለታቸውን የማጥፋት ሴራ ላይ ተጠምደዋል። አቶ ለማ መገርሳ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ባለውለታ ብቻ ሳይሆኑ የፓርቲያቸው ኢህአደግ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች ባለውለታና በአጠቃላይ ኢትዮጵያ አገራችንን ከውድቀት ያተረፉ ታሪክ ለዘላለም የሚዘከራቸው የአገር ባለውለታ ናቸው።

በአገራችን እየሆነ ያለው የፖለቲካ አካሄድ፦

"ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ

የሞተልሽ ቀርተው የገደለሽ በላ።" የሚለውን እውቅ የግጥም ስንኝ አስታወሰኝ።





## አዲሱ የሙስና መረብ

ሙስና በኢትዮጵያ አብዝቶ መንሠራፋቱንና ለዚህም ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከልየሲቪክ ማህበራት በነፃነት መንቀሣቀስ አለመቻል፣ የመናገርና የፕሬስ ነፃነት መገደብ፣ የሕዝባዊ ተሣትፎ ማነስ እና የመንግሥት ለሕግጋት ተገዥ አለመሆን እንደሚገኙበት አንዳንድ ጥናታዊ ፅሆፎች ያመለክታሉ።

መንግሥት ባለፉት አስርት አመታት የፌደራልየሥነ-ምግባርናፀረ-ሙስናኮሚሽንን አቋቁሞ ሙስናን ለመከላከል የተንቀሳቀሰ ቢሆንም በአገሪቷ የሚስተዋሉት የሙስናና ተያያዥ ድርጊቶች እንኳን ሊቀንሱ ቀርተው በተደራጀ መልኩ በየአመቱ እያሻቀቡ እንደመጡ አይተናል። ዓለምአቀፉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተባለው ድርጅት በ2018 ዓ.ም ባወጣው ከሙሲና ነፃ የሆኑ አገራት ሰንጠረዥ ሪፖርቱ ኢትዮጵያን ከ180 አገራት 107ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል።

ተጠያቂነትና ግልፅነት ማጣት፣ አነስተኛ የሆነ የዲሞክራሲ ባህል፣ የዜጎች ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆን፣ ግልፅ የሆነ ህግጋትና ስልጣን አለመኖር፣ በዝቅተኛ ደረጃ ተቋማትን መቆጣጠር፣ ወንጀለኞች ላይ ቅጣት አለመጣል፣ ስልጣንና ሀብትን ጠቅልሎ መያዝ ለአገራችን ከፍተኛ የሆነ ሙስና ካበረከቱት ውስጥ መሆናቸው የአለም ባንክ በ2008 ዓ.ም የሰራው ጥናታዊ ፅሁፍ ያመለክታል። የአሜሪካ ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት እንደሚያመለከተው ሙስና፣ የግብር ማጭበርበር፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የጦር መሳሪያ ንግድና የዱር እንስሳት ንግድ ባለፉት 27 አመታት ከተስተዋሉ ዋነኛ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ናቸው።

በቅኝ ገዢዎች እጅ ያለወደቀችው ኢትዮጵያ በ1983 ዓ.ም የደርግ መንግስት ከስልጣን መወገድን ተከትለው የኢህደግ መንግስት ስልጣንን ተረከበዋል። የደርግ መንግስት መውደቅን ተከትለው ምንም የኢትዮጵያ ህዝብ ብሩህ ተስፋን ሰንቀው ቢጠባበቅም ለየት ባለ መልኩ በኢህአደግ መንግስት ሙሲና የሚባለው ፀረ እድገትና ዲሞክራሲ በሽታ በአገራችን ተንሰራፋ። ላለፉት 27 ዓመታትም የኢህአዴግ አባል ድርጅት የሆነው ግን በበላይነት አገሪቷን እንዳሻው ሲያስተዳድር የኖረው ህወሀት ያልፈፀመው የሙስና ወንጀል፣ ያልመዘበረው የአገር ሀብት፣ ያልነጠቀው የደሃ ዜጎች ጉሮሮ አልነበረም። እዚህጋ ህወሀት የፈፀመውን የሙስና መንጀል ዘርዝረው ለመጨረስ አመትም አይበቃም።

ወደ ጠቅላይ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ስልጣን ከወጡ አንድ አመት ያለፋቸው ዶክተር አብይ አህመድ ስልጣን ከያዙበት እለት አንስተውና ከዚያም በኋላ በተደጋጋሚ ዋነኛ ትኩረታቸው ሙስናን መዋጋት ላይ እንደምሆን ተናግሯል። ሙስናን እንደሚፀየፉ ለማሳየት ሌባን ሌባ ብለን በስሙ እንጥራው ብሎ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በዚህ ሙስናን የመዋጋት ጥረት ውስጥ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ መሣተፍ እንደሚኖርባቸው ተነግሯል:: እውነት ግን በቃላቸው መሰረት ሙሰኞች ለህግ እንዲቀርቡ ያደረጉት ስራ አጥጋቢ ነውን?

መቼም ሙስና የአንድ አገርን እድገት በዋነኛነት እንደሚያቀጭጭ ሁሉም የተስማማበት በመሆኑና በተለይም በታዳጊ አገራት ወስጥ የህዝብ ድጋፍን ለማግኘት ሲል 'ሙስናን መዋጋት ቀዳሚ ስራዬይሆናል' ብለው ለዜጎቹ ቃል ያልገባ አፍሪካዊ መሪ የለም።





ግሎባል ፋይናንሽያል ኢንተሊጀንስ እንዳስቀመጠው ከሆነ ኢትዮጵያ ከ1996 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ብቻ 26 የአሜሪካን ዶላር በህገ-ወጥ መንገድ ከአገር እንዲወጡባት ተደርጋለች።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ እስከጫፍ በአንድነት ታግለው የህወሃት መንግስትን ያስወገደው በዋናነት ሙስናና አምባገነንነት ስላስመረረው ነበር። የህዝብና አገር ሀብት ምዝበራው፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍሉ፣ የስራአጥነትና የግሽበት መጠኑ በከፍተኛው ስላሻቀበ፣ የመንግስት ካዝና መራቆቱና የአንድ ብሔር መክበር ስላንገሽገሹት ነበር ለውጥ አምጥተን እነዚህን የሙስና ደርጊቶች እንቀለብሳለን ብሎ ከቤታቸው ሰላማዊ ትግል ለማድረግ የወጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ውድ ህይወታቸውን የገበሩት።

አሁን ትላልቆቹ አሳዎች እነ አቶ በረከት ሲሞን፣ አቶ ስዩም መስፍን፣ ወይዘሮ አዜብ መስፍን፣ አቶ አባይ ፀሐዬ፣ አቶ ስብሃት ነጋ፣ መ/ጄነራል ክንፈ ዳኘው፣ እና ብዙ መሰሎቻቸው የሉም። እነዚህ የመሰረቱት ግዙፉ የሙስና መረብ በዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት ተበጣጥሷል። ግለሰቦቹም ከመንግስት ስልጣን ውስጥ ተገፍትረው ጥቂቶቹ ታስረው ቀሪዎቹ ደግሞ ተደብቀዋል። የህወሃት የሙስና ዘመን ከአንድ አመት በፊት አብቅተዋል። ሙስና ግን አላበቃም። እንዲሁም ተባብዋል። ዶ/ር አብይ አህመድ የጠቅላይ ሚኒስቴርነትን ስልጣን ከተቆናጠጡበት ግዜ አንስተው አዲስ የሙስና መረብ ተዘርግተው ወደስራ ገብቷል። አዲሱ የሙስና መረብ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትንና ባለሀብቶችን በውስጡ አካተዋል። ከህወሃት ጋር ሎሌ ሆነው ሙስና ሲፈፅሙ የነበሩት አሁን ላይ ተከርብተው እራሳቸውን የአዲሱ ሙስና መረብ አካል አድርገዋል።

በተለይም አቶ ጌታቸው አሰፋን ከመሳሰሉ የህወሃት ባለስልጣናት ጋር ተመሳጥረው የአገርና ህዝብ ሀብት ሲዘርፉና ሲያዘርፉ የነበሩ ጥቂት ባለሀብቶች አሁን ላይ እንደምንም ይቅርታ ጠይቀውና በአያሌ ጥቅም ተደራድረው በመንግስትና ሌሎች ባለሀብቶች መካከል እንደ ድልድይ እያገለገሉ ይገኛሉ። ለምሳሌ ያክልም 44 የሚሆኑ ባለሀብቶች ሀሰት ደረሰኝ በመጠቀም እናግብር የማጭበርበር ወንጀል ክስ እንዲመሰረትባቸው ተወስኖባቸው የነበረ ሲሆን፣ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን ግለሰቦቹ በእነ አቶ አለማየሁ ከተማና አቶ ድንቁ ደያሳ አማካኝነት ከጠቅላይ አቃቤ ህግ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ጋር በረብጣ ገንዘብ ተደራድረው እንደማይከሰሱ ቃል ተገብቶላቸዋል። አቶ ድንቁ ደያሳ ከአቶ ጌታቸው አሰፋ ጋር እየሰራ በመቆየቱ መጀመሪያ ላይ በዶ/ር አብይ አህመድ ጥርስ ውስጥ ገብቶ የነበረ ቢሆንም በጓደኛውና የቢዝነስ አጋሩ አቶ አባዱላ ገመዳ አማላጅነት ምህረት ተደርጎለታል። አቶ ድርቁ ደያስ በ2007 ዓ.ም ለአቶ ጌታቸው አሰፋ በ2 ሚሊዮን ዶላር ከዋሽንግተን ዲሲ መኖሪያ ቤት ገዝቶላቸው ነበር።

ሌላው ባለግዜ አቶ አለማየሁ ከተማ ነው። የአቶ አለማየሁ ከተማ ባለቤት ወ/ሮ ሌንሳ ጉዲና ቱምሳና ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ባለፈው ከጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን በተገኘ ገንዘብ ውጫሌ ላይ ለትምህርት ቤት ግንባታ የሚሆን መሰረተ ድንጋይ ሲያስቀምጡ በተሌቭዥን መስኮት ተመልክተናል። የህወሃት ሸርክ የነበረውና በግንባታ ስም የመንግስት ካዝናን ያራቆተው አቶ ተክለብርሃን አምባዬም አሁን ህወሃትን ክዶ በረብጣ ገንዘብ በአቶ አለማየሁ ከተማ በኩል ከነ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ጋር ተደራድረው የሰላም እንቅልፍ እየተኛ ይገኛል።





ህገወጥ የገንዘብ ዝውውሩን የሚመራው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦርድ አባሉ አቶ አባዱላ ገመዳ ነው። ህገወጥ የውጪ ምንዛሪ ገንዘብ ዝውውሩ ዛሬም አልቆመም። ነገር ግን በበፊቱ የውጪ ምንዛሬ ዝውውር መረብ ውስጥ ሆኖ ስራውን ሲሰሩት የነበሩ ግለሰቦች አሁን ከተያዘባቸው ይወረስባቸዋል። አበዛኞቹ ደግሞ ስራውንም ትተውታል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሀላፊ አቶ ተወልደ ገብረማሪያም ስራውን በአቶ አባዱላ ትዕዛዝ መሰረት ያከናውናል። ለምሳሌም ባለፈው የየካቲት ወር ውስጥ መጠኑ 200,000 ዶላር፣ 150,000 ዩሮ፣ 68,000 ፓውንድና 150,000 የሳውዲ ሪያል ከአገር ሊያስወጡ ሲሉ በቦሌ አየር ማረፊያ ቁጥጥር ስር የዋሉ 8 የውጪ ዜጋዎች በአቶ አባዱላ ገመዳና አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ አዛዥነት እንዲፈቱና ወደአገራቸው እንዲመለሱ ተደርጓል። ገንዘቡ ግን የት እንደደረሰ የሚታወቅ የለም። ወደመንግስት ካዚና ገቢ አልተደረገም። ወደፖሊስ ጣቢያ፣ ገቢዎች ወይም ወደ ብሔራዊ ባንክ አልሄደም።

ይህንን ወንጀል አስመልክተው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ ለጠቅላይ አቃቢ ህግ በፃፈው ደብዳቤ ላይ በአጠቃላይ መጠኑ ወደ 1.3 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነውን የውጭ አገራት ገንዘብ ከአገር ሊያወጡ ሲሉ የተያዙት እነ ሚስስ ካትሩን ባሻቢ (ሯንዳዊት)፣ ሚስ ማሪያ ላንዱ ሎጴስ (አንጎላዊት)፣ ሚ/ር አሰንዱ አብደላ (ኮሞሮስ)፣ ሚ/ር ሰይድ ቦይሮ (ኮሞሮስ)፣ ሚ/ር ሳንጋሪ ዲያክራጃ (ኮት ዲቮር)፣ ሚ/ር ዶኒስ በንሰን አኮዬ (ናይጀሪያዊ) እና ሚ/ር ዙመና ዱምዚያ (ማሊ) ላይ የተገኘው ወንጀል የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦርድ ባስቀመጠው መንገድ እንደሚፈታ ጠቅሷል። የገቢዎች ሚኒስቴር የሆነችው ወ/ሮ አዳነች አበቤ እነዚ

በህገወጥ መንገድ የተለያዩ የውጭ አገር ገንዘቦችን ከአገር ለማስወጣት ሲሉ የተያዙ ሰዎች ለህግ ቀርበው መዳኘት አለባቸው ብላ ተካራክራለች።

ከዚ በተጨማሪ ከከባድ የሙስና ወንጀሎች ጋር ተያይዘው ያለው ነገር ከኮንትራክተሮች ጋር የሚያያዝ ጉዳ ነው። የለውጥ መንግስት ብሎ እራሱን የሚጠራው ወደስልጣን መምጣቱን ተከትለው በርካታ የኢትዮጵያ ደረጃ አንድ ስራ ተቋራጮች ህገወጥ/ ሀሰተኛ ደረሰኝ በመጠቀምና ግብር በማጭበርበር ከፍተኛ ወንጀል ጋር ተያይዘው በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ፣ የታክስ እና ጉሙሩክ ወንጀሎች ምርመራ ዳይሬክቶሪት ምርመራ ተደርጎባቸው ክስ እንዲመሰረትባቸው ወደ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ወደሚመራው ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተመርተው ነበር።

ከነዚህም ተቋራጮች ውስጥ የማንኮድ፣ ተክለብርሃን አምባዬ፣ ሳትኮን፣ ሳንሻይን፣ ሱር ፣ አኪር፣ አፍሮ ፅዮን፣ ዮቴክ ፣ ሳንታማሪያ ኮንስትራክሽን እና ሌሎች ይገኙበታል። በዚ መሃል ጉዳዩ እንዲዘገይ የፈለገው ጠቅላይ አቃቤ ህግ ተጨማሪ ማጣራቶች እንዲደረጉ የሚገልጹ ደብዳቤዎችን ወደፌደራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ እየፃፈ፣ ከጎን ደግሞ ተቋራጮቹ በማህበራቸው አማካኝነት አቤቱታን እንዲያቀርቡ እየጠቀማቸው ክስ ቶሎ እንዳይመሰረትባቸው ጉዳዩን ማዘግየትን ተያያዘ። ለምን ካላችሁ፣ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ በጎን በአቶ አለማየሁ ከተማ አማካኝነት ከተቋራጮቹ ጋር በገንዘብ እየተደራደሩ ነበር ። አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ጉዳዩን የመሩ ቢሆኑም አብሮአዋቸው ግን ሌሎችም አሉ። በመጨረሻም ለፈፀሙት ለዚህ በሀሰተኛ ደረሰኝ መጠቀምና ግብር በማጭበርበር ወንጀል ክስ ሊመሰረትባቸው ጫፍ የደረሱ ባለሀብቶች ምንም ሌላ ማምለጫ





እንደሌላቸው በመገንዘብ እንደወንጀላቸው ክብደት የተቆረጠባቸውን ገንዘብ ሰጥተው ነፃ ለመውጣት ችሏል።

አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ለሙስና የሚያመቹ ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን በሌላም መልኩ ይዟል። አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ከጠቅላይ አቃቤ ህግ በተጨማሪ የፍትህ ተቋማት ካውንስል ዋና ሰብሳቢ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ አባልና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባል ናቸው። የፍትህ ተቋማትንም እንዳሻቸው የሚያደራጁት እኚህ ባለጊዜ ናቸው።

ሌላው ምሳሌ ጥርሳቸውን የነከሱበትን አንድን ባለሀብት አንዲህ አድርጎታል። ሰውዬው ያለምንም የፖለቲካ ውግንና ጥሮ ግረው ቱጃር መሆን የቻሉ ትውልደ ኤርትራዊ ናቸው። የሚኖሩትም በመዲናችን አዲስ አበባ ሲሆን፣ ስማቸው አቶ አለም ተፈራ ይባላል። በጎፋ ማዞሪያ የሚገኝ የነዳጅ ማደያ ባለቤት ናቸው። እኚን ሰው ከአንድ ወር በፊት ያለምንም ጥፋት የደህንነት አባላት በማታ ከመኖሪያ ቤታቸውይወስደዋቸውና በማረሚያ ቤት እየገረፉቸው ያሳድረዋቸዋል። እየገረፉትም ያሉትን የገንዘብ መጠን ካልሰጣቸው በስተቀር እንደማይለቁት ያስፈራሩታል። እኚህ ለፍተው አዳሪ የንግድ ሰውም የተባለውን 20 ሚሊዮን ብር በመስጠት ሊለቀቁ ችለዋል። ከተፈቱ በኋላም ምንም ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሄደው አቤት ቢሉም ሰሚ አጥተው ልባቸው እንደተሰበረ ወደቤታቸው ተመልሰዋል። እኚን ሰው ቀድሞ እይታው ውስጥ ያስገባው ባለግዜው አቶ አለማየሁ ከተማ ነው። አቶ አለማየሁ ከተማ ብሔረ ትግሬ የሆነ ሰው አይወድም። ምክንያቱ ደግሞ የአገራችን ቢሊየነሯ ባለሀብት ወ/ሮ አኪኮ ስዩም (የአርኪድ ግሩፕ ባለቤት) አንድ ጊዜ በዩጋንዳ አገር እያሉ በመጋጨታቸው ገርፏው ነበር አሉ።

ሌላውና ዋነኛው ጉዳይ ደግሞ በጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ስም እየተሰራ ያለ የፋይናንስ ወንጀል ነው። 'ከጉዲና ፋውንዴሽን የበጎ አድራጎት ድርጅት በተገኘ ገንዘብ ... ' ሲባል መስማታችሁ አልቀረም። ለምሳሌ ከአለማችን አሜሪካዊው ቱጃሩ ባለሀብት የተገኘው ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ በጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን ስም ሸሽቷል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ከውጪ አገራት በእርዳታ መልክ የተገኙና በመገናኛ ብዙኀን የሰማናቸው እነዚህ ሁሉ ገንዘብ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ባለመደረጋቸው አገሪቷ በውጪ ምንዛሬ እጥረት ቀውስ እየተጠናወተች ትገኛለች። ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን የሚተዳደረው በአቶ አለማየሁ ከተማ ባለቤት ወ/ሮ ሌንሳ ጉዲና ቱምሳ መሆኑ ይታወቃል። አሁን ግን በዚህ የበጎ አድራጎት ድርጅት ስም የአገሪቷን የፋይናስ ህግ መጣስ መልኩ የገንዘብ ዝውውርና ማሸሽ ስራ እየተከናወነ ስለሆነ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ባለቤት ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸውም ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ነገር ግን በቅርበት ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽንን እየመሩ ትገኛለች። የፋይናንስ አሰራር ጥሰቱ ደግሞ ህጋዊ በሚመስል መልኩ እንዲከናወን የሰነድ ማደራጀት ስራውን የሚሰራው የአቶ አለማየሁ ከተማ የቅርብ ዘመድ የሆነውና ለዚህ ለሙስና ወንጀል ሽፋናቸው ሺባል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ዲኤታ ሆኖ እንዲሰራ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሾመው ዶ/ር ኢዮብ የተባለ ሰው ነው።

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሆኖ እየሰራ ያለው አቶ አህመድ ሽዴ ይህ ሰው ስራዬ ውስጥ ጣልቃ እየገባ በማለት በተደጋጋሚ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቤት ቢልም ተስማምታችሁ መስራት እንዴት ያቅታቿል የሚል ምላሽ አግኝቷል።





አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ የአዲሱ የውስናው መረብ ካፖና በአዲሱ የመስናው መረብ ጊዜያት (አንድ አመት ወዲህ) ውስጥ የቀድሞ የህወሃት አስተዳደር ሙሰኞች ባለፉት 27 አመታት በጋራ ሊሰበስቡ ያልቻሉትን የስርቆት ገንዘብ ሊያከማቹ ችለዋል:: የአቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ታማኝ ጉዳይ ፈፃሚ አቶ ሰለሞን በላቸው ይባላል። አቶ ሰለሞን በላቸው .ጋር ይዛመዳል:: አቶ ሰለሞን እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ የISUZU መኪና ረዳት ሆኖ ሲሰራ ቆይቷል። ከዚያ ወዲህ የአቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ደላላ ሆኖ የሰበታ ከተማን መሬት በገፍ ቸብችቦ FSR የገዛ ሰው ነው። በሰበታ ስንቶቹን የኦሮሞ አርሶአደሮችን ያፈናቀለና ያስለቀሰ ግለሰብ ነው። አቶ ብርሃኑ ፀጋዬና አቶ ሰለሞን በላቸው በሰበታ ከተማ አስተዳደር የሸጠዋቸው መሬቶች ቁጥር ስፍር የላቸውም። ይህንን በሚቀጥለው እትማችን በሰፊው እንዳስሳለን። ከዛን ግዜ ጀምሮም ከአቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ህጋዊ ውክልና ወስደው አለምገና የሚገኘውን G+2 መኖሪያ ቤቱን በማከራየት የሚያስተዳድርለት ይህ አቶ ሰለሞን የተባለ ደላላ ነው። የካቲት 2011 ዓ.ም ደግሞ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ በ23 ሚሊዮን ብር በንፋስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ልዩ ቦታው ቫቲካን ኤምባሲ የሚገኝን አንድ G+2 መኖሪያ ቤት በአቶ ሰለሞን በላቸው ስም ገዝቷል። አሁን በያዝነው ወር የነበረበትን የG+2 መኖሪያ ቤቱን አፍርሰው ሌላ የተሻለ ዘመናዊ ህንፃ እየገነቡ ይገኛሉ ። ከዚህ በተጨማሪ በግብር ማጭበርበር ወንጀል ሊከሰስ የነበረው አቶ ድንቁ ደያሳ ለአቶ ብርሃኑ ፀጋዬ በዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ ሶስት የመኖሪያቤት ቪላዎችን ስለገዛለት ክስ እንደማይመሰረትበት ቃል ተገብቶለታል። ሰሞኑን አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ክሱ በተቃራኒ የቆሙትንና የሙስና ድርጊቶቹን ያወቁበትን የመንግሰት ሹመኞች

እያሳደደ በመንግስት በተመሩት መሬት ላይ የሰሩትን መኖሪያቤት ከየት አመጣችሁ እያለ ሊያስፈራራቸው እየሞከረ ይገኛል።

ከላይ ከተጠቀሱ ጉዳዮች የምንረዳው አዲሱ የሙስና መረብ በአንድ አመት ውስጥ ይህንን ያከል በተቀናጀና ተራቀቀ መረብ ውስጥ መስፋፋቱን ነው። አዲሱ የሙስና መረብ ከመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት እስከ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር፤ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን እስከ አዲስ አበባና ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽኖች፤ ከጠቅላይ አቃቤ ህግ እስከ ፍትህ ሚኒስቴር፤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት እስከ ቱጃር ግለሰቦች፤ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እስከ ገቢዎች ሚኒስቴር በጥልፍልፎች የተዘረጋ ነው። የሙስና መረቡን በዋናነት ለሚመሩ ባለስልጣናትም በአሜሪካና ካናዳ የቅንጦት መኖሪያቤቶች እየተገዙላቸው ነው። ከሚታሰበው በላይ ገንዘብ በዚ አጭር ግዜ ውስጥ ወደውጪ እንዲሸሽ ተደርጓል። በአጭሩ ወያኔ በ27 አመታት ከዘረፈችው ገንዘብ በላይ በአንድ አመት ውስጥ በአዲሱ የዶ/ር አብይ አህመድ አስተዳደር ሰዎች ተዘርፏል። እየተዘረፈም ይገኛል። ሰዎቹ 'የኛ መንግስት የለውጥ መንግስት ነው' የሚሉት፣ 'ሙሰኛን በቀጥታ ሌባ ነው ማለት ያለብን' ያሉት አሁን ላይ በምስኪኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተፈዘ ነው የሚመስለው። አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ እንዳለው ... ለውጥ የተባለው አገሪቷ ውስጥ በስፋት የሚስተዋለውንና ለድህነታችን አንዱ ዋነኛ መንስዔ የሆነውን መስናን በተቻለ መጠን ማጥፋት ወይም መቀነስ ነው ? ወይስ ባለፉት 27 አመታት የነበሩትን ሙሰኞች በሌላ አዲስ ሙሰኞች መተካት? መልሱን ለናንተው ትቸዋለሁ።





## በደህንነት ካሜራው እየታደኑ የሚገኙ

ከአንድ አመት በፊት ገዢው ድርጅት ኢህአደግ ስርነቀል መንግስታዊ ለውጦችን አካሂጃለሁ ቢልም፣ ዛሬ እንደቀደመው የህወሃት የበላይነት አስተዳደር ዘመን ዜጎች በሚከተሉት የፖለቲካ አመለካከታትና ማንነታቸው ምክንያት በፀጥታ ሀይሎች እየታደኑ ለማስፈራሪያ እስራትና ግድያ እንዲሁም ለንብረት መቀማት እየተዳረጉ ይገኛሉ። በለውጡ ማግስት እየተካሄደ የሚገኘው አፈና በዋናነት ኦሮሞ የሆኑ ግለሰቦች ላይ ያተኮረ ቢሆንም በብሔር ትግሬ የሆኑና ጥቂት የማንነት ጥያቄን የሚያነሱና ባለሀብት የደቡብ ክልል ተወላጆችም ሰለባ ከመሆን አልተረፉም። በመዲናችን አዲስ አበባ በርካታ ባለሀብቶችን ተገደው ለፍተው ያፈሩትን ገንዘባቸውን ለፀጥታ ሀይሎች እየሰጡ ነው። በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ቀደም ባለ ጊዜ ለኦነግ የተደረጉትን የአቀባበል ዝግጅት ያስተባበሩ በሙሉ ተለቅመው እየታሰሩነው። በሀረርጌ ባሌ አርሲ ሸዋ በተለየ መልኩ ደግሞ በኮማንድ ፖስት በሚተዳደሩት በወለጋና ጉጂ የተገደሉና ንብረታቸውን የተቀሙም ንፁሃን በመቶዎች ይቆጠራሉ።


የፀጥታው ዘርፍ በተለይም የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ሰራተኞች በተለየ መንገድ እየተከታተሏቸው የሚገኙ ግለሰቦች በርካቶች ናቸው። እነዚህ የደህንነት መስሪያቤት ሰራተኞች ኢላማ የሆኑት ግለሰቦች ህዝቡን ሊያሳምፁ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ የፖለቲካ አካሄድ መንገድ በተቃራኒ የቆሙና ከአቶ ለማ መገርሳ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብሎ የተለዩ ግለሰቦች ናቸው።

ከነዚህ ዕላማ ከተደረጉ ግለሰቦች ውስጥ በተዕፅኖ ፈጣሪነቱና በፖለቲካዊ ስትራተጂው ፊርጥ የሆነው አቶ ጃዋር ሞሐመድ ይገኝበታል። አቶ ጃዋር ሞሐመድ ሁሉንም የኦሮሚያ ወጣቶችን አስተባበሮ በማታገል የህወሃትን የጭቆና አረንቋ ከላያችን ላይ ያነሳ ከኦሮሞ ህዝብ የተገኘ ብርቅዬ ልጅ ነው ማለት ይቻላል። ጃዋር ህወሃትን የታገለውና ያታገለው እንደግለሰብና እንደተቋም ነበር። እንደግለሰብ ፌስቡክን በመጠቀምና እንደተቋም OMNን በማቋቋምና በመምራት ህወሃትን ለአመታት ተዋግተዋል። ዶ/ር አብይ አህመድ ጃዋር ላይ ጥርሳቸውን የነከሱትጃዋር ቃል በቃልም ባይሆን "የኦህደድ/ ኦዲፒ ሊቀመንበር አቶ ለማ መገርሳ እንጂ ዶ/ር አብይ አህመድ መሆን የለበትም። የኦህደድ/ ኦዲፒ ከሆነ በመቀጠል የኢህአደግ ሊቀመንበር በመሆን ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ በማገልገል ስለሆነ እኔ ዶ/ር አብይን አላምነውም። ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው የኦሮሞ ህዝብን ጥያቄ ሊመልስ የሚችለው አቶ ለማ መገርሳ ነው።" ያለ ቀን ነበር። አሁን ላይ አቶ ጃዋር ሞሐመድ የዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ እንደማይመልስ ስለተረዳና ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ለኦሮሞ ህዝብ ቃል የገባላቸውን ጥያቄዎች ወደጎን በማለት ከተቃራኒ ጎራ ፖለቲከኞች ጋር ስለተሰለፈ፣ ጃዋር ህዝቡን ያሳምፃል ተብሎ ተሰግቷል። ከጃዋር ጋር ሆኖ ሲታገል የነበረው የፕሮፌሰር ህዝቅኤል ገቢሳም የዶ/ር አብይ አህመድ መንገድ ትክክል አይደለም የሚል አቋም ስለያዘ ብቻ ሌላኛው ታዳኝ ለመሆን ችሏል። ከሆነ ጃዋርም ሆነ ህዝቅኤል ተማረው አገር ጥሎ እንዲወጡ ጫና እየተደረገባቸው ይገኛል። ለዚህምበህዝብስም ገንዘብ በልታቹሃል የሚል የውሸት ወጥመድ ተዘጋጅቶላቸዋል። በፍጥነት መረጃን በማጋራቱ ምክንያት ፌስቡክ ኩባኒያ ከድረገፁ አግደውት የሚያውቀው





ከባድ ሚዛኑ አክቲቬስት ጃዋር ሞሐመድ ለምን ዝምታን መረጠ በማለት በተደጋጋሚ እየጠየቃችሁ የምትገኙ አድናቂዎቹና ባላንጣዎቹ በሙሉ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ አጥጋቢ ምላሽን እንዳገኛችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።



ከኦነግና ኦህደድ/ ኦዲፒ እርቅ ጉዳይ ጋር ተያይዘው እንደ ሶስተኛ ወገን አስታራቂ ሆነው ሁለቱንም አካላት ያስማማል ብለው ያሰቡትን የስምምነት ውል ያረቀቁትም በፀጥታ ሀይሉ ጥርስ ተነኮሶባቸዋል። ሁለቱንም አካላት ለማስታረቅ ሲባል በምዕራብ ዞን የኦነግ ጦር የሚመራውን ጃል ማሮ (ኩምሳ ድሪባ)ን ያለበት ቦታ ድረስ ሄደው ያነጋገሩት ባለሀብቷ ወይዘሮ ማኪያ፣ በሪልስቴትና ሌሎች የኮንስትራክሽን ዘርፎች ላይ የተሰማራው ዶክተር ኢንጂኔር መሰለ ሀይሌና በህወሃት ታፍኖ 15 አመታትን በእስር ቤት እየተሰቃየ ያሳለፈው ኢንጂኔር መስፍን አበበ ናቸው። እነዚ ሶስቱ ግለሰቦች ለምን እንደዚ አይነት የስምምነት ውል አዘጋጃችሁ ተብሎ ማስፈራሪያና እንግልት እየደረሰባቸው ነው። ዶክተር ኢንጂኔር መሰለ ሀይሌ ከለገ ጣፎ ከተማ አስተዳደር ለሪልስቴት ኢንቨስትመንት የወሰዳቸው

መሬቶች በመንግስት ሊወሰድባቸው መሆኑ ተሰምተዋል። ኢንጂነር መስፈን አበበ የኦነግና ኦህደድ/ ኦዲፒን እርቅ ማን እንዳደናቀፈ እንዳይናገር ማስፈራሪያ ደርሶበት አሁንም ክትትል እየተደረገበት ይገኛል።

የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ መስራችና የቦርድ አባል የነበሩት ባለሀብቱ አቶ ሀይሌ ገብሬ የተባሉ አዛውንት ኦነግና ኦህደድን ለማስታረቅ ባደረጉት ተሳትፎ ምክንያት ለማስፈራሪያና እንግልት ተዳርጓል።

አንዳንድ ቡና ላኪዎችም እንደዛዉ በአቶ አለማየሁ ከተማ ትዕዛዝ እየታደኑይገኙሉ፡፡ ከአቶ ለማ መገርሳ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በአገር ውስጥ ደህንነት ሹመኞች እየታደኑ ያሉት ብዙ ናቸው። እነዚህ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ሹማምንቶች እየታደኑ ተብለው ስማቸው ከላይ የተዘረዘረ ግለሰቦች ጥቂቶቹ ናቸው። በአጠቃላይ ከአቶ ለማ መገርሳ ጋር ግንኙትና ቅርበት አላቸው ተብሎ የተወሰዱ ሰዎች በሙሉ በቅርበት እየተሰለሉና እየታደኑይገኛሉ።

አቶ ሽመልስ አብዲሳ ወደኦሮሚያ ክልል አመራርነት እንዲሁም አቶ አዲሱ አረጋ ወደ ኦህደድ/ ኦዲፒ ፅህፈትቤት ሃላፊነት ከመጡ ጊዜ ጀምረው ከሃላፊነታቸው የተነሱት የክልሉ አመራሮች በሙሉ በደህንነት ካሜራ እይታ ውስጥ በመግባት ውሎና አዳራቸው በሙሉ እየተሰለለ ይገኛል።

የፀጥታ ሀይሉ ተግባር ዜጎችን ከጥቃት አገርን ደግሞ ከጠላት መጠበቅ ሆነው እያለ ንፁሃን ዜጎችን ወደማደን በማተኮሩ አገርም አደጋ ላይ ወድቀው ዜጎችም ለመልከ ብዙ የወንጀል ጥቃቶች እየተጋለጡ ይገኛሉ። መንግስት እነዚህን እንደ ድክመቶቹ ተቀብለው ካላስተካከላቸው በስተቀር ለውጥ የተባለው ወደነውጥ እንዳይለወጥ ስጋቴን ከወዲህው ለመግለፅ እወዳለሁ።



የተጠለፈ የህዝብ ትግል

## የፌስቡክ ሰራዊቶች

የዶ/ር አብይ አህመድ 2210 የሚሆኑትን ግለሰቦች በፌስቡክ ላይ ከአገር ውስጥና ውጪ ቀጥሮ እያሰራ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ የፌስቡክ ሰራዊቶችም የተደራጁት ህዝቡ እንዳያውቅ ተደርገው ነው። የፌስቡክ ሰራዊቶቹ ምንም ትዊተርን ጭምረው ሌሎች የማህበራዊ ትስስር ድረገፆችን የሚጠቀሙ ቢሆንም በዋነኛነት ግን የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመወጣት ሲባል የሚጠቀሙት ፌስቡክን ነው። ከሌሎች የማህበራዊ ትስስር ድረገፆች ውስጥ ፌስቡክ የተመረጠበት ምክንያት ሁሉም በሚቻል መልኩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግላቸው ጉዳይና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለመከታተል ፌስቡክን ስለሚመርጡ ነው። ከአንድ አመት በፊት አቶ ጃዋር ሞሐመድ የሚያሰራጨውን መልዕክት ለመከታተል እንኳ ስንቶቹ የፌስቡክ አካውንትን እንደከፈቱ አይካድም።

ፌስቡክ የአገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮች በሰፋት የሚዳሰስበት ከመሆኑ ባለፈ ህዝቡን ለማሳመፅም ሆነ ድጋፉን ለማግኘት ዋነኛ መሳሪያ ነው። አሁን አሁን ፌስቡክን መዝጋቱም የህዝቡን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንደማፈን ስለሚቆጠር ቀላል አይሆንም። ስለዚ ይህንን የተረዳው የዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት ፌስቡክን ከመዝጋት ይልቅ ግለሰቦችን (ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ጭምር) በገንዘብ ሀይል የራስ አድርጎአቸውና አደራጅቶአቸው ከባለፉት ስምንት ወራት ጀምሮ እየተጠቀመባቸው ይገኛል። እነዚ የፌስቡክ ሰራዊቶች በተፈለገ ግዜና ቦታም የዶር አብይ አህመድን አስተዳደር በመደገፍ በተለያዩ የመንግስት ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋሉ። በፌስቡክ ላይ የሚሰሩት ዋነኛ

ነገር ዶ/ር አብይ አህመድ የሆነ ጉዳይን አስመልክተው ፍንጭ በሚሰጡበት ጊዜ ያንን እንደአቅጣጫ በመውሰድ ሀሳብ አዳብሮ ህዝቡን ለማሳመን መሞከር ወይም ጫና ማድረግ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዛፍ ትከሉ ካሉ እርሳቸውን ተከትለው መዘገብና የዛፍ ተከላውን ዘመቻ በማራገብ ለፖለቲካዊ ፋይዳዎች እንድውል መልዕክቶችን ማሰራጨት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጪው ምርጫ መራዘም እንዳለበት ፍንጭ ሲሰጡ እርሳቸውን ተከትለው ምርጫው ቢራዘም የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ላይ የውሸት ማሳመኛ አፈላልጎ ህዝቡን ለማሳመን ይሞክራሉ። የፌስቡክ ሰራዊቶች ይህንን ሲያደርጉ እርስበርሳቸው ይናበባሉ። በተሰጣቸው አቅጣጫ መሰረት አንዱ የፌስቡክ ሰራዊት የፃፈውን መልዕክት በመረቡ ውስጥ ያሉ ሌሎች የፌስቡክ ሰራዊቶች ለሌሎች ያጋራሉ (ሼር ወይም ትዊት ያደርጋሉ)። የጠቅላይ ሚኒስትሩን የሚቃወም ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰብከተገኘ ደግሞ አንድ ላይ ይዘምቱበታል። ሀሳቡን ለማጣጣልና ለማንኳሰስ ይረባረባሉ። ለምሳሌ ዶክተር ኢታና ሀብቴ ጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብይ አህመድ ለኦሮሞ ብሔርተኝነት ካምፕ አዲስ ነው በማለቱ እነዚ የፌስቡክ ሰራዊቶች እንዴት እንደዘመቱበት አይተናል። እነዚ ስራቸው ሁሉ የአምበጣ መንጋ የሚመስለው የፌስቡክ ላይ ተቀጣሪዎቹ የተደረጁበት የደረጃ እርከን አላቸው። የተሻለ የትምህርት ደረጃ የፖለቲካ እውቀትና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑት የመጀመሪያው ደረጃ ውስጥ ይገኛሉ ። ባለስልጣን የሆኑትም ሆኑ ገለልተኛ የሚመስሉ አሉበት። እነዚ ደግሞ በእውቀትም ሆነ ተፅዕኖ ፈጣሪነት ያነሱ ናቸው ብለዉ ያሰቡአቸውን ከስራቸው አደራጅቷል። ለምሳሌ ያክል ከነዚ የፌስ ሰራዊቶች ውስጥ እነ ዶክተር ብርሃኑ መገርሳ፣ አቶ ዮናታን ተስፋዬ፣ ዶክተር ብርሃነመስቀል





አበበ፣ አቶ ኢያስፔድ ተስፋዬ፣ ወ/ርት ብሌን መስፍን፣ አቶ ስዩም ተሾመ (በቅርቡ የተቀላቀለ) ፣ ዶክተር ደረጀ ገረፋ አቶ ደረጀ በጊና ሌሎች 2110 የሚሆኑ ግለሰቦች ናቸው። የፌስቡክ አከፋፈላቸውን አስመልክተው በውጭ አገር የሚገኙት የፌስቡክ ተቀጣሪዎች በሙሉ የሚከላቸው በየወሩ 1,000 ዶላር ሲሆን ገንዘቡም በየወሩ አንዳንዴ በየሁለት ወሩ ያስመዘገቡት የባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ላይ ገቢ ይደረግላቸዋል። በአገር ውስጥ የሚገኙት ደግሞ ገንዘቡን የሚቀበሉት በዋና አደራጃቸው በኩል በካሽ ነው። በወር ውስጥም እንደግልሰቦቹ ከ10,000 ብር እስከ 20,000 ብር ያገኛሉ።

## የውጭ ምንዛሪው እጥረት ጉዳይ

አገራችን ኢትዮጵያ በለፉት በርካታ አመታት በውጪ ምንዛሪ እጥረት ተጠቅታ እንደቆየች የብሔራዊ ባንክ ሰነዶች ያመለክታሉ ። የገቢ ንግድን በታቀደውና በሚፈለገው መልክ ለማስኬድ አገሪቷ ያላት የውጪ ምንዛሪ ክምችት ዋነኛው ነው ። አነስተኛ የውጪ ምንዛሪ ክምችት ያላቸው አገራት ከዚህ ችግር ለመውጣት ሲባል የተለያዩ መፍትሄዎችን ይጠቀማሉ። ወጪ ንግድን ማበረታታትና ማሳደግ፣ ገቢ ንግዶች ላይ እንደየዘርፉ ጫና ቀረጥና ኮታ መጣል፣ ከውጭ አገራት ብድርና እርዳታን ማፈላለግ ይገኙበታል ። አገሪቷን የተቀበልኩት ከባዶ ካዝና ጋር ነው የምለው የዶክተር አብይ አህመድ መንግስትም አገሪቷ ከገባችበት የኢኮኖሚ ቀውሶች እንደሚያወጣት ቃል ገብተው ነበር። የዛኔ የነበረው የውጪ ምንዛሪ ክምችትም በጣም አንስተኛ በመሆኑ የጥቁር ገበያው ደርቶ፣ በመዘዙም የሸቀጦች ዋጋ ለመናር ችሎ ነበር ። ይህንን የውጪ ምንዛሬ ችግር ለመፍታት የተንቀሳቀሰው የዶክተር አብይ መንግስትም በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር በቂ የሆነ የውጪ ምንዛሬ ከዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ፣ ሳውዲና ከሌሎች አገሮች በእርዳታና ብድር መልክ እንዳገኘ ነግሮን ነበር ። ነገር ግን ዛሬም የብሔራዊ ባንክ ገዢው በተደጋጋሚ የውጪ ምንዛሪ እጥረት እያቃወሰን ነው እያሉ ይገኛሉ ። ችግሩ የሚመነጨው አንደኛ፡- ከእርዳታ መልክ የተገኙት የውጪ ምንዛሪ በሙሉ ወደ ብሔራዊ ባንክ ገቢ አልተደረጉም። በብሔራዊ ባንክ የሚገኘው አጠቃላይ የውጪ ምንዛሪ ክምችት ጭራሹኑ በመጠኑ በእርዳታ ተገኘ ከተባለው ያንሳል። የመንግስት ቡድን ለማናውቀው ግላዊ ምክንያት አስቀምጦታል ወይም አሸሽቶታል





ማለት ነው ። ሁለተኛው፡- በብሔራዊ ባንክ የሚገኘው የውጪ ምንዛሪም እየተፈቀደ ያለው ለጥቂት ለመንግስት ቅርበት ላላቸው ግለሰቦች ብቻ ነው። እነዚ ግለሰቦች ደግሞ በተደጋጋሚ ለማስፈቀድ ከሚገባው መጠን በላይ እያከማቹና ወደውጭ አገራት እያሸሹ ነው ። ለምሳሌ ያክል የዶክተር አብይ አህመድ ባለጊዜዎች የሆኑት አቶ አለማየሁ ከተማና አቶ ድንቁ ደያሳ በውጪ ጉዞ ስም በየሳምንቱ 20,000 ዶላር ከባንኮች እየተቀበሉ ይገኛሉ ። ለሌላው ግለሰብ ለውጪ ጉዞ ተብለው የሚፈቀደው 200 ዶላር መሆኑ ይታወቃል ። እነዚ ባለጊዜዎቹ ግለሰቦች የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እንዲፈቀድላቸው ትዕዛዝ የሚሰጡት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዝዳንት አቶ ባጫ ጊናና የብሔራዊ ባንክ ቦርድ አባልና ባለብዙ ስልጣኖች ባለቤት የሆኑት አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ናቸው ። ለዚው ትስስሩ ለአቶ ባጫ ጊና በልጁ ስም ከአሜሪካን አገር ደንቨር ኮሎራዶ በ500,000 ዶላር መኖሪያ ቤት በአቶ አለማየሁ ከተማ በኩል ተገዝቶለታል።

## የዜጎች መፈናቀል ቀውስ

2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የዜጎች አገር ውስጥ መፈናቀል (Internal Displacement) የተከሰተበት አመት ከመሆኑ አልፈው በአለም የመጀመሪያው ደረጃ ይዘዋል ። እንደ UNICEF እና IOM ሪፖርት እስከ ነሐሴ 2010 ዓ.ም ብቻ 2.8 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች ከሚኖሩበት ክልል የተፈናቀሉ ሲሆን፣ ለዜጎቹ መፈናቀልም ትልቁ መንስዔ በመንግሥት ባለስልጣናት የተቀነባበረ የእስርበርስ ግጭት ነው ተብሏል። ለምሳሌ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተፈናቀሉት ከ200,000 በላይ ዜጎች፣ የመንግስት የፀጥታ ሀይሎች የኦነግን ስም ለማጥፋት ሲባል እራሳቸው የጉሙዝ ባለስልጣናትን መንገድ ላይ ጠብቀው ተኩሰው በመግደል በኦነግ በማላከካቸው ምክንያት ነው። በከሚሴና ሰሜን ሸዋ የሆነውም ግጭት በተመሳሳይ የመንግስት ሴራ ነው።

በሪፖርቱ መሰረትም 1.6 ሚሊዮን ኦሮሞዎች ፣ 900 ሺ ገደኦዎች ፣ 200 ሺ ሶማሊዎች ፣ 60 ሺ ትግሬዎች፣ 25 ሺ አማራዎችና 15 ሺ ሌሎች ብሔሮች ከሚኖሩበት ከሶማሌ ኦሮሚያ አማራና ቤኒሻንጉል ክልሎች ተፈናቅለዋል ። ይህም አገር ውስጥ የተፈናቀሉ የህዝብ ቁጥር በፐርሰንት ስገለፅ ፦

ኦሮሞ - 57.15 %

ጌደኦ - 32.14 %

ሶማሌ - 7.14 %

ትግሬ - 2.14 %

አማራ - 0.89 %





ሌሎች - 0.53 %

እንደ US AID ሪፖርት አሁን በኢትዮጵያ የሚገኙ 7.9 ሚሊዮን ዜጎች አስቸኳይየምግብ እርዳታን ይሻሉ። እነዚ አስቸኳይ የምግብ እርዳታን የሚሹ ዘጎችም በቅድመ-ተከተል በኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ክልልና በተለያዩ የስደተኞች ካምፕ (አብዛኞቹ ከደቡብ ሱዳን) ይገኛሉ። ከሁሉም ደግሞ በሶማሌ ክልል ያሉት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስላሉ ቅድምያተሰጥቷቸዋል። ሶማሌዎች ኦሮሞውችጌደኦዎች የደቡብ ሱዳን ስደተኞች በቅድመተከተል ችግር ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ፡፡ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ ወደስልጣን ከመጡ ወዲህ የነበሩ የአገር ውስጥ መፈናቀሎች ሰው ሰራሽ (artificial) ከመሆናቸውም በላይ በአዲሶቹ የፀጥታው ዘርፍ ሹመኞች ለመፈፀማቸው ብዙ ማሳያዎች አሉ። አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት በነበሩበት ግዜ እርሳቸውን ለማሳጣት ሲባል ገንዘብ መድበውና ፈፃሚ ግለሰቦችን መልምለው በማደራጀት ዜጎች ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች በተለይም በጉጂ እንዲፈናቀሉ ሲደረግ ቆይተዋል። አቀናባሪዎች ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ የተሾሙ የመረጃና ደህንነት ፅህፈት ቤት ሰራተኞች ነበሩ ። በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞንና ቡራዩ ከተማ የነበረው የዜጎች መፈናቀል ታቅደው የተፈፀሙበት ሌላው ግቡ *ኦነግን የማኮላሸት ሴራ* የሚለው ርዕስ ስር እንደዳሰስኩት የኦነግን ስም ለማጠልሸት ጭምር ነበር። ከዚ በፊት ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የዜጎች ከሚኖሩበት ቀዬ መፈናቀል መቼ እንደሚያበቃ ተጠይቀው ለአንድ አመት ያክል ሊቀጥል እንደምችል ተናግሮ ነበር። ለምን የዶክተር አብይ አስተዳደር የዜጎች መፈናቀልን ፈለገ ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሆኑ

ጉዳዮችን በመፅሐፉ ውስጥ በተለያዩ ርዕሶች ስር ተብራርቶ ያገኙታል ። ይገኛሉ።

ምንም የሰላም ሚኒስቴር ከቀዬአቸው ከተፈናቀሉ ዜጎች ውስጥ አብዛኞቹ ወደቀድሞ ቀዬአቸውተመልሰዋል ቢልም አሁንም እነዚ ጠያቂ ያጡ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ዜጎች ከቀድሞ መኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የድህነት ፅዋን እየተጎነጩ በአገራቸውም በኢትዮጵያዊ ወንድሞቻቸውም እየተማረሩ ይገኛሉ። በመንግስት እንዳይማረሩማ ሲጀምር መንግስት ባለበት አገር አይፈናቀሉም ነበር። እነሱ መንግስት የለም ብለው ደምድመዋል። መንግስት ነው እንጂ አልፉታ ያላቸው። መንግስት ለፖለቲካ ንግዱ ሲል አይኑን በጨው አጥበው እራሱ እንዲፈናቀሉ ካደረጋቸው ምስኪኖች ጋር እየዞረ ፎቶ ይነሳል። መንግስት ህገመንግስቱ ላይ በተቀመጠው መልከ የዜጎችን ተዘዋውሮ የመኖር የመስራትና ሀብት የማካበት መብትን ማስከበር በብቸኝነት የእርሱ ስልጣን ሆኖ እያለ ከተፈናቃይ ዜጎች ጋር ፎቶ እየተነሳ የፎቶግራፍ ፖለቲካን ያራምዳል።





## በአፋን ኦሮሞ የመገልገል ጥያቄ?

የኦሮሞ ህዝብና ሌሎች የአገራችን ህዝቦች የብሔር ጭቆናን አጥብቀው በመቃወማቸውና የተወሰኑትም ወደ ትጥቅ ትግል በመሸጋገራቸው ጥያቄዎቻቸው በአንፃራዊነት ተመልሶላቸው ከነዚህም ውስጥ ባለፉት አመታት በጭቆና ቀንበር ስር ወድቀው የአማርኛ ቋንቋን ተገደው ሲማሩትና ሲገለገሉበት የነበሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች በራሳቸው ቋንቋ የመማር ማስተማርና እንደ የመንግስት የስራ ቋንቋ የመገልገል መብታቸው ተጠብቆላቸው አይተነዋል። ነገር ግን አሁንም በአገራችን የብሔር ጭቆና የለም ማለት አይቻልም። ምክንያቱንም በአገራችን የሚታየውን የህዝቦች የቋንቋ እኩልነት መመልከት እንችላለን።

የቋንቋ እኩልነት ጥያቄን እንደማሳያ የወሰድኩት የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋን አስመልክተው ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ስላሉት ነው። እነዚህም ለአመታት ሲጠየቁ የከረሙት ጥያቄዎች፡- አፋን ኦሮሞን የአዲስ አበባ (ፊንፊኔ) ከተማ አስተዳደር እና የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የማድረግ የሙብት ጥያቄዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝቦች በሚቺሉት ቋንቋ ከመንግስት አገልግሎት ሰጪ መስሪያቤቶች አገልግሎትን ማግኘት ካልቻሉ በንጉሱና ደርግ ዘመን ሲታገሉት የነበረው የብሔር ጭቆና አሁንም አልቀረም ማለት ነው።

አንድ ሰው ተወልዶ ባደገበት በአያት ቅድመ አያቶቹ ቀዬ በራሱ ቋንቋ ካልተገለገለ የብሔር ጭቆና ስር እንደሆነ ከዚህ በላይ ማስረጃ የለም። ዛሬም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ዋና ከተማ በሆነችውና የኦሮሞ ህዝብ የባህል ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ማዕከል በሆነችው ፊንፊኔ ከተማ፣ በአፋን

ኦሮሞ ለህዝቡ አገልግሎትን የሚሰጥ አንድም የከተማ አስተዳደሩ መስሪያቤት የለም። ሁሉም የከተማ አስተዳደሩ አገልግሎት ሰጪ መስሪያቤቶች ለከተማዋ ነዋሪዎች አገልግሎትን የሚሰጡት በአንድ ቋንቋ ብቻ ነው። በከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ልትገለገል የሚትችለው በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ነው። የአማርኛ ቋንቋን የማያውቅ ነዋሪ በከተማ አስተዳደሩ ደረጃ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት አያገኝም ማለት ነው። ወይ ደግሞ ከሌሎች ነዋሪዎች እኩል አገልግሎት ለማግኘት ይቸገራል ማለት ነው ። እያወራሁ ያለሁት የመንግስት አገልግሎትን ስለማግኘት ነው።

የከተማ አስተዳደሩ ለነዋሪዎቹ የሚሰጠው አገልግሎት በአማርኛ ብቻ ስለሆነ የከተማዋ ነዋሪ ሆነህ እያለ የአፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ፣ ሶማሊኛ ወይም ጉራግኛ ተናጋሪ ከሆንክ አማርኛ ቋንቋ ከሚችሉ እኩል አገልግሎት የማግኘት መብት የለህም ማለት ነው ። ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እኩል በከተማ አስተዳደሩ ተቀጥረህ ህዝብን የማገልገል መብት ለብዙዎቹ ቅንጦት ሊመስል ይችላል። ነገር ግን እኩል የስራ ዕድልን የማግኘት መብት ጉዳይ ነው። እኩል ህዝቡን የማገልገል ሀላፊነትን የመወጣት ጉዳይ ጭምር ነው። የኦሮሞ ህዝብ የኦሮሚያ እምብርት ብሎ በመጠራት ፊንፊኔ በራሱ ቋንቋ የመንግስት አገልግሎትን ማግኘት፣ እንዲሁም በራሱ ቋንቋ ሌሎች ወገኖቹን ማገልገል ይፈልጋል። የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በከተማዋ የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦችም በቋንቋቸው የሚሰጥን የመንግስት አገልግሎት ማግኘት የመብት ጉዳይ ነው።

ቋንቋን አስመልክተው ሁለተኛው የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ አፋን ኦሮሞ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ ነው። አሁን





ያለውየፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ አማርኛ ብቻ ነው። እዚህ ጋ ለምንና እንዴት አማርኛ ቋንቋ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ሆነ የሚለው ላይ ጊዜ መፍጀት አያስፈልግም። አማርኛ ቋንቋ ብቸኛው የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የሆነው በታሪክ አጋጣሚ ነው ብሎ ማለፉ ከበቂ በላይ ነው። እዚህ ጋ የተነሳው ጉዳይ አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ለማድረግ ስለተጠየቀው ነው።

ባለፉት የኢህአዴግ አስተዳደር ዘመን የኦሮሞ ህዝብ ባደረጋቸው ህዝባዊ ትግሎች ውስጥ አፋን ኦሮሞ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ እንዲሆን በተደጋጋሚና በሠላማዊ መንገድ ሲጠይቅ ከርሟል ። አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ማድረግ ማለት አሁን በብቸኝነት የፌደራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ እያገለገለ ያለውን አማርኛን በመተው በአፋን ኦሮሞ መተካት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። የተባለው ወይም እየተባለ ያለው አፋን ኦሮሞ ከአመርኛ ቋንቋ በተጨማሪ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ይሁንልን ነው። አማርኛ ቋንቋ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ እንዳልሆነም የማያውቁ በርካቶች ናቸው።

አንዳንዶች እያወቁም ይሁን ሳያውቁ አፋን ኦሮሞ የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ እንድሆን መጠየቅ ዘረኝነት መሆኑንና ለአገር አንድነት አደጋ መሆኑን ለማስረዳት ሲጋጋጡ ታዝበናል። በነሱ ስሌት በራስ ቋንቋ መጠቀም ዘረኝነት ስሆን በነሱ ቋንቋ መጠቀም ደግሞ የአገር አንድነት ነው። ይህ በደፈናው የኦሮሞ ህዝብ በራሱ ቋንቋ መገልገልና ማገልገል የለበትም እንደማለት ነው። ዘረኝነት የራሴን ቋንቋ ላሳድግ ማለቱ ሳይሆን የራስን ቋንቋ ማሳደግ የለብህም የሚለው ነው።

ከሁለት አመት በፊት የነበረው የኦሮሞ ህዝብ ትግል ወደ ድል በመቃረቡ ስልጣን ከእጁ እያፈተለከ መሆኑን የተረዳው የየዛኔው የመንግስት አስተዳደር ይህንን የኦሮሞ ህዝብን ጥያቄ ለመመለስ ፍላጎት አሳይተው ነበር። ምንም ህዝቡ ጥያቄው እንዲመለስለት ቢፈልግም የጀመረው የትግል ምዕራፍ ሲቋጭ በተሻለ መልኩ ከሌሎች ጥያቄዎች ጭምር አንድ ላይ ይመለሳል በማለት መንግስትን ያሳየውን ፍላጎት ወደ ጎን ብሎ የጀመረውን የትግል ምዕራፍ ቀጥሏል፤እድሉም ባክነው ቀረ ።

ከትግሉ በኋላ ወደ ዋነኛ ስልጣን የመጣው ኦህደድ / ኦዲፒ ከሌሎች ህዝባዊ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች በተጨማሪ አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ መንግስት የስራ ቋንቋ አደርጋለሁ በማለት በተደጋጋሚ ለህዝቡ ቃል ገብቶ ነበር ። ይሄው አሁን ቃል ከተገባ አንድ አመት አለፈ። በተለያየ ጊዜና ቦታ አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የማድረጉ ጉዳይን አስመልክተው የተጠየቁት የህዝቡ ባለአደራ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ የተለያዩ ምላሾችን ሰጥቶበታል ። ዶ/ር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስተር ከመሆናቸው ጥቂት ወራት በፊትና ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆኑበት ጥቂት ወራት በኋላ ተስፋ ሰጪ የሆኑትን ምላሾች ይሰጡ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስቴር ከመሆናቸውጥቂት ወራት በፊት በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ህዝባዊ ውይይት ባደረጉበት ጊዜ የህዝቡን ደጋፍና ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ማድረግ ዋነኛ አላማና ተግባራችን ይሆናል ብለዋል። ጠቅላይ ሚኒስተር ከሆኑበት ጀምሮ ለጥቂት ወራት ደግሞ 'አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት ተጨማሪ የስራ ቋንቋ ለማድረግ እየሰራንበት ነው በቅርቡ የፌደራል የስራ ቋንቋ ይሆናል' በማለት ህዝቡን ሲያጓጉቆይተዋል።





ዶ/ር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆኑበት ከተወሰኑ ወራት በኋላ ግን ምላሾቹ ተስፋ አስቆራጭ እየሆኑ መጥቷል።

ለምሳሌ ጥቅምት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ጀርመን አገር ፍራንክፈረት ከተማ ተገኝተው በዚያና አካባቢው ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትዉልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የማድረጉ ጥያቄ ከምን ደረሰ ተብለው ተጠይቀው እንዲ ብሎ ነበር፡- "አፋን ኦሮሞ የፌደራል የስራ ቋንቋ እንዲሆን ከኦሮሞ በበለጠ አማራው መጠየቅ አለበት። አማርኛ ቋንቋ እንዲያድግ ኦሮሞ ሊሰራበት ይገባል። ልክ ጣናን ከኛ እንዳልን አማርኛን ኬኛ ኦሮሚኛ የኛ እንበል።"ከዚ ምላሻቸው የምንረዳው ጥያቄውን ለመመለስ ቁርጠኛ አለመሆናቸውን ነው። የአማራ ህዝብ ካልፈቀደ የኦሮሞ ህዝብ በፌደራል መንግስት ደረጃ በራሱ ቋንቋ መገልገል አይችልም እንደማለት ነው። አሁን አሁን ደግሞ ይህንን ጥያቄ ማንሳት ዘረኝነት ነው ከሚሉት ጋር አብሯል።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እነዚህ የኦሮሞ ህዝብ የመብት ጥያቄዎች እንዲመለሱ የማይፈልጉና የሁሉንም ህዝቦች የማንነት ባህልና ቋንቋ መሰረት በማድረግ የተዋቀረውን የፌደራል ስርዓት ለማፍረስ ከሚታትሩ ሀይላት ጋር አብሯል ። በአጠቃላይ የኦሮሞ ህዝብ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ይህንን የቋንቋ ጥያቄ ጉዳይ ይመልሱልኛል ብለው መጠበቅ የለበትም ።

የዶ/ር አብይ አህመድ የቅርብ አማካሪ የሆነው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያዬቱንና አቋሙን በሰጠበት ላይ “አፋን ኦሮሞን የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ማድረግ ዘረኝነት መሆኑና ለጋራ ኢትዮጵያዊአንድነታችን አደጋ ነው” ማለቱ የቅርብ ግዜ ትውስታችን ነው።

## ሰውዬውና የሰውዬው መፅሐፍቶች

የጠቅላይ ሚኒስተር ፅህፈትቤት አንድ ሚሊዮን ብር ከመንግስት በጀት ወጪ በማድረግ ሶስት መፅሐፍቶችን አሳትሟል። ሁለቱ መፅሐፎች ሰውዬው እና የአንድ አመት ጉዞ የሚባሉሲሆን ሶስተኛው መፅሐፍ መጠሪያ ርዕስ አልወጣለትም።


መፅሐፉን የፃፉት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን በመሩበትወቅት ያወቋቸውና ጓደኞቹ የነበሩ ሰዎች ናቸው። በተጨማሪ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት መፅሐፍቶቹ የተፃፉበትን መልክ የቀረፀና የሳንሱር ስራውን የሰራ የቤተ መንግስቱ ዘዋሪ ነው።

የመፅሐፎቹ ዋና አላማዎች የጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድን ገፅታ ህዝቡ ዘንድበአዎንታዊ መልኩ ለማስረፅ ነው።መፅሐፎቹ በተጋነነ መልኩ ዶ/ር አብይ አህመድን የሁሉም ፈጣሪ እና አድራጊ እንደሆኑ እውቅና ለመስጠት መክረዋል፡፡ የኦሮሞና አማራ ህዝብን ታሪካዊ ቁርሾ በብቸኝነት የፈወሱ ጠቅላይ ሚኒስቴርዶ/ር አብይ አህመድ እንደሆኑ ከማያግባባታሪክ ጋር ነማዋዛት ለማስረዳት ሞክረዋል። ሶስቱም መፅሐፍቶች ዶ/ር አብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒሰቴር ከመሆናቸው በፊት ለውጡን ከኋላ ሆኖ ይመሩ እንደነበሩ እና ከለውጡ ጠንሳሾች አንደኛው እንደሆኑ ይተነትናሉ። በሚያስገርምና በሚያሳዝን መልኩም መፅሐፎቹ ለውጡ የዬትኛውምአካል ውጤት እንዳልሆነ በመተንተን፣ የለውጡ ብቸኛ ባለቤት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ብቻ እንደሆኑ እውቅና ሰጥተዋቸዋል፡፡





ሌላው በመፅሀፉ ላይየተብራራው ዋናው ጉዳይ ስለ ዶ/ር አብይ አህመድ ወላጅ እናት እና ወላጅ አባቱ አቶ አህመድ አሊ (አባ ፊጣ) ጉዳይ ነው።በሰውዬው መፅሀፍ ላይ ገንዘብ ተበጅቶለት መፅሐፉን የፃፈው ጋዜጠኛ በተሰጠው የአቅጣጫ ማዕቀፍ መሰረት የሰውዬውን ወላጅ እናት እያሞካሸ፣ ወላጅ አባቱን ደግሞ እየነቀፈ ለማቅረብ ሞክሯል።



ወላጅ እናቱ የዶ/ር አብይ አህመድ አስተዳደግ ላይ በጣም የገዘፈ አስተዋፅኦ እንዳበረከቱና ለዶ/ር አብይ አህመድ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ የእርሳቸው ጥረት ዋነኛው እንደነበር የተብራራበት ሲሆን፤ ወላጅ አባቱን ደግሞ ለልጆቹ ደንታ የሌላቸው ሰውና የልጆች አስተዳደግና ክትትል ላይ እጅጉን ደካማ እንደሆኑ ያትታል።ይህ የወላጆቹ ጉዳይ በዚ መልኩ ለህዝቡ እንዲደርስ የተፈለገበት ምክንያትየአባቱን ማንነት በማጣጣል የእናቱን

ማንነት ደግሞ ለማጉላት ሲባል ሆን ተብለው ፖለቲካዊ እንድምታው ተጠንተው ነው።

ምንም ይህንን የውሸት ድርሰት መፅሐፍ አንብበው መጨረሱ ትግዕስት ቢጠይቅም፣ ሌላው ከሰውዬው መፅሐፍ ላይ በጣም የገረመኝ አነግን ለመሳል የተሞከረበት መንገድ ነው። በመፅሐፉ ላይ ስለወንድሞቹ የሚያብራራው ክፍል የሰውዬው ወንድሞች ለህዝቡ ነፃነት ሲባል ገና በታዳጊ እድሜያቸው አነግን መዋጋት እንደጀመሩ ነው። ይህ የሰውዬውን ትክክለኛ ማንነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ሰውዬው ለአነግ ምን አይነት ጫፍ የረገጠ ጥላቻ እንዳለው ያሳየናል። ኦሮሞ ሆኖ አነግን የማይደግፍ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ለኦሮሞ ህዝብ የቆምኩ ነኝ፣ ኦሮሞ ነኝ እያሉ አነግን በዚ መልኩ ማንቋሸሽ ማንን ለማስተደሰት እንደሆነ የተሰወረ አይሆንም።

ገና በአንድ አመት የስልጣን ቆይታው ሚሊዮን ብሮችን ከመንግስት ካዝና አውጥተው በመመደብ የራሱን የውሸት ግለ-ታሪክ የሚያትቱ እያዳንዳቸው ባለ 500 ገፆች 3 መፅሐፍቶችያፃፈ ሰውዬ፣ እንደ ምንም ብሎ አንድአመት ከጨመረ ምን ሊያደርግ እንደሚችል አይጠፋችሁም።

በዘውዳዊ አገዛዝ ዘመን ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት ንጉሶች ራሱ በህይወት እያሉ በገንዘብ ሰው ገዝተው ግለታሪካቸውን አላፃፉም። የነአፄ ሚኒልክ፣ ቀዳማዊ አፄ ሀይለስላሴ ታሪክ የተፃፈው እነሱ ካለፉ ከስንት አመታት በኋላ በሌሎች ገለልተኛ ግለሰቦችነው።





## የመጪው ምርጫ ዕጣ ፋንታ

አንድ አገር ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ልትሻገር የሚትችለው ነፃና ፍትሃዊ የሆነ ብሔራዊ ምርጫ ስታካሂድ ብቻ ነው። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የአፍሪካአገራት ይህንን እድል አላገኙም። በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ያልተመረጠ መንግስት ባለበት አገር ዲሞክራሲ ሲሰፍን አይታይም። ዲሞክራሲያዊ ያልሆኑ አገራት ዲሞክራሴያዊ ከሆኑ አገሮች አንፃር ሲታዩ አነስተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት እያስመዘገቡ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃን እየመሩ የሚገኙ ናቸው።

ለምሳሌም ምዕራብ አውሮፓንና አፍሪካን ማነፃፀር ይቻላል። የአፍሪካ አገራት ከምዕራብ አውሮፓ አገራትአንፃር ስንት ዕጥፍ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራቸውም በህዝብ የተመረጠ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ስለሌላቸው ብቻ ሀብታቸውን መጠቀም ተስኖአቸው በምዕራብ አውሮፓውያኑ ዕርዳታ የዕለት ጉርሳቸውን እየሞሉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም በታሪኳ ውስጥ ለከፍለዘመናት በድህነት ማሳያ መስፈርቶች ደረጃ ከመሪዎቹ አንዷ ሆና እንዲትቀጥል ያስገደዳት ትልቁ ማነቆ የሀብት ውስንነት ሳይሆን የዲሞክራሲያዊ መንግስት አለመኖር ጉዳይ ነው።

የተፈጥሮ ሀብት ጉዳይ ካነሳን አይቀር ከሻኪሶና ለገዳምቢ የሚገኘው የወርቅ ማዕድን፣ ቦረና ያለው የቀንድ ከብት ሀብት፣ ጅማና ወለጋ ያለው ቡና፣ የወለጋ ዕምነበረድ ወርቅና ፕላቲንየምና የቅባት እህሎች፣ ኢሉባቦራ ያለው የድንጋይ ከሰል፣ ባሌ አርሲ ሸዋ ያለው የቱሪስት መስዕብ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫና መስኖ የሚውሉ ጊቤ ዲዴሳ አዋሽ ገናሌ የመሳሰሉ ወንዞቻችን እንኳን ለኢትዮጵያ አገራችን ለአለምም በቂ ነበሩ።

ግን ምን ያደርጋል? በህዝብ የተመረጠ መንግስት እስከሌለን ድረስ እነዚ የተፈጥሮ ሀብታችንን መጠቀም አንችልም።

እንደአለመታደል ሆኖ እስካሁን በህዝብ የተመረጠ መንግስት ኢትዮጵያን አላስተዳደራትም። ምርጫ ሲካሄድ የቆየው ለስም ነበር። ይህንን በምርጫ 1992 ዓ.ም፤ 1997 ዓ.ም፣ 2002 ዓ.ም፣ 2007 ዓ.ም አይተናል። የኮሮጆና የመራጮች ድምፅ ስርቆት የተሞላበት ነበር። ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚታሰሩበትና የሚደበደቡበት ነበር። አልፎም ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንኳን በምርጫው እንዳይሳተፉ አሸባሪ ተብለውም ከአገር ተሰደው ነበር። አሁን በስደት የቆዩትም ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወደአገር ተመልሷል። አዳዲስ ፓርቲዎችም ተመስርቷል። የተዋሃዱም አሉ፣ አላማችን የለውጡን መንግስት መደገፍ ነው ያሉም አልጠፉም።




እነ አነግ አብንየመሳሰሉና አንፃራዊ የተሻለ የህዝብ ድጋፍ ያላቸው ፓርቲዎች መጪው ምርጫ በተቀመጠለት የግዜ ሰሌዳ እንዲካሄድ ይፈልጋሉ። ኢ-ዜማ ተብሎ እንደአዲስ የተቋቋመውና በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ





የሚመራው ድርጅት ደግሞ የ2012ቱ አገርአቀፍ ምርጫ እንዲራዘም ይፈልጋል።

የብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ አባላት ሹመትም ቢሆን ለኢዜማና መሰል የፖለቲካ ድርጅቶች የተመቻቸ ነው። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን አባላት በጠቅላላ ተመሳሳይ የፖለቲካ አመለካከት ካላቸው እንዲሰባሰቡ ያደረጉት አስበውበት ነው። ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳም የቀድሞ ጓደኞቿን እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን እንዴት አድርጋ እየተንከባከበቻቸው እንደሆነ እያታዘብን ነው ያለነው።

መጪውን ምርጫ አስመልክቶ የኢህአዴግ አቋም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ምርጫው በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወን እንፈልጋለን እንደምሉት አይደለም። በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከወራት በፊት ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ላይ 'ምርጫው ይራዘማል ወይ? ' ተብሎ ተጠይቆ፣ 'ምርጫ ቦርድ ዝግጅቱን ከጨረሰ እኛ እንደ ኢህአደግ ዝግጁዎች ነን ብለው ነበር።

ጠቅላይ ሚኒሰቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ምርጫው እንዲራዘም ይፈልጋሉ፣ ይህንን ደግሞ በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች እውን ለማድረግ እየሰሩ ይገኛሉ:: አንደኛው በየኢትዮጵያ ክፍል አካባቢዎች የተረጋጋ ሰላም እንዳይኖር በማድረግ፣ ሁለተኛው በእነ ኢዜማ በኩል ምርጫ ቦድር ላይ መጪው ምርጫ እንዲራዘም ጫና በማድረግ፣ ሶስተኛው ደግሞ ምርጫውን ለማድረግ የሚያስችል በቂ በጀት አለመኖሩ እንደምክንያት መጠቀም ናቸው::

ባለፈው ግዜ ጠቅላይ ሚኒሰቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ወደትግራይ ክልል አክሱም ከተማ ባመሩበት ጊዜ ከከተማዋ ነዋሪዎች "መጪው ምርጫ

እንዲራዘም ዘንድ የመንግስትዎ ፍላጎት ነውና ይህንን ቢያብራሩልን? "ተብለው ተጠይቀው እንዲህ በማለት መጪውን ምርጫ አስመልክተው አቋማቸውን ግልፅ ያደረገችምላሽ ሰጥቷል፦ "የምርጫ ጉዳይ ሊያሳስበን አይገባም። ለሀያ ሰላሳ አመታት ምርጫ ያላደረጉ አገሮች አሉ።"
ይታያችሁ እንግዲ ህወሃት ከስልጣን መገፋቷን ተከትለው አገሪቷን ወደዲሞክራሲ አሸጋግራታለሁ በማለት የለውጡ መንግስት ብሎ እራራቸውን የሰየመውመሪ ልክ ወደጠቅላይ ሚኒስቴርነት እንደመጡ"የሽግግር መንግስት ቢቋቋም የተሻለ አይደለምን ወይ?" ተብለው በተደጋጋሚ ተጠይቀው "ይሄኛው አሁን ያለው የሽግግር መንግስት ነው። አላማችን ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ እንዲደረግ አድርገን አገሪቷን ወደ ዲሞክራሲ ማሸጋገር ነው። ከዚ በላይ ሽግግር የለም። "ያሉት መሪ አሁን ላይ ደርሰው ቃላቸውን በማጠፍ የምርጫን አላስፈላጊነት በአደባባይ እየሰበኩ ይገኛሉ። ዲሞክራሲን መሪ አድርገው የዲሞክራሲን ጠቀሜታ እየሰበከ ወደስልጣን የወጣ መሪ ገና በአንድ አመት የስልጣን ቆይታው የምርጫን አላስፈላጊነት ወደማስተማር ከተሸጋገረ፣ በቀጣይ ፍላጎቱና ድርጊቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅታችሁም።





## ኦሮሞን የመከፋፈል ሴራ

### ለይተው የማልማት ፖለቲካ

ሁሉንም የአገሪቷን ክፍሎች ፍትሀዊ በሆነና እኩልነት ላይ መተመሰረተ አካሄድ በማልማት የየአካባቢዎችን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ማድረግ የመንግስት ዋነኛ ተግባሩ መሆኑ ይታወቃል። ባለፉት የህወሃት አስተዳደር ዘመን በዚህ መልኩ እኩልነትን መሰረት በማድረግ አገሪቷ ሲትለማ አላየንም። አንዳንዱ አካባቢ ነፍጠኛ ተብለው አንዳንዱ አካባቢ ደግሞ አነግ ተብለው ከነበረው ውስን ልማት ተጠቃሚ ሳይሆን ቀርተዋል። አሁንም በዶ/ር አብይ አህመድ አስተዳደር ዘመን ይህ ለይተው የማልማት ፖለቲካዊ ሴራ ቀጥሏል። ዛሬም ወለጋ ሀራርጌ ባሌ አርሲ የለውጡን መንግስት ከልባችሁ አልተቀበላችሁም በሚል ሰበብ ካለችውም ልማት ተገለው ይገኛሉ። ልማቱ በሸዋ አካባቢዎች፣ በጂማና ኢሉባቦር ብቻ ተወስኗል ። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ አምቦን ኒው ዮርከ እናደርጋታለን ያሉበት ንግግር ፖለቲካዊ መልዕክትን ያዘለ ነው። የዶ/ር አብይን መንግስት የደገፉ አካባቢዎች ይለማሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ አይለሙም። በዚህም ውስጥ በለሙና ባልለሙ አካባቢዎች በሚኖሩ ህዝቦች መካከል ጥርጣሬ ይፈጠራል። ጥርጣሬው ወደ ጥላቻ ያድጋል። ጥላቻው ደግሞ ግጭትን ይወልዳል። በዚህ መልኩ ኦሮሞን በአካባቢ አጋጭተው አንድነቱን ለመስበር ታስቧል።

### ከኦዴፒ አመራር ሹሜት በስተጀርባ

ከአመት በፊት አንደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶር አብይ አህመድና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ለማ መገርሳ ከተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ከተሰባሰቡ የአገር ሽማግሌዎች፣ ፖለቲከኞች፣ አክቲቬስቶችና ሌሎች

ግለሰቦች ጋር በቤተመንግስት 'የኦሮሞ ፖለቲካ ከዬት ወደት?' በሚል ርዕስ ተወያይቷል። በመጨረሻም ከተሳታፊዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፣ አንዱጥያቄ እንዲ የሚል ነበር፦ ዶ/ር አብይ በተለያዩ ሌሎች ክልሎች ጉብኝት እያደረጉ ለምን በምዕራብ ኦሮሚያ ወለጋ የሚገኙ ከቤኒንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ኦሮሚያ ክልል ድምበር የተፈናቀሉትን ዜጎች አልጎበኙም?

ዶ/ር አብይ መመለሱን ቀጠለ፦

"እኔ በልጅነት እድሜዬ ገና 15 16 አመት እያለሁ ለትግል ወለጋ ነበርኩ። የወለጋ ህዝብ የሚጠጣ ውሃ ጠይቄን ውሃ ሰጥቶን አያውቅም፣ ወተት ነበር የሚሰጡን። ህዝብን በጣምነው የሚወደው። የኦሮሚያ ክልል መንግስት ላይ እያለሁ ሻምቡ ነቀምቴና ግምቢ ሄጄህዝቡን አወያይቻለሁ። ከዛም ደምቢዶሎ ደግሞ ለምን ቀረ ስሉ ልክ ጠቅላይ ሚኒስቴርእንደሆንኩ ሄጄ አገኟቸው። አሁን ወለጋ መሄዱ ላይ ከለማ ጋር ስድስት ሰባት ጊዜተጋጭተናል። እኔ ተጨባጭ መረጃ እጄ ላይ ስላለ ነው። የተፈናቀሉትን ሊጎበኙ ወለጋመጥተው ህዝቡ መሃል ሲሄዱ ህዝብ ስስሙ እዚው እናስቀራቿሃለን የሚል ማስረጃ ይሄውብእጄ አለ። እኔ ሌላ ክልል ሄጄ ቢሞት የኦሮሞ ህዝብ አይለያይም አንድነቱን አጠናከረውትግሉን ይቀጥላል እንጂ። ወለጋ ላይ ቢሞት ግን ጂማና ወለጋ፣ አርሲና ወለጋ፣ ባሌና ወለጋአንድ ሊሆን አይችልም። እኔ ሞትን ፈርቼ አይደለም ለአመታት ብዙ መስዋእትነትን ከፍያለሁ እናንቴ ካመናቹበት አሁን ተነስቼ መሄድ እችላለሁ።"



የተጠለፈ የህዝብ ትግል

ይህ የዶ/ር አብይ አህመድ የፀጥታው ዘርፍ ሹመኞች ሆን ብለው የወለጋን ህዝብ ከኢትዮጵያና ኦሮሞ ፖለቲካ እያገለሉ ይገኛሉ። ባለፈው ወር የደህነት ሹመኞቻቸው ሆን ብለው ወለጋ ላይ ሊገድላችሁ የተዘጋጀ አካል አለ በማለት ዶር አብይና አቦ ለማን ከወለጋ ህዝብ የመነጠል ስራቸውን ሰሩ። ትላንት ደግሞ ለአገሪቱ የሚያሰጋ ትልቅ የአማፂ ቡድን እንዳለ ነገር የወለጋ ህዝብ በጦር ሄሊኮፕተሮች እንዲሸበር ተደረገ። የወለጋ ህዝብ ከሌላው ህዝብ የተለየ ነገር የሚፈልገው የለም። የወለጋ ህዝብ የሚፈልገው ፀጥታው እንዲከበርለትና እኩል የአገሪቷ ፖለቲካ ውስጥ ተሳታፊ መሆንን ብቻ ነው። ከዚ ባለፈ እንደቀድሞው የሚኒሊክ ሀይለስላሴ ደርግና ወያኔ ዘመን የወለጋን ህዝብ ከማዕከላዊው የፖለቲካ ጨዋታ ማስወጣት ከቶ አይቻልም። ይሄንን ስል የወለጋ ህዝብ ፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚወከለው በአንድ ድርጅት ብቻ ነው ማለቴ አይደለም። እዚያ ያለውን ህዝብና የፖለቲካ ድርጅት ለይተው ማየት ተገቢ ነው።

አሁን ደግሞ ኦሮሞን ከኦሮሞ ለማጋጨት ሲባል የኦዴፒ አመራርን ከትውልድወይም መኖሪያ አካባቢያቸውወጪ የመመደብ ፖለቲካዊ ሴራ እየተሰራ ነው። ለምሳሌም የቡሌ ሆራ ካንቲባ የነበሩት አቶ ኡቱካና ኦዳ የሆለታ ከተማ ካንቲባ ሆነው ተሹመዋል።

ከሻሸመኔ ተሹመው ወደ ቄለም ወለጋ የሄደው ሰው ደምቢዶሎ በገባበት ማታውኑ ታቅዶበት በመንግስት የአገርውስጥ ደህንነት አባላት ተገድሏል። በዚም ወለጋዎች አርሲን ገደሉ የሚል ወሬ እንዲወራ ተደረገ። ከዚያም ወሬውን በማራገብ ኦሮሞን ከኦሮሞ አርሲ ወለጋ ሀረርጌ ወዘተ እያሉ ለመከፋፈል እየሞከሩ ነው። በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦህደድ /ኦዴፒ አመራር ከአካባቢያቸው ውጪ ተሹሟል። በአባዱላየሚዘወረው የኦሮሚያ

ክልል መንግስት አላማው ኦሮሞን በአካባቢ አጋጭተው አንድነቱንመስበር ነው። ህወሃትን ያዋረደው የህዝቡ አንድነት ለኦዲፒ ደግሞ እንደስጋት ተወስዷል።

የኦሮሞን አንድት ከተቻለ ለመስበር ካልሆነ ደግሞ ለማዳከም በዋናነት እየመራና ለጀሌዎቹ ይህንን የሚፈፅሙበትን ዘዴ እየቀመረላቸው ያለው የኦሮሞ ህዝብ ትግልን አደራ የበሉት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር አብይ አህመድ ናቸው። ዶክተር አብይ አህመድ በኦህደድ/ ኦዲፒ ውስጥ ያሉትን ከፍተኛ አመራሮችን በአካባቢ ለያይተው ለማጋጨት በማሰብ የትውልድ ስፍራቸው ከወለጋ የሆኑት አመራሮች ጋር ሲሄዱ"እነዚ ጎበናዎቹን አትመኑ" እያሉ በጎን ደግሞ የትውልድ ስፍራቸው ሸዋ አካባቢ የሆኑት አመራሮች ጋር በመሄድ "ጎበና ጀግና ነው፣ ወለጋን አትመኑ ከሃዲዎች ናቸው" እያሉ የድርጅቱ አመራሮች ሸዋና ወለጋ እያሉ እንድፋጁ አነሳስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ዶ/ር አብይ አህመድ አንዳንዶችን አመራር ለማን አትመኑት እሱ ወለጋ ነው ያሉዋቸውም አልጠፉም፡፡አላማቸውም የሚመኩበትን የአፄ ሚኒልክን መንገድ በመከተል ኦሮሞን በአካባቢው እየከፋፈሉ እርስበርሱ እንዳይስማማ በማድረግ መግዛት ነው። የኦሮሞ ብሔርተኝነትና አንድነት ራስ ምታት የሆነባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኦሮሞን በአካባቢ ሸዋ ወለጋ አርሲ ባሌ ሀራርጌ በማለት እየከፋፈሉዋቸውና እንዳይግባቡ በየጊዜው የማያስማማ አጀንዳ እየፈጠሩላቸው ስልጣናቸውን ማራዘም ይፈልጋሉ። በዚህ ስልጣን ዘመናቸውም በአራት ኪሎ ቤተመንግሥት የሚገኘውን የሚኒሊክን አዳራሽ እንዳሳደሱ ሁሉ የቀሩትን የሚኒልክን ለጋሲዎች በማስቀጠል ዳግም ኦሮሞ በአሃዳዊ ስርዓት መንግሰት እንዲገዛ ማስቻል ነው።





ሌላው ምሳሌ ኦሮሞን በአካባቢ ከፋፍለው ለማጋጨት ሲባል አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደቻሳን ከሀላፊነቱ እንዲያነሳ አቶ ለማ መገርሳን ጎትጉቶ ካስነሳው በኋላ ከወር በፊት መልሰው እዛው ቦታ ላይ እንዲሾም አድርጓል።

በተጨማሪ ኦሮሞን በአካባቢ ከፋፍለው የማጋጨቱን ሴራ እየፈፀመ ያለው የኦህደድ/ ኦዲፒ ከፍተኛ አመራር የሆነው አቶ ካሳሁን ጎፌ ነው። በቀናት በፊት ወደ ባሌ ሮቤ ሄደው ህዝቡን ባወያየበት ወቅት ህዝቡ የአካባቢነት ስሜት እንዲሰማው ለማድረግ ሲባል "አቦ ለማ መገርሳ ተባብረው ሊሰሩ የሚችሉ የአመራር ቡድንን ማደራጀት አልቻለም። አሁን እኛ ይህንን አያደረግን ነው" ብሏል።

### ***ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ ክፍፍል***

ሀይማኖትን መሰረት አድርገው ህዝቡን በማጋጨት ከዚያም ከፋፍለውና አንድነት አሳጥተው መግዛትን የህወሃት አስተዳደር ለረዥም ጊዜ ተጠቅሞበታል። ይህ ፋሽኑ ያለፈበት ሴራ ነው ብላችሁ እንዳትሸወዱ። ዛሬም የኦሮሞን ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላውን ኢትዮጵያውያንን በሀይማኖት የመከፋፈል የተንኮል ፖለቲካ እየተፈፀመ ይገኛል። እውነት ነው በባለፈው የህወሃት ስርዓት በርካታ ሙስሊም ወጣቶች ሀይማኖታዊ መብታቸውን ለማስከበር በተንቀሳቀሱ ግዜ ለእስርና ስቃይ ተዳርጎ ነበር። የሌሎች ሀይማኖት ተከታዮችም በሀይማኖታቸው ምክንያት ለእስርና ማስፈራሪያ እንደተዳረጉ ሁሉ ጎላ ባለ መልኩ ደግሞ በርካቶች ሙስሊም ስለሆኑ ብቻ አሸባሪ ተብለው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ደርሶባቸዋል። በሀይማኖቱ ውስጥ ያሉትም በህወሃት መንግስት እንዲከፋፈሉ ተደርጎ ነበር። እኚ በሀይማኖታቸው ምክንያት ዘብጥያ ወርደው የነበሩትን ኢትዮጵያውያን

አስፈትተው ከዚያም በመጅሊሱ ውስጥ የነበረው ሽኩቻ እንዲፈታ ከፍተኛ የሆነ ጥረት አድርጎ ስለተሳካላቸው ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድና አብሮት የነበሩት ከፍተኛ አመራሮች ምዝጋና ይገባቸዋል። እውቅናም ሊሰጣቸው ይገባል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዶክተር አብይ አህመድ በተለያየ ግዜ የሙስሊም ሀይማኖት መሪዎችንና መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴውን በተደጋጋሚ አግኝተው ሲያወያዩ እንደነበር ይታወሳል። ነገር ግን በውይይቶቹ ግዜ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከእርሳቸው ውጪ ያለው ሁሉም የኦህደድ/ ኦዲፒ አመራር የሙስሊም ማህበረሰቡ ጥያቄዎች እንድመለሱ ፍላጎት የሌላቸው መሆናቸውን ለተወያዮቹ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ችሏል። ይህ ትክክል ያለሆነ ህዝቡን የማጋጫ መንገድ ነው። የሙስሊም ማህበረሰቡ ሙስሊም ያልሆነው አመራር ላይ አመኔታን እንዲያጣ ያደርጋል። ከዚያም ወደህዝብ ይወርድና ህዝቡ በሚኖርበት አካባቢ በሀይማኖት እንዲጋጭ ያነሳሳል። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ አንዳንዱ አካባቢ ሙስሊም የሚበዛበት ሌላው ደግሞ ክርስቲያን የሚበዛበት ስለሆነ አንዱን አካባቢ ከሌላው ለማጋጨት ሀይማኖት እንደ ሴራው ማስፈፀሚያ ሊያገለግል ይችላል። ይህ በሀይማኖት ህዝቡን በተለይም የኦሮሞን ህዝብ የማጋጨቱ አላማ የህዝቡን አንድነት ለመስበር ነበር። በምርጫ ወደስልጣን ያልመጣ መንግስት ሁሌም የህዝብ አንድነት እንዳስፈራው ነው። አንድነቱ እንዳይሰበር ወይም እንዳይላላ ስል ህዝቡ ነቅተው ሀይማኖትን መሰረት ካደረጉ ግጭቶችና መንስዔዎቻቸው እራሱን ሊጠብቅ ይገበዋል።

**ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለይተው መያዝ**

ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለይተው መያዝ  ሲባል አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን በአዱዋ ድል አከባበር ቀን አስቀድሞ ወግቶታል።እዉቁና ተወዳጁ የኦሮሞ





አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ብዙሃን ዘንድ የሚታወቀው የትግል ዘፈኖችን ለህዝቡ በማቅረቡ ነው። ሃጫሉ ጀግና መሆኑን በዚያ በርካቶቹ አርቲስቶች ከአገር ተሰደው በተለያዩ የአለም አገራት ይኖሩ በነበሩበትና የትግል ዘፈን ሰማ ተብለህ በሚትታሰርበት አስፈሪ ጊዜ ከአገሬ አልወጣም ብሎ በድፍረት እንደፈለገ አገሪቷ ውስጥ ሲዘዋወር የነበረ ልባም ነው። አልፎም በየመድረኩ በቀጥታ በሚያቀርባቸው ቀረርቶዎች የማናውቀው ስሜት እንዲንዋጥ አድርጎናል። ከአሁን በኋላ ግን አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ መንግስትን እንዳይቃወም ተደርጓል። አንድ በጥቅም፤ ሁለት በዛቻ። የዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቃብይነት አላቸው ብለው ያመነባቸውን ሰዎች በጥቅምና በማስፈራራት እያኮላሻቸው ይገኛል። በተይም የኦሮሞ አንድነት በዚዚሁ ከቀጠለ ለኔም ስጋት ነው ብሎ የሚያስበው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኦሮሞ ህዝብ አንድነትን በዘዴ ማዳከም ይፈልጋል። በዚህ ደግሞ ሸዋን አቅርቦ ወለጋና ሀራርጌን ማራቅ አንዱ ዘዴ ነው። የተመረጡት የሃጫሉ አይነቶቹ ደግሞ የመንግስት  ደጋፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። እምቢ ካሉ ቀጭን ማስፈራሪያ ይከተላቸዋል። የዚህ አመት የአዱዋ በዓል አከባበርን አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ ከንቲባ ኢንጅነር ታከለ ኡማ በኩል ለአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ 2.8 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ ተሰጥቶታል። የአዱዋ በዓል በደረሰ ግዜም በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በዓሉን በኦሮሞ ባህላዊ አለባበስና ፈረስ ደምቀው ፒያሳ ላይ አክብሯል።

ከዚያም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አርቲስት ሃጫሉ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት በአቶ ሽመልስ አብዲሳ አማካኝነት ስልክ ተደወለለትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚፈልጉት ተነገረው። በተያዘው የቀጠሮ ሰዓት መሰረትም

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድና አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ በአራት ኪሎ ቤተመንግስት የጠቅላዩ ቢሮ ተገናኙ። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከአስር ደቂቃ በላይ አላዋራዉም። ጥቂት የደህነንት አባላትም አብሮአቸው ነበሩ። በአጭሩ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ለአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ እንዲህ በማለት ዛቻ አዘል ቀጭን ትዕዛዝ አስተላልፏል፦ <<ትግሉ አብቅቷል። አገሪቷን እያስተዳደረ ያለው ኦሮሞ ነው። ከአሁን ወዲህ ከአንተ የምንጠብቀው ህዝቡን ለተቃውሞ እንዲታነሳሳ ይሆን ለውጡን እንድትደግፍ ነው። እኛም የጥቅም ፍላጎትህን እንጠብቅልሃለን። ተወደደም ተጠላም ቢያንስ ለሚቀጥሉት አስር አመታት አገሪቷን የሚያስተዳድረው እኔው ነኝ። ከዚህ አፈነግጣለሁ ካልክ ለአንድ ደቂቃ አንታገስህም።>>

**ጀግኖችን በአካባቢ ለይተው ማድነቅ**

የዶርአብይ አህመድወደጠቅላይ ሚኒስቴርነት መምጣትን ተከትለው የጎበና ዳጬስም ሆን ቸብለው በአንዳንድ ካድሬዎች ሲነሳ ሁላችንም ታዝቤናል።መጀመሪያ ጎበና ዳጬ ጀግና ነው አይደለም በምል ክርክር ተደረገበት። ቀጥሎ ጉዳዩ ወደሚፈለግበት የአቅጣጫ ማዕቀፍ ውስጥ ገባ። በአካባቢኦሮሞን ለመከፋፈል የሚያመች ማዕቀፍ ውስጥ።

የጄነራል ታደሰ ብሩን የመታሰቢያ ሀውልት የማቆም ፖለቲካ ነዉ ፡፡ የጄነራል ታደሰ ብሩን መታሰቢያ ሐውልት በሰላሌ ፍቼ ከተማ መሰራት ጀርባ ያለውን የኦሮሞን መከፋፈል ሴራ እንኳ እንደማሳያ መውሰድ ይቻላል። ጄኔራል ታደሰ ብሩ በኦሮሞ ህዝብ ትግል ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ታጋይ ጀግና ነው። ጀነራል ታደሰ ብሩ እንደነ ጀነራል ዋቆ ጉቱ፣ ዶር ሀይሌ ፍዳ፣ ... ሁሉም ለመላው ኦሮሞ ህዝብ ዘመን የማይሽረው ትግል በማድረጉ በሁሉም ኦሮሞ ልብ ዘንድ የሚኖር ነው።






ታዴ ብሩ መላውን የኦሮሞ ህዝብ ከነበረበት ጭቆና ለማላቀቅ ሲታገል የነበረው እንደ ብሔርተኛ (nationalist) ነው። በደል ሲደርስበትና ሲታሰር የነበረው በኦሮሞነቱ ነው። ለኦሮሞ ህዝብ ውድ ህይወቱን የተነጠቀውም በኦሮሞነቱ ነው። ታዴ የኦሮሞን ህዝብ በተቀናጀና ዘመናዊ መልኩ ሲመራ የቆየው የኦሮሚያ እምብርት በሆነችው ፊንፊኔ ላይ ሆኖ ነው። ምንም የጄኔራል ታደሰ ብሩ የትውልድ ስፍራ ሸዋ ሰላሌ ቢሆንም የመታሰቢያ ሀውልቱ መሰራት የነበረበት በትግል ማዕከሉና የኦሮሚያ እምብርት ፊንፊኔ ላይ ነው።እንደቀዬው ልጅ አቡነ ጴጥሮስ (መገርሳ በዳሳ) የመታሰቢያ ሀውልቱ ለምን በፊንፊኔ አልቆመም? በዛ ላይ ታደሰ ብሩ ኔልሰን ማንደላን የመሰለ የአፍሪካ የነፃነት አባት በማሰልጠኑ የኦሮሞ፣ ኢትዮጵያ ጀግና ብቻ ሳይሆን አልፎም የአፍሪካዊያንና መላው ጥቁር ህዝብ ባለውለታ ነው። ከዚ አንፃርም ካየነው የጄኔራል ታዴ ሀውልት መቆም የነበረበት በአፍሪካ መዲና ፊንፊኔ ነው። የሀይሌ ፍዳና ባሮ ቱምሳ የታገሉት ለወለጋ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኦሮሞ ህዝብ ነው። ዋቆ ጉቱ የታገለው ለባሌ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኦሮሞ ነው፡፡

ኦዴፓና አጋሮቿን በፊንፊኔ ጉዳይ ከመፍራት በተጨምሪ የጄኔራል ታደሰ ብሩን የመታሰቢያ ሀውልት በፍቼ ሰላሌ ከማቆም ጀርባ የኦዲፒ የፖለቲካ ሴራ አለ። ኦሮሞን የመከፋፈል ሴራ። ለስልጣን ማራዘሚያ ሲባል የኦሮሞን አንድነት የመስበር ሴራ። ህወሃትን ከስልጣን የገፋው የኦሮሞ ህዝብ አንድነት ኦዲፒ እንደስጋት ተቀብሎታል።

## ኦነግን የማኮላሸት ሴራ

ኦነግ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነው ማለት አይቻልም። የኦነግ ስም ሲነሳ የወዳጅም የጠላትም ልብ ይቆማል። የአንደኛው በፍቅር፣ የሌላኛው በጥላቻ እና በፍርሃት። ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ የትግል አርማ ነው። ኦነግ ድርጅት ብቻ አይደለም። ኦነግ የነፃነት መንፈስ ነው። ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የመጨረሻው እጣ ፈንታው ሆኖ የሚታይ እንጂ በስልጣን እና የጦር ሜዳ ድል ብቻ የሚለካ ነገር አይደለም።



ስለ ኦነግ ሲነሳ አርማው፣ ሰራዊቱ እና አመራሩ የየራሳቸው የሆነ በጎ ተፅእኖ አላቸው። አርማውን ሲያይ ውስጡ የማይርድ እና የማይረበሽ ጠላት አይኖርም። ለዚህም ነው አንዳንዶች የቡዳ መድሃኒት የሚሉት። አሁን አሁን ይሄን የኦነግ አርማ ለድርጅቱ ብቻ ከመተው ይልቅ ማንኛውም ለኦሮሞ ህዝብ መብት እና ነፃነት የሚንቀሳቀስ ቡድን





ሲጠቀምበት ማየት የተለመደ ሆኗል። ከኦነግ አርማነት ወደ የresistance flagነት ተቀይሯዋል። ማንኛውም የኦሮሞ ህዝብን የሚመለከት የተቃውሞም ሆነ የድጋፍ እንቅስቃሴ በሚኖርበት ጊዜ የሚታጀበው በዚህ ባንድራ ነው።

ሁለተኛው የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት ነው። ይሄ ሰራዊት አወቃቀሩን እንኳን ብንመለከት እንደ ማንኛውም ውትድርናን እንደ አማራጭ የስራ ዘርፍ የሚመለከት ሰው የተሰበሰበበት ሳይሆን በተለያየ ምክንያት የህዝቡን ብሶት ያየ እና ያደመጠ፣ ይሄንንም የተቃወመ ብቻ ሳይሆን ይሄንን ጭቆና እና አፈና ከህዝቡ ላይ ለማላቀቅ ወስኖ በአላማ የትጥቅ ትግልን የተቀላቀለ ስብስብ ነው። በዚህ የሰራዊት ስብስብ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ምሩቃን፣ የመንግስት ሰራተኞች እና ሌሎች በተለያየ የሙያ እና የስራ ዘርፍ ተሰማርተው የነበሩ ወጣቶች ፤ እንዲሁም በነበረው ጭቆና ምክንያት ሕይወታቸውን በአግባቡ መምራት ያልቻሉ ሌሎች ዜጎች ይገኙበታል። የኦነግ ሰራዊት በአግባቡ የሰለጠነ እና የተሰጠውን ወታደራዊ ግዳጅ በሙሉ ብቃት እና ቁርጠኝነት መወጣት የሚችል ብቁ እና ንቁ የወታደር ስብስብ እንደሆነ ይመሰከርለታል።

ሶስተኛው የኦነግ አካል አመራሩ ነው። ኦነግ እንደ ፓርቲ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ከኦሮሞ ህዝብ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ እና በፖለቲካ እውቀታቸው አንቱ የተባሉ ሰዎች መርተውታል።

ኦነግ እንደ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጋቸው አስተዋፅዎች በደማቅ ቀለም የተፃፉ ናቸው። የንጉሱን ስርዓት እና ቀጥሎ የደርግን አምባገነናዊ ወታደራዊ መንግስት ለማስወገድ በተደረገው የትጥቅ ትግል ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። በተለይም ደግሞ ከደርግ ውድቀት በኋላ ባለው

የሽግግር ወቅት የፓርላማ መቀመጫን በመያዝ ጭምር ለህገ መንግስቱ መረቀቅ እና መፅደቅ የራሱን ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ለተተገበረው የፌደራሊዝም ስርዓትም የራሱን ሚና ከመወጣትም በተጨማሪ ኦሮሚያ የምትባለውን ክልላዊ መንግስት ቅርፅ በማስያዝ እና መሬት ላይ በማስመር የተጫወተው ሚና ከፍ ያለ ነው። የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትምህርት እና የስራ ቋንቋ ኦሮሚኛ እንዲሆንና ለዚህም ተፈፃሚነት እንደማንኛውም ሌላ ክልል ለክልሉ የሚገባውን ፖለቲካዊ መብት ለማስከበር ከፍተኛ የሆነ ሚና ተጫውተዋል።

በተለያዩ ጊዜያት ኦነግ እንደ ፓርቲ የፈፀማቸው ጥቃቅን ስህተቶች ቢኖሩም በኦሮሞ ህዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር ፅረ ጭቆና ትግል ውስጥ ያደረገው አስተዋፅኦ ግን በታሪክ ውስጥ አቻ የለውም።

የኦነግ እንቅስቃሴ እጅግ በጣም በአደጋዎች የተፈተነ እና ትግሉ ማዕከል ባደረገው የኦሮሞ ህዝብ ላይ ያደረሳቸው አደጋዎችም እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የኦነግ ስኬት እና አንፀባራቂ ውጤቶች እንዲሁ በአጋጣሚ የተገኙም አልነበሩም። ኦነግ እንደ ፓርቲ ወሳኝ አባላቱን እና አመራሮቹን ሰውቶበታል። በ1980 ዓ.ም ? ሰማሌ ላይ አመራሩን ሙሉ በሙሉ በሞት ያጣበት የታሪክ አጋጣሚ ይታወሳል። በተጨማሪም አቶ ሌንጮ ለታ እንደ ገለፁት" የፖለቲካ ቁማር የተበላበት" እና በሽግግር መንግስቱ በህወሃት የተደረገባቸው ክህደትም ሌላው የፖለቲካ ኪሳራ የተጋፈጠበት አጋጣሚ ነበር።

ይሄም ቢሆን ከውጪ በኤርትራ፣ በኬንያ እና በደቡብ ሱዳን አዋሳኝ አካባቢዎች በማድረግ እና በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች መሬት የያዘ እና መንግስትን ያስጨነቀ የትጥቅ ትግሉ አድርጓል።





በዚህም የተነሳ በተለይም ህወሃት በበላይነት ሃገሪቱን በመራችባቸው ጊዜያት በኦነግ ስም ቤተሰቡ የወከባ እና እስራት፤ ስቃይ እና ግድያ ሰለባ ያልሆነ ቤተሰብ ኦሮሚያ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት እጅግ ከባድ ነው።

ይሄ ሁሉ የስቃይ እና አፈና ጊዜ እንዲያልፍ እና በተለይም የኦሮሞ ህዝብን የራስን እድል በራስ የመወሰን ትግል የመራው ኦነግ በሃገሪቱ ውስጥ የህወሃትን የበላይነት እና ቅጥ ያጣ ጭቆና በማስወገድ በኩል ትልቅ የሆነ አስተዋፅኦ እንደነበረው የሃገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ የሚከታተል ማንም ሰው መመስከር ይችላል።

በሃገሪቱ ውስጥ ከውስጥ እና ከውጪ የተደረገውን እልህ አስጨራሽ ትግል ደግፎ የተንቀሳቀሰው ኦነግም ከድሉ ማግስት እንደማንኛውም የሃገሪቱ የተቃዋሚ ፓርት ከለውጡ መንግስት የተላለፈለትን በጋራ የመስራት እና በሰላማዊ መንገድ የመታገል ጥሪ ተቀብሎ ወደ ሃገር ገባ።

ህዝቡም ደማቅ አቀባበል ለአመራሩ መጀመሪያ አዲስ አበባ፣ ላይ ቀጥሎም በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ተደረገለት። ይሁንና ለኦነግ የተደረገው አቀባበል ብዙም በሰላም የዘለቀ አልነበረም።

የመንግስትን ቀናነት ማጣት በሚያሳብቁ ድርጊቶች የታጀቡ እና የኦነግን እንቅስቃሴ የሚገድቡ ሁኔታዎች መታየት ጀመሩ። ይሄንን ተከትሎም የኦነግ እና የመንግስት ባለስልጣናት በየፊናቸው መግለጫዎችን መስጠት ጀመሩ።

ነገሩ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ ሄደ። በተለይም በኦዲፒ አመራሮች በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁት አሉባልታዎች ዋነኛ የችግሩ ምንጮች እንደነበሩ መታዘብ ይቻላል።

በተለያዩ ጊዜያት ልዩነቶቻቸውን ለመፍታት በሌሎች አሸማጋይነት ለድርድር ተቀምጠው የተስማሙ ቢሆንም ውሎ ሳይደር ግን ተስማማን ከሚሉት ጉዳይ በተቃራኒ መግለጫዎችን በመስጠት ሁኔታዎች እንዲወሳሰቡ ተደርጓዋል። ከዚህ ጀርባ ግን የኦነግ ህልውና ጭራሽ እንዲከስም የሚፈልጉ ወገኖች ሚና በፍፁም መዘንጋት የለበትም። እነዚህ ወገኖች ኦነግ እንደማንኛውም የተቃዋሚ ፓርቲ እንዲንቀሳቀስ ሳይሆን ፈፅሞ እንዲከስም የሚፈልጉ እና የኦሮሞ ህዝብ ትግል እረፍት የሚነሳቸው እንዲሁም በኦሮሞ ህዝብ ጥላቻ የታወቁ አካላት ናቸው።

ይሁንና ግን ይሄ ሁኔታ ለመንግስትም ለኦነግም ሆነ ለሃገሪቱ ህልውና ጭምር አደጋ መጋረጡን የተገነዘቡ ፥ በተለይም የሃይማኖት መሪዎች፣ አባገዳዎች የሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የሃገር ሽማግሌዎች እና ሃደ ሲቄዎችን ያካተተ አሸማጋይ ቡድን ተቋቁሞ እልህ አስጨራሽ ድርድር ከመንግስት እና ኦነግ አመራሮች ጋር በማድረግ "የመጨረሻ ስምምነት" ላይ በመድረስ "የአምቦ ስምምነት" ተፈራረሙ።

በዚህ ስምምነት መሰረት ኦነግ ሰራዊቱን ወደ ካምፕ አስገብቶ አስፈላጊው ስልጠና ከተሰጠው በኋላ ወደ ኦሮሚያ ፖሊስነት ወይም ወደ መከላከያ ሰራዊት 'እንዲቀላቀል ፤ አመራሩ ደግሞ በነፃነት ቢሮዎችን ከፍቶ በነፃነት የፖለቲካ ስራዎችን እንዲሰራ እንዲመቻችለት ነበር።

ይሁንና ግን አዴፖ መራሹ የመንግስት ወገን ግን ይሄንን ስምምነት መጣስ የጀመረው እና ኦነግን የማጥፋት እንቅስቃሴውን የጀመረው ከስምምቱ ማግስት ነበር። የፓርቲው ጽህፈት ቤት ሃላፊ በማግስቱ ለሸገር ሬዲዮ በሰጡት ቃለ ምልልስ የኦነጉ መሪ በስምምነቱ እለት የኦነግ ሰራዊትን ለአባ





ገዳዎች አስረክቤአለሁ ያሉት በመጥቀስ እየተዘባበተ እንደዚህ የሚባል ነገር የለም የኦነግ  የምንረከበው እኛ ነን አለ።

በመቀጠልም በተቋቋመው የአሸማጋይ አካላት አማካይነት በተለይም ከወለጋ የተለያዩ አካባቢዎች እና ከደቡብ የቦረና አካባቢ በመምጣት ወደ ማሰልጠኛ የገቡ እንዲሁም ቀደም ብለው ከኤርትሪያ መጥተው የኦነግ ሰራዊት አካባቢ ጥሩ አያያዝ እየተደረገላቸው እንዳልሆነ መረጃዎች መውጣት ጀመሩ።

ይሄም ተጨማሪ ስጋት በመፍጠሩ በሚመስል መልኩ ሌሎች ጫካ የቀሩት በተለይም በአቶ ኩምሳ ድሪባ ወይም ጃል መሮ የሚመራው የምዕራብ ኦሮሚያ የትጥቅ ትግል ክንፍ አሁን የተደረገው ድርድር ለአንድ ወገን ያደለ በመሆኑና የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊትን ጥቅም የሚያስጠብቅ ባለመሆኑ ስምምነቱን እንደማይቀበል እና በትጥቅ ትግሉ እንደሚቀጥል አስታወቁ።

መንግስትም ኦነግን በቀላሉ ያጠፋ መስሎት ወደ ካምፕ ያስገባቸውን በስምምነቱ መሰረት ለተግባራዊነቱ ከመንቀሳቀስ ይልቅ በድል አድራጊነት መንፈስ ካምፕ ውስጥ የገቡትን የሰራዊቱን አባላትን አፈነ። ለጉብኝት የተንቀሳቀሱትን የአሸማጋዮች ቡድን አዋርዶ መለሰ።

በምዕራብ ኦሮሚያ ውስጥ የሚቀሳቀሱ የኦነግ አባላት ላይ ሙሉ በሙሉ የታጠቀ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን አሰማራ። የጦር አዛዡን ጃል መሮን ከአየር ጭምር ለመግደል ሙከራ አደረገበት። ወለጋን እና ደቡብ ጉጂን ከሌሎቹ የሃገሪቱ ክልሎች በተለየ መልኩ በወታደራዊ እዝ ስር አስገባ። የህዝቡ እንቅስቃሴ ታገደ።

የፕሮፖጋንዳ ዘመቻዎች በኦነግ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተደረገ። ለምሳሌም የደቡብ ጉጂ የጦር አዛዥ እጁን ሰጠ ተብሎ በአደባባይ ያልተጣራ መረጃ ተለቀቀ።

**የኦነግ አቀባበል ዝግጅትን ማደፍረስ**

ለኦነግ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የአቀባበል ስርዓት ለማድረግ ከጥቂት ቀናት በፊት በሸገር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ። እኔም ከቡራዩና ሱሉልታ የመጡ ቄሮዎችን እንቅስቃሴ በፓስተርና አዲሱ ሚካኤል አካባቢዎች ላይ ተገኝቼ ታዝቤያለሁ። አንድ ቀን ቀደም ብዬ በግምቦት ሰባት ደጋዎችና ለኦነግ አቀባበል ባንዲራ በመስቀልና ቀለም ለመቀባት ከቡራዩ በመጡ ቄሮዎች ጉለሌ ክፍለ ከተማ መዳኒያለም መሰናዶ ትምህርት ቤት አጠገብ ባለው አደባባይ ጠብ ሲነሳም በቦታው ነበርኩኝ። በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጠብ እንዲነሳ የተፈለገው በመንግስት ፀጥታ ሀይሎች ታስቦበትና ታልሞበት ነበር። በቀጣዩ ቀንም ፀቡ በረታ። በጣም የሚያስጠላ ጦርነት እያየሁኝ ነበር ። ጦሪነቱ የተካሄደው በዱላና በድንጋይ ነው ። የፌደራል ፖሊስም ሆነ የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት በስፍራው ቢኖሩም ፀቡን ለማስቆም ጥረት አላደረጉም። ዝም ብሎ እያዩ ነበር። በሰልፍ ሆነው መንገድ ዘግተው ጭስ ቦምብ በመወርወር ብቻ፣ እኔንም የፌዴራል ፖሊስ ጭስ ቦምብ አግኝተውኛል። ከፒያሳ ወደ አስኮ የሚወስደው መንገድ ለትራንስፖርት ሙሉበሙሉ ለሶስት ቀናት ዝግ ነበር።

የኦነግ አቀባበል ከመድረሱ ከቀናት በፊት የሸገር ወጣቶች በእራሳቸው መንገድ ማንም ሳይጫናቸው የፈለጉትን ባንዲራና መፈክር ይዘው የሚደግፉትን ግለሰቦችና እነ ግንቦት 7 የተባለውን የፖለቲካ ድርጅት





በተቀበሉበት ጊዜ ማንም የተቃወማቸውም ሆነ ዝግጅታቸውን ለማወክ የተንቀሳቀሰ ግለሰብ ቡድንም ሆነ ድርጅት አልነበረም ። ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለው የነ ግንቦት 7 ደጋፊ ያልሆኑት የመዲናዋና አካባቢዋ ህዝቦች በዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የሌሎችን ልዩነት መቀበል በመቻላቸው ነው ። በተለይም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ለውጥ ውስጥ ንቁ ተሳታፊና ትልቅ ድርሻ የነበረው ቄሮም ልዩነት ውስጥ ዲሞክራሲን እንገባ በሚል እሳቤው ተሞርከዞ የግንቦት 7 አቀባበል በሰላም እንዲጠናቀቅ የበኩሉን ተወጥተዋል። አሁን ላይ በተራው ቄሮ ይወክለኛል የኔ ነው የሚለውን የፖለቲካ ድርጅት ለመቀበል የቅድመ ዝግጅት ስራውን ለማከናወን በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከግንቦት 7 ደጋፊዎች የጠበቀው ነገር የተቃራኒ ነበር። ቄሮ የኦነግን አርማና ባንዲራ እንዳይሰቅል ተከልክለዋል፡፡ የሰቀለውንም ባንዲራ አውርደዋል፣ በሚሰቅሉበት ጊዜም ድብደባና ግድያ ደርሶበታል፣ በፖሊስ በጥይት ተመቷል ፣ የኦነግ ባንዲራ የለጠፉና የሰቀሉ ተሽከርካሪዎች ወድመዋል፣ የኦሮሞ ስም ያሉባቸው ባንኮች ትምህርት ቤቶችና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች ተዘርፏል፣ ቄሮ በየአቅጣጫው ወደ መዲናዋ እንዳይገባ በፖሊሶች ተከልክሏል ። ይህ የሆነው በኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መንግስት፣ ኦነግ ፣ ኦፌኮ ፣ ኦህደድ መቀመጫ በሆነችው በፊንፊኔ ከተማ ላይ ነው።

ይህ ሁሉ በመንግስት የፀጥታ አካላት የተቀነባበረው ለአንድ አላማ ነው። እሱም ከኦህደድ/ ኦዲፒ ይልቅ ብዙ እጥፍ ህዝባዊ ድጋፍ ያለውን ኦነግን ስሙን ጥለሸት ለመቀባት ሲባል ነው።

የዚህ በኦነግ አቀባበል ማግስት የተጫረው ፀብ አልቆመም። በቡራዩ ወደሌላ ምዕራፍ ተሸጋገረ።

**የቡራዩ መፈናቀል**

የኦነግ አቀባበል ቀን ሌሊቱን በመንግስት የፀጥታ አካላት በተመለመሉ ስልጠናና ገንዘብ በተሰጣቸው ወጣቶች አማካኝነት በቡራዩ ከተማ በብዛት ልዩ ቦታው ከታ ከተባለ ስፍራ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ የጋሞ ብሔረሰብ ነዋሪዎች እንዲዘረፉና እንዲገደሉ ተደረገ። ድርጊቱም ወዳልተፈለገ ግጭት አመራ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎችም ውድ ህይወታቸውን ገበሩ። የመንግስት የፀጥታ አካላትም ግጭቱን ለማርገብ አቫፈረኝ አሉ። የሞተው ሞቶ የተጎዳው ተጎድተው የጋሞ ብሔረሰብ ተወላጆችም መኖሪያ ቤታቸውን ትተው ወደ አዲስ አበባ ተሰደዱ። ሁሉም በሚቻል መልኩ ግለሰቦችና የመገናኛ ብዙኀን የወንጀል ድርጊቱን ቁሮና ኦነግ ላይ ለጠፉ። መንግስትም ይህንን ነበር የፈለገውና ተሳካለት።

በአዲስ አበባና ቡራዩ የተከሰተውን ግጭትና የሰዎች መፈናቀልን ያቀነባበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና የአቶ አባዱላ ገመዳ ቡድን አህደዶች ነበሩ። የሴራው ዋና ዋና ተሳታፊዎችም በሸገር ያሉ የግንቦት-7 የተመለመሉ ንቁ አባላት እና በአቶ ለማ መገርሳ የተባረሩና የመሬት ንግዳቸው በመቆሙ ያኮረፉ የቀድሞ ኦህደድ አመራሮች ሲሆኑ በዋናነት የመራው ደግሞ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቅርብ ሰው የሆነው የግንቦት-7 የአቀባበል ኮሚቴ አስተባባሪ የነበረው አቶ ብርሃኑ ተከለ ያሬድ ነበር። የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር አቶ ዜይኑ ጀማልም ጉዳዩን አስመልክተው ከአንድ ቀን በፊት በሰጡት መግለጫ ወንጀሉ ሁለቴ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ባሉ የተቀነባበረና በአንደኛው እንደተመራ ነግረውናል ። የአዲስ አበባ ፖሊስ በአዲስ አበባ እና ቡራዩ የተከሰተውን የዝርፊያ ፣ ግድያ፣ ግጭትና የዜጎች መፈናቀል ወንጀልን በዋናነት መርተዋል ብለው የጠረጠረውን የግንቦት-7 የአቀባበል





ኮሚቴ መሪ የነበረውን አቶ ብርሃኑ ተከለ ያረድን በቁጥጥር ስር አውሎ ነበር። ምንም በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ቀጭን ትዕዛዝ ከቀናት በኋላ ቢፈታለም።

በቡራዩ ከተማ አስተዳደር የፀጥታ ዘርፍ ሐላፊ የሆነው ኮሚሺነር ሰለሞን ታደሰ ETv ስቱዲዮ ቀርበው ፣ በቡራዩ በተፈፀመው ግድያና መፈናቀል ጋር ተያይዘው ቁጥጥር ስር ከዋሉ 364 ግለሰቦች ውስጥ አንድም የቡራዩ ቄሮ እንደለለበትና ወንጀለኞቹም ከአዲስ አበባ ወደዚያ ያመሩ የተለያዩ ብሔር ስብጥር መሆናቸውን አብራርተዋል።

እንግዲ ከዚ ጊዜ ጀምሮ ነው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድና ዶር ብርሃኑ ነጋ መተባበር የጀመሩት። የኦነግን ስም በማጥፋት ተባበሩ። የኦሮሞን ብሔርተኝነት ለማቀጨጭ ትብራቸውን ቀጠሉ።

**ሌሎች የኦነግ ክፋዮችን እንደኢጋር መጠቀም**

ሌላው ኦነግን የማከላሻ ዘዴ የቀድሞ ኦነግ አካል ፓርቲዎችን እንደአጋር መያዝ ነው። በሌንጮ ለታ የሚመራውን ODF፣ በጄነራል ከማል ገልቹ የሚመራውን ONP እና በገላሳ ዲልቦ የሚመራውን OLF TAን እንደአጋር በመያዝ በዳውድ ኢብሳ የሚመራውን ኦነግ ነጥብ ማስጣል አንዱ የዶር አብይ አህመድ ፖለቲካዊ ሴራ ነበር።

**በአቦ ገላሳ ዲልቦ የሚመራው ኦነግ ወደ አገር መግባትን ተከትለዉ**

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶር አብይ አህመድ ልክ ወደ ስልጣን እንደመጡ ከኢትዮጵያ ወጪ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ አገራቸው ገብተው በተመቻቸው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ሠላማዊ ትግልን እንዲያካሄዱ ባደረጉት ጥሪ መሰረት በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪውን ተቀብለው ወደአገር ተመልሰዋል። በዚህም በኦሮሞ ህዝብ ስም የተቋቋሙ

የፖለቲካ ድርጅቶች ወደአገር ገብተው እንቅስቃሴዎችን የጀመሩ ስሆን አነዚህም መካከል በአቦ ሌንጮ ለታ የሚመራው አሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግምባር፣ በአቦ ዳውድ ኢብሳ የሚመራው አነግ፣ በአቦ ሀይሉ ጎኖፋ የሚመራው አነግና በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ብሔራዊ ፓርቲ ተጠቃሾች ናቸው። ከተጠቀሱት በተጨማሪ ወደአገር ሳይገባ የቆዬው በአቦ ገላሳ ዲልቦ የሚመራው አነግ ነው።

የአነግ- ሽግግሩ አካል (OLF- Transitional Authority) በመባል የሚታወቀው የፖለቲካ.ድርጅት 22 አመራሮች ከመንግስት የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብለውና ሠላማዊ ትግልን ለማድረግ ቅዳሜ ታህሳስ 20፣ 2011 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቷል። በአቦ ገላሳ ዲልቦ የሚመራው የአነግ ሽግግር አካል ወደአገር በገባበት ግዜም በመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው አማካኝነት ደማቅ አቀባበል የተደረገላቸው ስሆን በተጨማሪም በአሮሞ ባህል ማዕከል የአቀባበል ስነስርዓት ዝግጅት ተሰናድቶላቸዋል። የሽግግሩ አካል አነግ በማዕከላዊ ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ወደአገር ገብተው በሠላማዊ መንገድ ለመታገል የወሰነው ጥቅምት 20 ፣ 2011 ዓ.ም በጀርመን በርሊን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ባደረጉት ድርድር ከስምምነት ላይ በመድረሳቸው ነው።

በሽግግሩ መንግስት ወቅት የአነግ ተወካይ የነበሩትን አመራሮች በውስጡ ያቀፈው አነግ-የሽግግሩ አካል በወቅቱ የአነግ ተወካይ የነበረውን አቦ ገላሳ ዲልቦ፣ አቦ ኢብሳ ጉተማ፣ አቦ እና ሌሎች ቀደምት ታጋዮችን ይዘው ወደአገር ተመልሷል። ከነዚ ወደአገር ከተመለሱ የቀደምት የአነግ አመራር አባላት ውስጥ አንዱ የሆነው አቦ ኢብሳ ጉተማ በ1970ዎች የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ጉልህ ሚና የነበረው ስሆን እስካሁን በብዙዎች ዘንድ





ታዋቂና ተወዳጅ የሆነችውን 'ኢትዮጵያዊ ማነው?' የተሰኘችውን ግጥም የገጠመ አገር ወዳድ ታጋይ ነው። ኢብሳ ጉተማ በሽግግሩ መንግስት ወቅት እስከታሰረበት 1986 ዓ.ም የትምህርት ሚኒሰቴር ምንስትር ሆኖ አገልግሏል። የትምህርት ሚኒስቴርን በሚኒስትርነት በመራበት ግዜያትም በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉም መደበኛ የትምህርት አይነቶች በአፋን አሮሞ እንዲሰጡና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግም አፋን አሮሞ እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንዲሰጥ በማድረጉ በብዙዎች ዘንድ 'የቁቤ አባት' በመባልም ይታወቃል።

የዚህ በአቦ ገላሳ ዲልቦ የሚመራው የአነግ ከንፍ ወደ አገር መግባቱ በርካታ ፖለቲካዊ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት በጠቅላይ ሚኒስቴር ዶር አብይ አህመድ ታምኖበት ነው።

የአነግ ሽግግር መንግስትን በተደጋጋሚ ወደአገር እንዲገቡ በመጠየቅ እንዲገቡ ያደረገው የዶር አብይ አህመድ መንግስት የሚከተሉትን ፖለቲካዊ ትርፎች ለማግኘት በማሰብ ነበር። ከነዚም ውስጥ ዋነኛው አነግን ማኮላሸት ነው። በሽግግር መንግስቱ ግዜ የነበረው ትክክለኛው አነግ በገላሳ ዲልቦ የሚመራው ነው በማለት የአነግ ደጋፊዎችን በማወናበድ ድጋፋቸውን መከፋፈል ነው።

ሌላኛው ፋይዳው፣ ይህ በገላሳ የሚመራው አነግ የነ ዶር አብይ አህመድን የለውጥ መንግስት የመደገፍ አቋም እንዳለው በመግለፁ፤ በዳውድ ኢብሳ የሚመራው አነግ ከጠላት ጋር በማበር በአሮሚያ ክልል የተለያዩ ቦታዎች የሚንቀሳቀሱ ናቸው በማለት በህዝቡ በኩል ተቀባይነትና አመኔታን እንዲያጡና እንዲዳከሙ ለማድረግ ነበር።

በዚህም በክልሉ የተለያዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ እየተስተዋሉ የሚገኙ ግጭቶች፣ የንፁሃን ግድያ፣ የዜጎች መፈናቀሎችና ሌሎች ችግሮችን የሚፈፅመው በዳውድ ኢብሳ በሚመራው አነግ እንደሆነ ህዝቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር ነው።   ። በመጨረሻም፣ በሽግግሩ መንግስት ወቅትበብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የነበረው አነግ የሚታወቀው በአቦ ገላሳ ዲልቦ ስም በመሆኑ፣ እንደ አዲስ አንመዘገብም በሽግግሩ መንግስት ወቅት ተመዝግበናል ያሉት የአነግ ተከፋይ ድርጅቶች ተገደው እንዲመዘገቡ መስገደድና አንመዘገብም ካሉም ከቀጣዩ ምርጫ ውጪ እንዲሆኑ በማሰብ የተሰረ ነበር። ነገር ግን የዶር አብይ አህመድ መንግስት እንዳሰበው በገላሳ ዲልቦ አነግ የተጠበቀውን ያክል ከኦሮሞ ህዝብ ድጋፍ ሳያገኝ ቀረ። ህዝቡ ጦር ያለውን አነግ መደገፉን ቀጠለ። ከምርጫ ቦርድም እውቅና ተሰጠው።


**ባንኮችን ማዘረፍ**

የአነግን ስም ጥለሸት ለመቀባት ሲባል የመንግስት የፀጥታ ሀይሎች ግለሰቦችን በመመልመልና የጦር መሳሪያ በማስታጠቅ በተለያዩ የወለጋ ዞኖች የመንግስትና የግል ባንኮች እንዲዘረፉ አድርጓል። በዚም መሰረት በቄለም ወለጋ`ዞን በስድስት ከተሞች የተዘረፉ የባንኮች ቁጥር 18 ነው። እነዚም በጫንቃ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኦሮሚያ ህብረትስራ ባንክ እና የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አ.ማ)፣በመቻራ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ፣ የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ)፣በቀቤ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ)፣ በጋባ ሮቢ (የኦሮሚያ ህብረትስራ ባንክ)፣በኢናንጎ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኦሮሚያ ህብረትስራ ባንክ)፣በጉሊሶ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኦሮሚያ ህብረትስራ ባንክ፣ አዋሽ ባንክ እና





የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አ.ማ) ፣በነቀምቴ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሌቃ ቅርንጫፍ)፣ በሻምቡ (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ) እና ሌሎችናቸዉ::



ከጥቂት ግዜ በፊት ከLTV ጋር ቃለምልልስ ያደረገው የቀድሞ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የፀጥታና አስተዳደር ጉዳዮች ሀላፊ ጀነራል ከማል ገልቹ በአደባባይ በምዕራብ ኦሮሚያ ባንኮችን ሲዘርፍና ሲያዘርፉ የነበሩት የመንግስት የፀጥታ አካላት መሆናቸውን ተናግሯል።

**ባለሀብቶችን መዝረፍና መግደል**

በምዕራብ ኦሮሚያ ነጆ አካባቢ የአካባቢው ተወለጆች እና የውጭ ሃገር እንቬስተሮች የያዘ መኪና ከነሰዎቹ በአነግ በተጠመደ ፈንጂ ጋየ የሚል አስደንጋጭ ዜና ሁሉ ተሰራጭቶ ነበር። ይሁንና ትክክለኛው ነገር ሁኔታው መፈፀሙ እንጂ በአነግ መፈፀሙን ማረጋገጥ አልተቻለም። ይሄንን ጉዳይ እንዲያጣራ ከፌዴራል ፖሊስ ፀረ ሽብር ግብረ ሃይል የተላከው ቡድን ባቀረበው ሪፖርት " ይሄንን የፈንጂ አይነት ከመንግስት ውጪ በፍፁም

አነግ መታጠቅ አይችልም " የማ።ሚል ሪፖርት ስለ መቅረቡ አስተማማኝ መረጃ አለ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች እውነታዎች ዛሬም ልክ እንደትናንቱ አነግን ለማጥፋት እና የኦሮሞን ህዝብ ለእኩልነት የሚደረግ ትግል ለማኮላሸት እየተደረገ የነበረው ሴራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ነው።

በዚህም ሁኔታ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ አሁንም የዚህ ውጤት ገፈት ቀማሽነቱን ቀጥሏል። በተለየ መልኩ ደግሞ በህወሃት ጊዜ በአደባባይ የፀረ ጭቆና ትግል በማካሄድ ላይ እያሉ የብዙዎችን ህይወት የገበረው የወለጋ ህዝብ በይበልጥ ተጋላጭ ሆኗል።

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ባለስልጣናትን መግደል**

በተለያዩ ኦሮሚያ ክልል የሰላም መደፍረስ መቀጠሉንና በዚም 190,000 የሚሆኑ ኦሮሞዎች ከቤኒንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መፈናቀላቸውን ተከትለው ቀናት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶር አብይ አህመድና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ለማመገርሳ ከተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ከተሰባሰቡ የአገር ሽማግሌዎች፣ ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶችና ሌሎች ግለሰቦች ጋር በቤተመንግስት 'የኦሮሞ ፖለቲካ ከዬት ወደት?' በሚል ርዕስ ተወያይቷል። በመጨረሻም ከተሳታፊዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች የተነሱ ስሆን፣ አንዱ ጥያቄ እንዲ የሚል ነበር፦ ዶ/ር አብይ በተለያዩ ሌሎች ክልሎች ጉብኝት እያደረጉ ለምን በምዕራብ ኦሮሚያ ወለጋ የሚገኙ ከቤኒንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ኦሮሚያ ክልል ድምበር የተፈናቀሉትን ዜጎች አልጎበኙም?

ዶር አብይ መመለሱን ቀጠለ፦

"እኔ በልጅነት እድሜዬ ገና 15 16 አመት እያለሁ ለትግል ወለጋ ነበርኩ። የወለጋ ህዝብ የሚጠጣ ውሃ ጠይቄን ውሃ ሰጥቶን አያውቅም፣ ወተት ነበር





የሚሰጡን። ህዝብን በጣም ነው የሚወደው። የኦሮሚያ ክልል መንግስት ላይ እያለሁ ሻምቡ ነቀምቴና ግምቢ ሄጄ ህዝቡን አወያይቻለሁ። ከዛም ደምቢዶሎ ደግሞ ለምን ቀረ ስሉ ልክ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንደሆንኩ ሄጄ አገኟቸው። አሁን ወለጋ መሄዱ ላይ ከለማ ጋር ስድስት ሰባት ግዜ ተጋጭተናል። እኔ ተጨባጭ መረጃ እጄ ላይ ስላለ ነው። የተፈናቀሉትን ሊጎበኙ ወለጋ መጥተው ህዝቡ መሃል ሲሄዱ ህዝብ ስስሙ እዚው እናስቀራቿሃለን የሚል ማስረጃ ይሄው በእጄ አለ። እኔ ሌላ ክልል ሄጄ ቢሞት የኦሮሞ ህዝብ አይለያይም አንድነቱን አጠናክረው ትግሉን ይቀጥላል እንጂ። ወለጋ ላይ ቢሞት ግን ጂማና ወለጋ፣ አርሲና ወለጋ፣ ባሌና ወለጋ አንድ ሊሆን አይችልም። እኔ ሞትን ፈርቼ አይደለም ለአመታት ብዙ መስዋእትነትን ከፍያለሁ።እናንቴ ካመናቹበት አሁን ተነስቼ መሄድ እችላለሁ።"

**የታጠቀው አካል**

ከአነግ ጦር ውጪ በስሙ የታጠቀ ሌላ የታጣቂ ቡድን አለ። የአነግን ስም ለማጠልቸት ሲባል የመከላከያና ፌደራል ፖሊስ አባላትን መልምለውከዚያም የአነግጦር እንደሆኑ አስመስለው በምዕራብ ኦሮሚያ፣ጉጂና ከሚሴ አካባቢዎች በማስፈር ንፁሃንን እያስገደሉ ቡድኖች አሉ ።

## የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች መተባበር አለባቸው

የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች በባህላቸውም ሆነ በማንነታቸው በሰው ልጆች ማንነት፣ ክብር፣ ባህልና ቋንቋ እኩልነት የሚያምኑ ህዝቦች ናቸው። ለዚም ነው የፖለቲካ አመለካከታቸውም የተመሳሰለው። ምክንያቱም የሁለቱም ህዝቦች ማህበራዊ መሪ የሚመነጨው ከእኩልነት ነው ። ፖለቲካዊ አመለካከት ደግሞ የሚመነጨው ከህዝቦች ማህበራዊ እሴቶች ነው። እነዚ በማህበራዊ እሴቶቻቸውን እኩልነት በማድረግ ተመሳሳይ የሆነን የፖለቲካ መንገድ የሚከተሉ ሁለቱ ህዝቦች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ትልቅ በጋራ ትልቅ አሻራን ጥሰዋል።

የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች ከሶስት አስር አመታት በፊት በአገራችን ኢትዮጵያ የነበረውን የብሔር ጭቆናን በመቃወም በርካታ አመታትን የፈጀ ተመሳሳይ አላማ ያለው ትግል ያደረጉ ህዝቦች ናቸው።

የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች በቋንቋየው ምክንያት ለዘመናት ተጨቁነዋል። ሁለቱም ብሔሮች በየራሳቸው ቋንቋዎች እንዲገለገሉበት አይፈቀድላቸውም ነበር። ሁለቱም ህዝቦች ተገደው የየራሳቸውን በመተው በአማርኛ ቋንቋ እንዲማሩና እንዲገለገሉ ተደርጓል። እኩል የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን እድል እንዳያገኙ ተጨቁና ኖሯል።

በትጥቅ ትግል ዘመናቸውም ሁለቱም የኦሮሞና ተጋሩዎች ለመቁጠር የሚያዳግት ውድ ልጆቻቸውን መስዋእት አድርጓል። አንድ ትውልድ አልቆባቸዋል ማለት ይቻላል። ከአርባ አመታት በፊት ኦሮሞዎች ኦነግን መስርተው ተጋሩዎች ደግሞ ህወሃትን አቋቁሞ ህዝቦቻቸውን





ከተጫነባቸው የብሔር ጭቆና ነፃ ለማውጣት ስሉ ግማሽ ክፍለዘመንን ያስቆጠረ የትጥቅ ትግል አድርጓል።

ሁለቱም ተባብረው ትግል በማድረግ አምባገነኑን የደርግ መንግስት ከስልጣን ያስወገዱት ህዝቦች፣ የህዝቦችን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እኩልነት የሚያረጋግጥን ህገመንግስት በማርቀቅ አፀድቀውና ስራ ላይ በማዋል በጭቆና አረንቋ ስር ይኖሩ ለነበሩ የኢትዮጵያ ብሔሮችና ህዝቦች መልከ ብዙ የሆነ እኩልነትን አረጋግጠላቸዋል።

በዚ የሁሉንም ህዝቦች እኩልነትን መሪ ባደረገ ህገመንግስትና የብሔር ፌደራሊዝም አወቃቀር ባለፉት 27 አመታት አገሪቷና ዜጎቿ ተዳድሮበታል። በነዚ በለፉ ግዜያት የኦሮሞ ህዝብ የህወሃት ባለስልጣናት ህገመንግስቱን በማንሻፈፍና በመጣስ ሲፈፅሙ የነበሩትን የሰብዓዊና ዲሞክራሴያዊ የመብት ጥሰቶችን እንዲሁም እኩል የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ለመሆን ሲባል ረዥም የሆነ የትጥቅና ሰላማዊ ትግል ሲያደርግ መቆየቱ የማይካድ ሀቅ ነው። ነገር ግን የኦሮሞ ህዝብ በነዚ በህወሃት ዘመን ትግሉ ህገመንግሥቱ እንዲቀየር ወይም የፌደራሊዝም ስርዓቱ እንዲፈርስ ፈፅሞውኑ ፀይቆ አያውቅም ነበር። ምክንያቱም ህገመንግስቱ የህዝቦችን እኩልነት መሰረት አድርጎ የተፃፈ ስለነበር ነው።

ሁለቱም የኦሮሞና የትግራይ ህዝቦች ህገመንግስቱን ያከብሩታል። ተስማምቶበት ነው ያረቀቁት። ከሌላ ጎራ ህገመንግስቱን የማያከብሩና ሰበብ እየፈጠሩ ህገመንግሥቱ እንዲቀየር የሚፈልጉ እንዳሉ ይታወቃል ። በግልፅ ቋንቋ እነዚ ጎራዎች በህዝቦች እኩልነት የማያምኑ ናቸው። ህገመንግስቱን አፍርሰው እንደቀድሞ ዘመን ሁለቱ ህዝቦች ላይ አሃዳዊ መንግስትን በመጫን ሊቀጨቁኑአቸው የሚፈልጉ ፕሮ ሚኒሊካዊያን

ናቸው። እነዚ ሀይሎች አሁን በተሰፋ ተሞልተው እየፈነደቁ ይገኛሉ ። ምን አግኝተው ካላችሁ? መልሱ እንዲ ነው። የህግመንግስቱን የማሻሻል ፍላጎታቸውን የሚደግፍና ይሄንንም ለማድረግ ተቀራርበው አብሯቸው እየሰራ የሚገኝ ግለሰብ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው አገሪቷን እየመራ ይገኛል። ይሄ ሁለቱም የኦሮሞና ትግራይ ህዝቦች ለድርድር የማያቀርቡት ከተከፈተባቸው ጦርነት ነው። ይህ የኦሮሞና ትግራይን ህዝብ ለመጨፍለቅ የሚደረግ ሴራ ነው። ህገመንግስቱን በማሻሻል ወይም በመቀየር የፌደራል ስርዓቱን አፍርሰው አሃዳዊ ስርዓት በሚመሰረትበት ጉዳይ ላይ ሁለቱንም ህዝቦች ዘረኞች ብሎ የሚጠሩ እነ ዲያቆን ዳኒኤል ክብረት፣ ዶር ወንድወሰንና ዶር ዳኛቸው አሰፋ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ቀንተለሊት በማማከር ተጠምዷል።

ምንም አይነት ታሪካዊ ቁርሾ የሌላቸው የኦሮሞና ትግራይ ህዝቦች ይህንን የተጋረጠባቸውን አደጋ በመረዳት አንድ ላይ ተባብረው የተጠናከረ ትግል በማድረግ ዳግም ሊጨፈልቃቸውና ሊጨቁናቸው እያሰፈሰፈ ያለውን ንጉስ ድል ሊያደርጉት ይገባል።






## የፈገግታ ውጋት

ሁሌም ፈገግታ ቅን ልቦና ያለውን ሰው እንዳማለለ ነው። ቅን ሰው ከሆንክ በፈገግታ የተቀበለህን ሰው ታከብረዋለህ። አልፎም ትወደዋለህ። ፈገግታን ላሳየ ሰው ክፉ ወይም ተንኮለኛ አትለውም። በኛ አገርም ከፍትፍቱ ፊቱ የሚል የአባቶቻችን አባባል አለ። ዶ/ር አብይ አህመድ ይህንን የህዝቡን ደካማ ጎን በአስተዳደራቸው እየተጠቀሙበት ይገኛል። ህዝቡን ባወያዩ ቁጥር በፈገግታ ታጅበው ንግግር በማድረግ በመጨረሻም አስጭብጭበአቸው ይሄዳሉ። እንደታዳሚው ሁናቴ መተወንን ተክኖበታል። በፈገግታ ከታጀበው ውይይት በኋላ ግን ተወያዮች ያነሱት ጥያቄዎች ወይም ችግሮች ሲፈቱ አይታይም።

ከቅርብ ግዜያት ወዲህ ደግሞ እስራቱና አፈናው በርትተዋል። በተለይም በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ሰዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በፈገግታ የታጀበ ውይይት ካደረጉ በኋላ ታፍነው ወደ እስርቤት እየተወሰዱ ነው። በአፋን ኦሮሞ የተፃፉ መፅሐፍቶችን አሳትመው ማስመረቅእንደ ወንጀል በመቁጠሩ ለህዝባቸው ቋንቋ እድገት የራሳቸውን አበርክቶ ለማድረግ በማለም ለምርቃቱ ወዳጅ ዘመዳቸውን ጠርተው ተሞሽረው አዳራሽ የተገኙ ወጣት ደራሲያን በመንግስት ፀጥታ ሀይሎች ታፍነው ዘብጥያ ሲወርዱ በተደጋጋሚ እያየን ነው። በነቀምቴ ከተማ የመፅሐፍ ምረቃ ስነስርዓት ላይ ሁለት ግዜ የሆነውን መጥቀስ ይቻላል። በሻሸመኔ ጭሮ ገለምሶ ወሊሶ ግምቢ ደምቢዶሎና በሌሎች የወለጋ አካባቢ ከተሞች የኦነግን የአቀባበል ስነስርአት ያስተባበሩ ግለሰቦች በሙሉ አሁን ተይዘው እስርቤት ተወርውሯል። የኦነግ አባል ወይም ደጋፊ ናቸው የተባሉ

ሰዎች ሁሉ ከሚኖሩበት ቦታ ተለቅመው ለእስራት ተዳርጓል። ምን አለፋችሁ ከኦነግ ስም ጋር በተያየዘ አፈና ብቻ ወደ ሁለት ሺ የሚጠጉ ግለሰቦች ከጉጂ፣ አርሲ፣ ሀራርጌና ከአራቱ የወሊጋ ዞኖች ያለበቂ ምክንያትና የፖሊስ መጥሪያ በመንግስት የፀጥታ ሀይሎች ተወስደው እንዲታሰሩ ተደርጓል። አባገዳዎችን ጨምረው የየአካባቢው የአገር ሽማግሌዎች በመንግስት የፀጥታው ዘርፍ ሹመኞች ማስፈራራትና ዛቻ ደርሶባቸዋል። እያየን ያለናቸው አፈናዎች በህወሃት ዘመንም ያልታዩ አይነቶች ናቸው። ደርግ በአደባባይ ነበር የወጣቱን ግንባር በከላሽንኮቭ የሚለው፤ ህወሃት ደግሞ በግላጭ ማድረግ የሌለብህን ነገር ይነግርህና ተላልፈህ አታድርግ ያለህን ከፈፀምክ ይወስድህና በአደባባይ ሳይሆን በስውር ያሰቃይ ወይም ይገድል ነበር። የዶ/ር አብይ አህመድ አስተዳደር ደግሞ ከሁለቱም ይለያል። ከሁለቱ የሚለየው ባለማፈኑ ሳይሆን በማፈን ዘዴው ነው።







የዶ/ር አብይ አህመድ አፈና በፈገግታ የታጀበ ነው። ስትቃወመው ህዝቡ ፊት ያደንቅሃል። ያሞግስሃል። ይህንን በግልፅ መቃወምን በሱ ቸርነት እንዳገኘ አድርጎ ይመፃደቅበታል። ከዛም ጉዳዩን ከቁብ ያልቆጠረ ይመስላል። ያረሳሳል፣ ነገር ግን አይለቅህም። ቂም ይይዝብሃል። ቀጥሎም ትልቅ ተፅዕኖ መፍጠር የሚትችል አይነትና ህዝቡን ሊታሳምፅ የሚትችል አይነት ሰው ከሆንክ እራሱ ካለበት አስጠርቶህ ያስፈራራል። እየሳቀ ያዘጋጀልህን የውንጀላ ጉዳይ በውሸት ፈገግታ ታጅቦ ይነግርሃል። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በተፅዕኖ ፈጣሪነቱ በሚታወቀውና በትግሉ ወቅት የቄሮን ትግል እየመራ ህወሃትን በማስቀገዱ ዘመቻ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የፖለቲካ ተንታኝና አክቲቪስትጃዋር ሞሐመድ ከወራት በፊት ለዚ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የፈገግታ ማስፈራሪያ ሰለባ ሆነዋል። የቀድሞው ኮለኔል የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ መላው የኦሮሞ ህዝብ የሚሳሳለት ጃዋር ሞሐመድን ቢሮአቸው ድረስ በማስጠራት፣ ከአሁን በኋላ ወጣቱን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ ከማነሳሳት እንዲቆጠብ ምክር አዘል ትዕዛዝ ከሰጡት በኋላ በጨዋታ መልክ በፈገግታ ታጅበው "ከአላሙዲ ገንዘብ ተቀብለሃል። በህዝቡ ስም ገንዘብ ሰብስበሃል።" ብለውታል። ያው በግልፅ አማርኛ ያልኩህን ካላከበርክ በዚ ባዘጋጀሁልህ የውሸት ውንጀላ እከስሃለሁ ማለታቸው ነበር። ህዝቡ ፊት ትሁት መስለው ለመታየት የሚጥሩትእኚህ መሪ ከካሜራ ጀርባ "ጀዝባ" ብለው ሲሳደቡ ያዩም ለማመን ተቸግሮ ነበር። ነገር ግን እውነተኛ ማንነትን ደብቆ አይቻልም።

ይህ በፈገግታና ረኸርሙ ምላሳቸው የታጀበው ንግግራቸው ቀድሞውኑ ያልጠዋጠላቸው አንዳዶች በግዜ "ቅቤ ምላሱ" በማለት ሊተቹዋቸው ሞክረዋል።

ሰውዬው ፈገግታቸውን ከቬትናሞች የወረሱ ይመስላል። የቬትናም ዜጎች በጣም በተናደዱ ጊዜ በጥርሳቸው ፈገግታ የታጀበ ሳቅን ይስቃሉ። የነሱን ባህሪ ያልተረዳ ሰው ያዝናናቸው ወይም ያስደሰታቸው ይመስለውና ድርጊቱን ሊቀጥል ይችላል። የመሪያችን የዶ/ር አብይ አህመድ ሳቅም የቬትናም ሳቅ እንደሆነ መረዳት የግድ ይላል።በግዜ ሂደት ሁሉም ማስመለሶች ግልፅ እየወጡ ይገኛሉ። ከፈገግታው ጀርባ ያለው አምባገነንነትም እየተገለጠ ነው።





## የፊንፊኔ ጉዳይ ከምን ደረሰ ?

ባለፉት ሁለት ሶስት አመታት የአዲስ አበባን ማስተር ፕላንን በመቃወም የኦሮሞ ህዝብ ትግል ህወሃት ከስልጣን የማስወገድ ግቡን መቷል። በዚን የትግል ጊዜ ዋነኛ የኦሮሞ ህዝብ ፖለቲካዊ ጥያዎች ውስጥ አንዱ የነበረው የፊንፊኔ ባለቤትነት ጉዳይ ነው። አሁንም የኦሮሞ ህዝብ በሙሉ በቀድሞ የንጉሳዊ አገዛዝ ዘመን ከአንድ ክፍለዘመን በፊት በሀይል ለቀው እንዲቀጣ የተደረገውን ቀየውን መመለስ ይፈልጋል። በራሱ ቀዬ ወይም ከተማ እየተረገጠ፣ እንዲሸማቀቅ እየተደረገ፣ እየተፈናቀ እንዲሁም ማንነቱንና ባህሉን እየተነጠቀ ከመቶ አመታት በላይ የኖረው የኦሮሞ ህዝብ ይህንን ሁሉ ዘመን የታገለው የተነጠቀውን ቀዬውን ወይም ፊንፊኔን መልሰው የራሱ ለማድረግ ነው። መልሰው የራሱ ለማድረግ ሲባል ግን ሌሎችኦሮሞ ያልሆኑትን ህዝቦች ገፍተው ብቻውን ሊኖርበት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል ። ይሄ አንዳንድ ሴረኛና ሀላፊነት የጎደላቸው የፖለቲካ ነጋዴዎች የኦሮሞን ህዝብ ከሌሎች ህዝቦችጋር በማጋጨት ጠላት እንዲበዛበት እራሳቸው የፈጠሩት ደባ ነው። አንድም የኦሮሞ ፖለቲከኛ ይህንን ብሎ አያውቅም። ቢልም ከኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም። ይልቁኑ ተቃውሞ ይገጥመዋል እንጂ። ምክንያቱም የኦሮሞ ህዝብ ባህልና ወግ የተመሰረተው በአቃፊነት ላይ ስለሆነ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ሌሎችን አቃፊ ህዝብ በመሆኑ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚኖሩትን ሌሎች ህዝቦችን አንድም ቀን በከፋት አይን አይተው አያውቅም። ታዲያስ እንዴት ብዙ ሌሎች ኦሮሞ ያልሆኑ ህዝቦች በሚኖሩበት በጂማ አዳማ ወይም ሻሸመኔ

ያላለውን ፊንፊኔ ላይ ደርሰው ሌሎች ህዝቦችን ለመግፋት ሲባል ግማሽ ክፍለዘመንን የፈጀ ህዘባዊ ትግል ያደርጋል?

የኦሮሞ ህዝብ የታገለው እምብርቴ ብሎ በሚጠራት ከተማ በሙቶ አመታት ውስጥ ያጣውን ማንነቱን ባህሉን ቋንቋውን ሀብቱን መልሰው ሌሎችን ሳይገፋ ለመኖር ሲል ነው።

የኦሮሞ ህዝብ ትግል ውጤት በሆነው የኢፌድሪ ህገመንግሥት አንቀፅ 49 "የኦሮሚያ ክልል፣ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።" በማለት የተቀመጠው የሙብት ጉዳይ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ህዝቡ ባለፉት አመታት በተደጋጋሚ በትግሉ ውስጥ እየጠየቀ መቆየቱ ይታወሳል። በማለት ያስቀመጠው አብይ ጉዳይ የኦሮሞ ህዝብን የአገር ባለቤትነት ጥያቄ አሳንሰው የወሰነበት ምላሽ ነው።

ፊንፊኔ የኦሮሚያ ክልል አካል ለመሆኗ ከአፄ ሚኒሊክ ቀደም ብለውና ከዚያም በኋላ የነበሩ ታሪኮቿ ከተማዋ የኦሮሞ ጎሳዎች መኖሪያ እንደሆነች ያትታሉ። ሌላው ፊንፊኔ ከተማ ያላት የመልክአ ምድር አቀማመጥና መገኛ ከኦሮሚያ ክልል ውጪ የማንም እንድትሆን አይፈቅድም። ፊንፊኔ አሁን ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ብሔራዊ መንግስት መቀመጫ ሆና እያገለገለች ነው። ፊንፊኔ የኦሮሞ ህዝብ ርስት ለመሆኗ ከዚ በላይ አመላካች ማስረጃ የለም። ጉዳዩ ፊንፊኔ የማን ነች የሚለው አይደለም። ይልቁንስ ህዝቡና መንግስት መካከል ሲያከራክር የቆየው የኦሮሞ ህዝብ ፊንፊኔን





አስመልክተው የጠየቃቸው ህገመንግስታዊ የሙብትና የሞራል ጥያቄዎች መቼ ነው ምላሽ የሚያገኙት የሚለው ነው ።

ዶ/ር አብይ አህመድ ገና ወደ ጠቅላይ ሚኒስተርነት ከመምጣታቸው በፊት ኦሮሚያ ከፊንፊኔ የሚታገኘው ልዩ ጥቅም በዝርዝር መውጣት አለበት ከሚለው አልፈው የኦሮሚያ እምብርት የሆነችውን ፊንፊኔ የባለቤትነትን ጉዳይ በቅርቡ የምናረጋግጥ ይሆናል እያሉ በተዘዋወሩበት ሁሉ ለኦሮሞ ህዝብ ቃል ሲገቡ እንደነበር ሁሉም ያስታውሰዋል።

ዶ/ር አብይ አህመድ ወደ ጠቅላይሚኒስትርነት ከመጡ በኋላ ከኮዬ ፈጬው ቀውስ ጋር ተያይዘው የፊንፊኔና ኦሮሚያ ክልል ወሰን ማካለል ጥያቄ በማገርሸቱ ይህንን የሚያጠና አንድ ኮሚቴ ያዋቀሩ መሆናቸውን በሚዲያ የገለፁ ቢሆንም አሁን ላይ ኮሚቴውያለበት አይታወቅም ። መጀመሪያውኑ ህዝቡን ዝም ለማስባል የተዘጋጀ የሞኝ መፍትሄ እንጂ ጠቅላዩ ሚኒስትሩ የፊንፊኔና ኦሮሚያ ክልል የወሰን ማካለል ጉዳይ ፍፃሜ እንዲያገኝ ፍላጎታቸው አይደለም።

የፊንፊኔ ጉዳይን አስመልክተው የዶ/ር አብይ አህመድ አቋም ከህወሃትም በባሰ መልኩ ተስፋ አስቆራጭ ነው። ህወሃት አልተሳካላትም እንጂ በማስተር ፕላን ስም ፊንፊኔን ዙሪያዋ ካሉት የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ቀላቅላ ከኦሮሚያ ክልል በመነጠል ራሱን በቻለ መንግስት ለማስተዳደር ነበር። የዶክተር አብይ አህመድ አቋም ደግሞ እንኳን ፊንፊኔን መልሰው የኦሮሚያ ክልል አካል ሊያደርጋት ይቅርና፣ ይልቁኑ ፍላጎታቸውና እየሄዱበት ያለው አቅጣጫ ህገመንግስቱን በመቀየር የፌደራል ስርዓቱን በማፍረስ ኦሮሚያ ክልል የሚለው ተበትነው ኦሮሚያ የሁሉም ብሔሮች መሬትና ግዛት እንድትሆን ማድረግ ነው። የፊንፊኔ የባለቤትነት ጥያቄን

አስመልከተው የኦሮሞ ህዝብ ምርጫ ሁለት ነው። አንደኛው የዶ/ር አብይ አህመድን መንግስት ጋር ሆነው እንኳን ፊንፊኔ ሌሎች የኦሮሚያ ከተሞችም በሌሎች ህዝቦች አስተዳደር ስር እስኪወድቁ መጠበቅ። ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ የወደፊት የትግል አቅጣጫን በማስቀመጥ በአንድነት የተለመደውን ህዝባዊ ትግል ማስቀጠል ነው።





## ቀጣዩ የኢትዮጵያና የኦሮሞ ህዝብ ትግል ምን መሆን አለበት?

ዛሬ ዛሬ አገራችን በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ሆና መንታ መንገድ ላይ ቆማ የሚትገኝበት አንዱና ቀዳሚው ምክንያት እንደመንግስት አገርን እየመራ የሚገኘው ኢህአደግ በመዳከሙ ነው። በአገር ውስጥ የነበሩትም ሆነ ከውጪ የገቡት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እጃቸውን ተጠምዝዘውና እርስበርስ ባለመግባባታቸው እንኳን ህዝቡ የሚተማመንባቸው ሊሆኑ ይቅርና እራሳቸውንም ችለው መቆም አቅቶአቸዋል። የኢህአደግ አራቱ እህት ድርጅቶች እርስበርሳቸው እየተግባቡ አይደለም። ህወሃት፣ ብአዴን/አዴፓ፣ ኦህደድ/ኦዲፒና ደህዴን ለስም ኢህአደግ ተብለው አንድ ላይ እየተጠሩ ይገኛሉ እንጂ ከተለያዩ ቆይተዋል። ህወሃት ለፌደራሉ መንግስት ተጠሪነት የሌለው ራሱን የቻለ መንግስት መስርተዋል። ብአዴን/አዴፓ በስልጣን ሽኩቻና በቡድን ፍላጎቶች ልዩነቶች ምክንያት እርስበርሱ እየተጫረሰ ነው። ደህዴን ምን እየሰራ እንደሆነ ለማወቅ የበላው ጅብ አልጮህ ብለዋል። ኦህደድ/ኦዲፒ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው ይገኛል። በሃያ ስምንት አመታት ታሪኩ ኢህአደግ ይህን ያክል ተዳከመው አላየንም። በኢህአደግ ታሪክ ውስጥ አባላቶቹ እንደዚህ በአደባባይ ውጊያ ሲገጥሙና ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ የተቀመጡ ባለስልጣናት በዚህ መልኩ ሲገዳደሉ ታይተው አይታወቅም። ከአንድ አመት በፊት ስርነቀል ለውጥ አድርጌያለሁ ያለው ፓርቲ ብዙም ሳይገፋ ዛሬ በዚህ መልኩ በውርደት መታየቱ የያዘው በሽታ የማይድን ነቀርሳ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው። አሁን አገሪቷ እየተመራች የሚትገኘው በኢህአደግ የጋራ አቋም መሰረት ሳይሆን በግለሰቦች ፍላጎት መሰረት ነው።

ሁሉም ተበታትነው በመሰለኝ እሳቤ እየተራመደ ነው። በመሰለኝ እሳቤ አገርን መምራት አይቻልም። አገር በጋራ ወጥ የሆነ ፖሊሲ፣ ስትራተጂ፣ ህግና ደምብ እንጂ በመሰለኝ የመሪዎች አካሄድ ሊትመራ አትችልም። በዚህ አካሄድ አገርንና ህዝብን መምራት ከተሞከረም ውጤቱ ለመሪዎቹም ሆነ ለተመሪው ህዝብ አደገኛ ነው። የያዝነው መንገድ ለኢህአዴግና አመራሮቹ አደጋ ከመሆኑ በተጨማሪ ለአገርንም ሊያጠፋ ይችላል። ከውጪ ከሚመጣ ጠላት ይልቅ ውስጣዊ አለመግባባቶችና ሽኩቻ አገርን የማፍረስ አቅም አላቸው። ስለዚህ  እነዚህና ሌሎች የአገራችንን ነባራዊና ተጨባጭ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በመገንዘብ ህዝቡ አገሩንና እራሱን ከተጋረጠበት የመጥፋት አደጋ ሊጠብቅ አልፎም ሊያድን ይገበዋል። ኢትዮጵያ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ብቸኛዋ የጋራ መኖሪያ መሆኗን ተቀብለን፤ ሊያናውጣት እየነፈሰ ካለው አውሎ ንፋስ፣ ሲበላት እየተንቦገቦገ ካለው እሳትና ሊያጥለቀልቃት ከተቃረበው ማዕበል የመኖሪያ ጎጆአችንን ሊናድናት ይገባናል።

እየነፈሰ ያለው አውሎ ንፋስ፣ የተለኮሰው ሰደድ እሳት፣ አቅጣጫውን ወደኛ ያደረገው ማዕበል ደርሶ የተጠለልንባትን ብቸኛዋ የመኖሪያ ጎጆአችንን አፍርሰው እኛንም ከማጥፋቱ በፊት አስቀድመን መላ በመዘየድ ሊናስቆመውና ለቀጣዩም ዘመናችን ለአደጋ ተጋላጭ ያልሆነች አስተማማኝ ጎጆአችንን እንደ አዲስ ሊንገነባ ጊዜው አሁን ነው።

አገራችንን ለማዳን እንደ አንድ አገር ዜጎች በቁርጠኝነት ከወሰንን በመጀመሪያ አሁን እየተዳደርንበት ያለነውን ህገመንግስት ተቀብለን መንግስትም እንዲያከብረው ግፊት ማድረግ ይኖርብናል። መንግስት ህገመንግስቱን ባለተከተለ መልኩ እያደረጋቸው ያለውን አሰራሮች





እንዲያቆምና ለሚያደርጋቸው በሙሉ ህገመንግስቱን መሰረት ባደረገ መልኩ መከናወን እንዳለበት ጠበቅ አድርገን ልንነግረው ይገባል። የፌደራል መንግስት የክልል መንግስትን ስልጣን በገፈፈ ጣልቃ ገብነት የየክልሎች ፕሬዝዳንቶች ካሉበት የሃላፊነትና ስልጣን ቦታዎች እንዲነሱ እያደረገ ይገኛል። የፌደራሉን መንግስት ተጠቅመው ግለሰቦች ከውጪ አገራት ጋር ግልፅ ያልሆነ ስምምነቶችን እየተፈራረሙ ይገኛሉ። ህገመንግስቱን መሰረት አድርገው የማንነትና ወሰን ጥያዎችን ያቀረቡ ህዝቦች በህገመንግስቱ መሰረት ምላሽ እያገኙ አይደሉም። የፌደራሉ መንግስት የፀጥታ ሀይሎች ያለክልሉ ጥያቄ ዘልቀው በክልል የሚኖሩትን ዜጎች እያሸበሩ ይገኛሉ። ዜጎች በነፃነት በአገሪቷ ክፍሎች ተዘዋውረው የመስራትና ሀብት የማፍራት ህገመንግስታዊ መብታቸው ተገፈዋል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤት ህገመንግስታዊ መብቶቻቸው በአዋጅና በኢህአዴግ መተዳደሪያ ደምብ ተወስዶባቸዋል። መንግስት መጪውን ምርጫ በማራዘም ሳይመረጥ ሊያስተዳድር እያኮበኮበ ነው። እነዚህና ሌሎች መንግስት ህገመንግስቱን በጣሰ መልኩ ያከናወናቸውና እያከናወናቸው የሚገኙ መሆኑን በመረዳት፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት በመንግስት በኩል የሚፈፀሙ የህግና ደምብ ጥሰቶች ላይ ትኩረት አድርገው ሊያወግዛቸው ይገበዋል።

በተጨማሪ የጋራ አገራችንን ከተጋረጠባት አደጋ ለማዳን ሲባል ሁሉም ኢትዮጵያውያን እርስበርሳቸው በሀይማኖትና ዘር ከመጋጨት በመቆጠብ የሚወክሉትን የማህበረሰብ ክፍል ወይም ቡድን የፖለቲካ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች በሰለጠነ መንገድ ማቅረብና እርስበርሳቸውም እንዲወያዩባቸው ማስሻል የሁሉም ድርሻ መሆን አለበት።

በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉ ፖለቲከኞችና አባላት ከብሽሽቅና ስሜት ፖለቲካ እራሳቸውን ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የጋራ መፍትሄ ላይ በማተኮር ሃላፊነታቸውን እንደዜግነት ግዳጃቸው በመውሰድ ሃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

ወደ የኦሮሞ ህዝብ ትግል ሲንመጣ የኦሮሞ ህዝብ ግልፅ የሆነ ፖለቲካዊ አላማዎችና ጥያዎችን ይዘው ግማሽ ክፍለዘመን በላይ የፈጀ ትግል ማድረጉ እሙን ነው ። በነዚህ ረጂም የትግል ጉዞው ብዙ ፈተናዎችን አልፏል። በርካታ ድሎችንም አስመዝግቧል። የኦሮሞ ህዝብ በረዥሙ የትግል ጉዞ ውስጥ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ብርቅዬ ልጆቹን ገብሯል። ዘመን የማይሽራቸው የትግል መሪዎችም አፍርቷል። በኦሮሞ ህዝብ ጥቅም የማንደራደሩ በርካቶች አልፈዋል። በህይወት ያሉም አሉ ። በቅርቡ የነበረው የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከሌሎች የትግል ምዕራፎች በተሻለ በርካታ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄዎችን ይመልሳል ተብለው ቢጠበቅም በመጨረሻ ከሽፏል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ለኦሮሞ ህዝብ ቃል ገብተው የተቀበሉን አደራ በልቷል። ዶክተር አብይ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ፍላጎት የላቸውም። የቋንቋ፣ ራስን ማስተዳደር፣ ፊንፊኔ፣ መሬት፣ ‵ኢኮኖሚ፣ ማዕድን ወዘተ ጥያቄዎች በዶክተር አብይ አህመድ ሊመለሱ እንደማይችሉ ሁሉም ኦሮሞ ማወቅ ይኖርበታል። አንዴ ህዝቡን ሸውዶታል። ዶክተር አብይ አሁን የቆሙት ከኦሮሞ ህዝብ በተቃራኒ ነው። ሰውዬው አሃዳዊ ስርዓትን ሊጭኑብን ያለእረፍት እያሴሩ ካሉት አካላት ጋር ናቸው።

በቀጣይ መላው የኦሮሞ ህዝብ አንድነቱን ጠብቀው ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል ። ህዝቡ ትግሉን በመንግስት መዋቅር ውስጥ ሆኖም በውጪ





ማካሄድ አለበት ። ትግሉ እንዳይደናቀፍ ሲባል የኦሮሞ ህዝብ አንድነት መላላት የለበትም ። እንደበፊቱ የኦሮሞ ህዝብ በአንድነት እንዳይነሳ ኦሮሞን የመከፋፈል ሴራ በሰፊው እየተሰራ ስለሆነ ይንን ነቅተው በመጠበቅ ሊያከሽፈው ይገባል። ስርዓት ያልፋል። የኦሮሞ ህዝብ አንድነት ግን ለመኖሩ ዋስትና መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ህዝቡ በየአካባቢው በተናጠል ሳይሆን በመደራጀት ወደፊታችን ላይ ሊመክርበት ይገበዋል ። ወጣቱ ከሚያምናቸው ፖለቲከኞች ጋር ሊመክር ይገበዋል። በየአካባቢው የሙስና ድርጊቶችን በጋራ መዋጋት የህዝቡ በተለይም የወጣቱ ድርሻ መሆን አለበት ። ወጣቱ የስራ እድል እንዲፈጠርለት መጠየቅ የዜግነት መብቱ ነው። የወደፊቱን የትግል አቅጣጫ ለመወሰንም ሆነ አመራሮቹን ለመምረጥ ቀደም ብሎ ትግሉን ሲመሩ ከነበሩትየህዝብ ልጆች ከሆኑጋር መወያየት ምርጫ የሌለው ግዴታ ነው።

## የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከየት ተነስተው ወዴት እየሄደ ነው?

የኦሮሞ ሕዝብ በሚኒሊክ ጦር ተወሮ፣ ሀገሩንና ነፃነቱን ካጣበት ጊዜ ጀምሮ ከመቶ ዓመታትበላይ ይነስ ይብዛ፣ ይጥበብ ይስፋ እንጂ በተናጠልም ሆነ በተደራጀ መልክ ያጣውን ነፃነቱንና ሀገሩን ለመመለስ ያልተቋረጠ ትግል ስያካሄድ እስከ ዛሬ ደርሷል። ስለዚህ የኦሮሞ የነፃነት ትግል ከየት እንደ ተነሳ ወይንም እንዴት እንደጀመረ በሰፊው ማብራራት አስፈላጊአይሆንም። ይህ ትግል የደረሰበት ደረጃና ዛሬ ምን ላይ እንደሚገኝም ለጠላትም ሆነለወዳጅ ግልፅ ስለሆነ፤ ይህንንም ጉዳይ በጥልቀት ማብራራት አስፈላጊ አይደለም።

ነገር ግን በጥልቀት መታየት ያለበትና እኔም በዚህ ላይ የራሴን ሀሳብ ለመግለፅየምፈልገው ጉዳይ፣ ይህ ትግል ወዴት እየሄደ ነው? የሚለውን ጥያቄ ማየትና፤ እንደዚሁም በዚህ የነፃነት ትግል ውስጥ የነበሩት፣ አሁን ያሉትና ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉት ፈተናዎችን በስፋት ማየት ነው። ይቆይ ይፍጠን፣ ይርዘም ይጠር እንጂ ይህ ትግል ወደ መጠናቀቂያው እንደተቃረበ ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ ወዴት እንደሚያመራና የትኛውን ግብ እንደሚደርስ አሁን ማወቅ ያስቸግራል። ለምን ቢባል፣ ለዚህ ትግል ዓላማ የሚሰጠው ትርጉምና የትግሉ የመጨረሻ ግብ ምን መሆን እንዳለበት አከራካሪ ስለሆነ ነው። እዚህ ላይምን ማለት እንደፈለኩ እንደሚከተለው ለመግለፅ እሞክራለሁ።

ቀዳሚው የትግሉ ዓላማ የነበረዉ ሰው በላዉን የወያኔን ስርዓት ገርስሶ፤ በሕዝባችን ላይ የተከፈተውን የዘር ማጥፋት ጦርነት ማብቃት ነው። እሱ ተሳክቶአል፡፡ ወያኔም ትግራይ መሽጋለች፡፡የኦሮሞ ወይም የለዉጥ





መንግስት ነኝ የሚለዉ የጠቅላይ ሚኒስተር ዶ/ር አብይ አህመድ መንግስት ወደ ስልጣን ቢመታም የሕዝባችንን ግድያ ማስቆም አልቻለም፡፡ ሕዝባችን ዛሬም እንደ ህወሃት ዘመን ሰላምና ነፃነት አጅግጥሞታል፣ እጅግ ርቦታል። የሚታየዉ ሁሉ የዉቸት ነዉ፡፡ የአስመሳይነት፡፡ የፎቶግራፍ ፖለቲካ፡፡ የሆነዉ ሆኖ ሰፊው የአሮሞ ሕዝብ የምፈልገውና የምመኘውን የምወስንና ከግብ የሚያደርስበት ትግል ባለቤትነት  የምታወቅ ታላቀ የሆነ ሕዝብ ነው። የትኛውም ድርጅትም ሆነ ቡድን ይህንን ልወስንለት አይችልም። ባጭሩየራሱ ዕድል መወሰን ያለበት ይህ ሰፊው ሕዝብ ብቻ ነው ማለት ነው። የትኛውም ኃይል ይህንን ልወስንለት አይችልም። የግል ፍላጎትም ሆነ ምኞት የዚህ ታላቅ ሕዝብ ፍላጎትም ሆነ ምኞት ሊሆን አይችልም። ይህ እውነታ ግልፅ መሆን አለበት።

እንግዲህ የትግሉን የመጨረሻ ግብ በሚመለከት ይህን ያህል ካልኩኝ በኋላ፤ የትግሉን ፈተናዎች በሚመለከት ኣንዳንድ ነገሮችን ማንሳት እሞክራለሁ። የነፃነት ትግሉን ፈተናዎች በሶስት ቦታ ከፍለን ማየት እንችላለን። እነሱም ትላንት የነበሩት፣ ዛሬ ያሉት እና ነገ ሊታዩየሚችሉ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ትላንት የነበሩትን ፈተናዎች እዚህ በሰፊው ማንሳት አስፈላጊ ባይሆንም፣ ነገር ግን ካለፈው ለመማር ይረዳ ዘንድ እነዚህንም ትኩረት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል።

## የኦሮሞ የነፃነት ትግል የትላንትናዎቹ ፈተናዎች

የነፃነት ትግሉ ውስጥ የነበሩትን ፈተናዎች ሁሉ ማንሳትና ማብራራት ቀላል የማይሆን ጉዳይነው።

ከታሪክ መረዳት እንደሚቻለው፣ የመጫና ቱለማ የመረዳጃ ማህበር ምስረታ በፊት የነበረውጊዜ በኦሮሞ ታሪክ ውስጥ የጨለማ ጊዜ እንደነበረ ነው። ምክንያቱም ባለፉትየነገስታት ዘመን በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የማንነት ማጥፋት ዘመቻ ሲካሄድነበር። በዚህ የተነሳ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የኦሮሞ ሕዝብ እንኳንስ መገናኘትቀርተዉ የጋራ ማንነታቸው ለመጥፋት መቃብር አፋፍ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር። ስለዚህ በዚያንጊዜ የነበረው ትልቁ ፈተና የኦሮሞን ማንነት እና ይህንን ትልቅ ብሔር ከጥፋት ማዳን ነበር።

በዚህ ምክንያት በዚያን ጊዜ የነበሩት የኦሮሞ ብሔርተኞች ይህንን ጥፋት ተረድተውመፍትሔ ለመፈለግ ብለው ልዩ በሆነ ስልት የመጫና ቱለማን ድርጅት አቋቋሙ። እዚህ ላይ ግልፅ ማድረግ የምፈልገው አንድ ጉዳይ ከመጫና ቱለማ ምስረታ በፊት የነበሩትእንደ ወሎና ባሌ የመሳሰሉትን ንቅናቄዎች መርሳቴ ወይም መዘንጋቴ ላለመሆኑን ነው።

የመጫና ቱለማን ምስረታ እንደ መነሻ የወሰድኩት ይህ ትግል በተቀናጀ መልክ መቸ እንደተጀመረና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሕዝብን ማንቃት የተጀመረው መቸ እንደሆነ ለመግለፅ ነው።

ከዚያ በፊት የነበሩት ፈተናዎችም ከየትኛውም ፈተናዎች ያላነሱ እንደሆነ የታሪክ ሰዎችማስረጃ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ የመጫና ቱለማ መስራቾችና መሪዎች ያሳለፉት ፈተናዎችታሪክ የማይረሳው ጉዳይ ነው። በዚያን ጊዜ





የነበሩት ታጋዮች ያስመዘገቡት ድሎች ናቸውለዛሬው ትግልና እንደ እሳት እየነደደ ላለው ሕዝባዊ ንቅናቄ መሰረት የጣለው።

ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ምስረታ ጀምሮ እስከ 1991 ድረስ ኦነግን ስፈታተኑት የነበሩትፈተናዎች በሁለት መንገድ ነበሩ። እነዚህም ባንድ በኩል ከጥላት ጋር በጠመንጃ መፋለምሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝባችንን በይበልጥ ማስተማርና ማንቃት ነበር። በዚያን ወቅትበኦነግ ሲመራ የነበረው ትግል የተለያዩ ችግሮችንና ፈተናዎችን በማሻነፍ 1991 ትላልቅድሎችን አስመዝግቧል። ይህ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ የተገኙት ድሎች ናቸው ለጠላት የማይንበረከክና ጭቆናን መሸከም እንቢ ያለውን የቁቤ ትውልድን (Qubee Generation)የወለዱት።

ከ1991 በፊት ኦነግ ውስጥ የተለያዩ ፖለቲካዊ አመለካከትና አይዶሎጂ ቢኖሩም፣ ይህ የነፃነት ትግል መሪ የሆነው ድርጅት አንድነት ያለውና ጠንካራ ግንባር ነበር። እንዲዚያ ባይሆንኖሮ ዛሬ የኦሮሞ ሕዝብ የሚኮራባቸው ድሎች ባልተገኙ ነበር። በመሆኑም ኦነግ ዛሬተከፋፍሎ እቅሙም እንደ ያኔ ባይሆንም፣ አንግቦት የተነሳው ዓላማ በኦሮሞ ሕዝብ ልብናአእምሮ ውስጥ ነው ያለው ቢባል ሀሰት የሚሆን አይመስለኝም። ኦነግ እንደ ድርጅት ቢዳከም እንኳን የተቋቋመለትና ይዞት የተነሳው ዓላማ ነው በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት እንዲያገኝ የሚያደርገው። ስለዚህ እንደ እኔ አመለካከት ይህ ድርጅት መሪዎቹ ስህተትቢሰሩም፣ ድርጅቱ ሁለት ሶስት ቦታ ቢበታተንም፣ መሰደብ፣ መናቅ፣ መረገም የለበትም። ይህድርጅት ለኦሮሞ ያደረገውን መርሳት የለብንም ማለቴ ነው።

እስከ 1991 ድረስ በኦነግ የተመራው የነፃነት ትግል ታላላቅ ድሎችን ማስመስገብ ብቻሳይሆን የዚህ ትግል ግብ ምን መሆን እንዳለበትም ግልፅ

አድርጎ ነበር። ከ1991 በኋላ የኦሮሞ ሕዝባዊ ንቅናቄ እስከ ጀመረበት እስከ 2015 ድረስ የኦሮሞ የነፃነት ጎራ (camp) መድከምና መቀዝቀዝ ብቻ ሳይሆን ስግብግብነት፣ ለስልጣን ሩጫ፣ ክህደት፣ የኦሮሞባሕልና ስርዓት ማጣት፣ መተቻቸት፣ መሳደብ፣ ትዕግስት ማጣት፣ በራስ መተማመን መጥፋት፣በጠላት ላይ የሚደረገውን ትግል ትተው እርስ በርስ ላይ ጦርነት ማካሄድ ወዘተ በእጅጉ የታዩበት ወቅት ነበር። እነዚህ መጥፎ ልምዶች ዛሬም ቢሆን አልጠፉም። እነዚህ ደግሞ ለነፃነት ትግሉ ፈተናና እንቅፋት ከመሆንም ባሻገር፣ የትግሉንም ዓላማና ግብ ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ናቸው።





## የኦሮሞ የነፃነት ትግል ጠላቶች እነማን ናቸው

ይህ የነፃነት ትግል የውስጥና የውጭ ጠላቶች እንዳሉት ከማንም የሚደበቅ ጉዳይአይደለም። የውጭው ጠላት፥ከዚህ በፊት የኦሮሞን ሕዝብ ሲገዙና ሲጨቁኑ የነበሩ፤ ወደፊትም ይህንን ለማድረግናየድሮውን የጭቆና ስርዓት በተዘዋዋሪ መልሰው ሕዝባችን ላይ ለመጫን ምኞት ያላቸውኃይሎች ናቸዉ፤ እነዚ አካላት አሁን በተመንግስት ገብተዋል፤

ሌላው ደግሞ ይህንን የነፃነት ትግል ከተቻለው ለማጥፋት ካልሆነ ደግሞ ለማዳከም ብለውከላይ የተጠቀሱትን ኃይሎች የሚረዱ፤ ከኦሮሞ ነፃነት ትግል ጥርጣሬ ያላቸው የውጭመንግስታት በተለይም በምዕራቡ ክፍል የሚገኙ የውጭ ኃይሎች ናቸው። እንደኔ አመለካከት የውስጥ ጠላቶችን በሶስት ቦታ ወይም ቡድን ከፍለን ማየት እንችላለን። እነሱም፥አንደኛ ፥ በጠላትና ለጠላት የተገዙት፣ ለሆድ አደሮች፣ ከሃዲዎች፣ ሰርጎ ገቦችና ሰላዮችሌት ተቀን ለጠላት የሚሰሩ ተላላኪዎች፡፡ ሁለተኛ ፥ በቀጥታ ጠላት ባይሆኑም፣ ባካሄዳቸው ግን ግልፅ አቋም የሌላቸው፣ ግልፅዓላማና ግብ የሌላቸው፣ ትላንት ያሉትን ዛሬ የሚሸሩ፣ አውቀውም ይሁን ባለማወቅ(አብዛኛውን ጊዜ ግን እያወቁ) የዚህን የነፃነት ትግል ዓላማና ግብ በተሳሳተ መንገድለመግለፅ የሚጥሩና አሁንም ኢያረጉ ያሉ ናቸዉ፡፡ ሶስተኛ ፥ በየትኛውም ምክንያት ይሁን ለዚህ ትግል ምንም ደንታ የሌላቸው፤ በጠላትፕሮፓጋንዳ በቀላሉ የሚሸነፉ፣ የሚነገራቸውን መቀበል እንጂ የራሳቸው የሆን ምንም አቋምየሌላቸው፤ የማንነት ችግር ያለባቸው ሲሆኑ እነዚህ በቀጥታ ጠላትባይሆኑም አሁን ግን ኦዲፒን እየሞሉት ነዉ፡፡ እነዚህበተዘዋዋሪ ለትግሉ እንቅፋት የሚሆኑ ስራዎችን የሚሰሩ ናቸው።

## የኦሮሞ የነፃነት ትግል የዛሬቹ ፈተናዎች

ከትግሉ ጠላቶች የውስጥ ጠላት በጣም አደገኛ ነው። ይህ ጉዳይ አንድ የኦሮሞን ተረትያስታውሰኛል። እሱም ስለ እሳት ሲወራ ነው። "Diina jedhanii irƨaa hin fagaatan;fira jedhanii itti hin dhiyaatan" ወደ አማርኛ በግረድፉ ሲተረጎም፥ "ጠላት ነው ብለውአይርቁትም፣ ዘመድ ነው ብለው አይቀርቡትም" የሚል ነው። የትግሉ የውስጥ ጠላቶች እንደእሳት ናቸው ማለት ነው። ሲያቀርቧቸው የተለያዩ ተንኮልና ደባ እየሰሩ እውነተኛ ታጋዮችንለመጉዳት ይሞክራሉ። ካልሆነም በርቀት የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ የታጋዮች ሞራልእንዲነካ ይጥራሉ። ጠላት ናቸው ተብለው እንዳይርቁ ደግሞ የራስ ዜጎች ናቸው። ወገኖች ናቸዉ:: ታዲያየራሱን ወገን ወይም ዜጋ ከሚከድ ዜጋ የበለጠ ምን ጠላት አለ??

በኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ የሚኒሊክ ወታደሮች ኦሮሞን በኃይል ካሸነፉበት ጊዜ ጀምሮእስከ ዛሬ ድረስ የኦሮሞ ጠላቶች በራሳቸው ኃይል ጠንካራነት በቻ ሳይሆን፣ ኦሮሞን በኦሮሞበመያዝ ነው እስከ ዛሬ የደረሱት። ከሃዲና ተላላኪዎች ናቸው ለጠላት መንገድ እያሳዩሕዝባችንን ሲያስጨፈጭፉ የቆዮት፣ አሁንም ያሉት። ሲመጡና ሲያልፉ የቆዩት ጠላቶቻችንበሙሉ በውጭ ዕርዳታ ታንክና ተዋጊ አይሮፕላን ይኑራቸው እንጂ እውነት የትግሉ የውስጥጠላቶች ትብብር ባይኖር ኖሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኦሮሞን ሕዝብ በጭቆና ስር አያቆዩም ነበር።

አሁንም ኦሮሞ ነፃ አልወታም:: የኦሮሞን የነፃነት ኃይል የሚያዳክሙትና የውጭው ጠላት እንዲጠነክር የሚያደርጉትየውስጥ ጠላቶች ናቸው። የኦሮሞ አንድነት እንዳይኖር ወይም እንዲዳከም የሚያደርጉትምየውስጥ





ጠላቶች ናቸውእንጂ የውጭ ጠላቶች ጥንካሬ አይደለም። በርግጥ የውስጥጠላቶች በሚፈጥሩት ቀዳዳ በመጠቀም የውጭ ጠላት ውስጣችን ገብተው አንድነታችንእንዳይጠነከር ዕድል ያገኛሉ። ይህ ነው ለነፃነት ትግሉ እንቅፋትና ፈተና ሆኖ ትግሉም ግቡን እንዲስት ያደረገው።

ስለ ኦሮሞ የነፃነት ትግል ግብ ማንሳቴ ካልቀረ፣ እስቲ ሌሎች ለትግሉ ዓላማም ሆነ ግብፈተና የሆኑትን አንዳንድ ነገሮች ለማንሳት ልሞክር። እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነገር ዛሬአንዳንድ የኦሮሞ ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ወይንም አክቲቪስቶች የሚያደርጉትን ቢናይ፥ እነሱ ለኦሮሞ የነፃነት ትግል የሚሰጡት ፍቺ የሚያወናብድና ሕዝባችንን የሚያሳስትሆኖ ይታያል። እንዴት ቢባል፥

አንደኛ ፥ አገራችን ኦሮሚያ በወታደራዊ ኃይል እንደተያዘችና ዛሬም እንደዚሁ ተወራ እንዳለችየዘነጉ ወይንም ደግሞ እያወቁ መሬት ላይ ያለውን እውነታ ለመደበቅ የምሞክሩ ይመስላሉ። አሁንም ምእራብ ኦሮሚና ጉጂ በአስቸኳይ ግህ አዋጅ እየተዳደረ ነዉ::

ሁለተኛ ፥ የትግሉን መነሻ ወይም ዓላማውን በተሳሳተ መንገድ ለመግለፅ ከሞከሩ በኋላበዚህ ግንዛቤ ላይ በመመስረት የትግሉም ግብ የኦሮሞየአገር ባለቤትነትን ማረጋገጥ እንዳልሆነ አድርገው በማቅረብ፤ ኦሮሞ ኢትዮጵያየምትባለውን አገር ነፃ ለማውጣትና ዲሞክራሲያዊ አገር ለማድረግ እንደሚታገል

በማስመሰል የኦሮሞ የነፃነት ትግል ዓላማና ግብም ይኸው እንደሆነ አድርገው ያቀርባሉ።

ሶስተኛ ፥ የኦሮሞ ሕዝብ ለረጅም ጊዜ ሲጠይቅ የቆየውን መሰረታዊ ጥያቄ በተለይምደግሞ የኦሮሞ ወጣቶች ቄሮ ( Qeerroo ) ሲያነሱት የቆዩትን

ጥያቄዎች፣ አንግበውእየወጡ የነበሩት መፈክሮች ማስረጃ ሆነው ሳሉ፣ የኦሮሞ ሕዝብ እየጠየቀ ያለው የፖሊሲሪፎርም ( Policy Reform) ነው ባማለት የትግሉን ዓላማ እጅግ አሳንሰው በማቅረብ፣ጥቃቅን ለውጦች ከተደረጉ የኦሮሞ ሕዝብ በነዚህ ተደስተው ትግላቸውን እንደሚያቆሙአድርገው ሰውን ለማሳመን ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ።

ሌላው የሚገርም ነገር ዛሬ በይበልጥ የሚታሰር፣ የሚሰቃይ፣ የሚገደል፣ ከአገር የሚሰደድ፣ንብረቱ የሚቀማ፣ ከቀዬውና መሬቱ የሚፈናቀል ወዘተ ኦሮሞ ሆነው እያሉ፤ እስከ ቅርብ ጊዜድረስ ሌሎች ሕዝቦች ዝምታን መርጠው በነበሩበት ወይንም ባሉበት ወቅት፣ ሳይጠሩ፣ሳይጠየቁ ኦሮሞ ለመላው ኢትዮጲያ መሞት አለበት፤ መስዋዕትነት ከፍሎ ይህችን አገርማኖር አለበት በማለት ለሰው ብለው ሕዝባችንን ለማስጨረስ ሕዝብን እያሳሳቱ ነው። እስቲልብ በሉ፥ ኦሮሞ እስከ ዛሬ ድረስ ለዚች አገር የከፈለውን ትልቅ መስዋዕትነት ለነፃነቱ ቢከፍልኖሮ ዛሬ የአገሩ ባለቤት መሆን በቻለ ነበር።

እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ሲነሱ እኔ ኦሮሞ ከኢትዮጲያ ችግርም ሆነ ጥላቻ ኖሮት አይደለም። የዚህ የነፃነት ትግል ዓላማም ሆነ ግብ ወደማይሆን አቅጣጫ እንዳይወሰድ ይህንን መጠበቅናመከላከል ግዴታ ስለሚሆን ነው። አለበለዚያ በወደቁት ጀግኖቻችን ደምና አጥንት መቀለድይሆናል። ለሁሉም ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይና እውነታ ግን የኦሮሞ የነፃነት ትግል ዋናውዓላማ የኦሮሞ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን ማስቻል መሆን አለበት ::

በዚህ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሂደትም ሆነ ውሳኔ ውስጥ ከማን ጋርና እንዴት መኖርእንዳለበት የሚወስነው ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ነው።





በነገራችን ላይ የራስን ዕድል በራስየመወሰን መብት የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች በመሆኑ፣ ይህ ጉዳይ ለኦሮሞ ብቻ ተብሎ የተቀመጠ ተደርጎ መታየትም ሆነ መወሰድ የለበትም።